

በደቡብ ወሎ ዞን

የበቶ፣ ወለቃና አባይ ሸለቆ ታሳቢ ብዜራዊ ፓርክ

የተፈጥሮ ሃብትና የቱሪዝም አቅም ዝርዝር የጥናት ሪፖርት

በባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ

በዱር እንስሳት ጥናት፣ ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ዋና የስራ ሂደት

የዱር እንስሳት ጥናት የትግበራ ቡድን

ሰኔ/2004 ዓ.ም

ባህር ዳር

ማውጫ

1. መግቢያ 1
2. የጥናቱ መነሻ 2
3. የዝርዝር ጥናቱ አስፈላጊነት 2
4. ዝርዝር ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ አጠቃላይ ሁኔታ 2
4.1. ዝርዝር ጥናቱን ለማካሄድ የተመረጡ ቦታዎች፣ መገኛና ስፋት 2
4.2. የአየር ንብረት 3
4.3. የመሬት አቀማመጥ 5
5. የዝርዝር ጥናቱ ዓላማ 6
5.1. ዝርዝር ዓላማ 6
6. የጥናቱ ስልቶችና ቁሳቁሶች 6
6.1. ስልቶች 6
6.2. በጥናቱ ጥቅም ላይ የዋሉ ቁሳቁሶች 7
6.3. በመስክ ጥናቱ የተከናወኑ ተግባራት 7
7. የዝርዝር ጥናቱ ሂደትና የተዳሰሱ አካባቢዎች 8
8. ከዝርዝር ጥናቱ የተገኙ ውጤቶች 15
8.1. የበቶ፣ ወለቃና አባይ ሸለቆዎች ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ ዝርዝር የተፈጥሮ ሃብት ሁኔታ ትንተና 15
8.2. የሶሽዮ ኢኮኖሚ ሁነቶች 19
8.3. የቱሪዝም አቅም፣ 24
8.4. የወለቃ፣ በቶና አባይ ሸለቆ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ላይ እየደረሱ ያሉ ችግሮች 31
8.5. ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች እና ጠቀሜታቸው 35
8.5.1. የበቶ፣ ወለቃና አባይ ሸለቆ የተፈጥሮ ደን ጥብቅ ሰፍራ የመሆን አቅም 35
8.5.2. ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚኖረው ጠቀሜታ 38
8.6. የታ/ጥ/ስፍራው ጠቀሜታና ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች ጥምረት ዝምድና 39
8.7. የበቶ፣ የወለቃ እና አባይ ሸለቆ የተፈጥሮ ደን ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ የመሆን ዋና ዓላማ 40
9. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች 42
10. ወደፊት መከናወን ያለባቸው ስራዎች 42
11. የጉዳዩ ቀጥተኛ ባለቤቶችና የባለድርሻ አካላት ተግባራትና ኃላፊነት ትንተና 44
12. ማጠቃለያ 47
13. ዋቢ መጽሐፍት (References) 48
ዕዝል 1. የተመዘገቡ ዋና ዋና እፅዋት መረጃ 49
ዕዝል 2. የተመዘገቡ ዋና ዋና የእፅዋፍት ዝርያዎች መረጃ 51
ዕዝል 3. የተመዘገቡ ዋና ዋና የአጥቢ እንስሳት ዝርያዎች መረጃ 53
ዕዝል 4፡ በ2002 የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት መሰረት የሚኖረው ቤተሰብና ህዝብ ብዛት በቁጥር 54
ዕዝል 5፡ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ በሚገኝባቸው ቀበሌዎች ያሉ የቤት እንስሳት መጠን በቁጥር 55
ዕዝል 6፡ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ በሚገኝባቸው ቀበሌዎች በ2003/04 የምርት ዘመን 56
ዕዝል 7. ዋና ዋና የጅፒኤስ መረጃዎች 57

1. መግቢያ

በክልሉ የሚገኙ በርካታ የደን ክልሎች ለረጅም ዓመታት በሰዎች ተዕዕኖ ውስጥ ሆነው ቆይተዋል። መሬቱና በውስጡ የሚገኙ ሌሎች የተፈጥሮ ሐብቶች በከፍተኛ ሁኔታ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። በአሁኑ ጊዜ በክልሉ 4 ብሄራዊ ፓርኮች ያሉና ይህም በIUCN መስፈርት መሰረት ከጠቅላላው የመሬት ስፋት 10 ከመቶ መሸፈን ያለበት ቢሆንም እነዚህ ጥብቅ ስፍራዎች ከጠቅላላ የክልሉ ቆዳ ስፋት የሚሸፍኑት 2 ከመቶ ብቻ ነው። ከዚህ አንፃር በቀጣዮቹ 5 ዓመታት በክልሉ ያሉ የጥብቅ ስፍራዎችን ቁጥር ከ4 ወደ 11 በማሳደግ በክልሉ የሚገኘውን ወካይ የተፈጥሮ ስርዓተ ምህዳር መጨመር ከስትራቴጅክ ዘመኑ የተቋመ ቁልፍ ግቦች አንዱ ነው። ስለሆነም ተቋመ በአዋጅ ከተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት አንዱ በክልሉ ውስጥ ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ያለቸውን የተፈጥሮ ደን ቦታዎች በአለም የተፈጥሮ ጥበቃ ሕብረት (IUCN) መስፈርት መሠረት በማጥናትና በመከለል ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኙ ማስቻል ነው።

በዚህ መሰረት በ2003 ዓ.ም በደቡብ ወሎ ዞን በወግዲ ወረዳ ውስጥ በወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደን አካባቢ በተደረገ የመስክ ጥናት አካባቢው ካለው ስፋትና ስርዓተ ምህዳር አንፃር ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚስችል የዳሰሳ ጥናት ተካሂዶ ብሄራዊ ፓርክ የመሆን አቅም እንዳለው ጥናቱ ያመለክታል። ይሁን እንጅ ከጥናቱ በኋላ በዞኑ ከአጋር አካላት ጋር ውይይት ስናደርግ በቦረና እና በከላላ ወረዳዎች በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ሊካተት የሚችል ሰፊ የደን ሽፋን እንደነበረና አብሮ መፈተሽ እንደነበረበት ጥቆማ ሰጥተውን ነበር።

በተጨማሪም በመጀመሪያ የዳሰሳ ጥናት ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም እንዳለው የተለየ አካባቢ ቦታውን በአዋጅ ለማቋቋምና ለመከለል የሚያስችል ስለጥብቅ ስፍራው ዝርዝር መረጃ ማሰባሰብና ማደራጀት ከተቋመ አብይ ተግባራት መካከል አንዱ ነው። በ2004 ዓ.ም የወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደን ዝርዝር ጥናት ሲሰራ በከላላና ቦረና ወረዳዎች የበቶና አባይ ሸለቆዎች ወስጥ የሚገኘው የተፈጥሮ ደንም አብሮ በዝርዝር ጥናቱ ውስጥ ተካቶ መጠናት እንዳለበት በዕቅድ እንዲያዝ ተደረገ። ስለሆነም የክልሉን ወካይ የተፈጥሮ ስርዓተ ምህዳር ለማሳደግ በደቡብ ወሎ ዞን በከላላ፣ ወግዲና ቦረና ወረዳዎች ውስጥ የሚገኘውን የበቶ፣ የወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደን ዝርዝር ጥናት ማካሄድ ተቋመ በዚህ ዓመት ለመስራት ከያዛቸው ተግባራት መካከል አንዱ በመሆኑ የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩን ለመከለልና ህጋዊ ለማድረግ የሚያስችል ከግንቦት 5 እስከ ሰኔ 5/2004 ዓ.ም በመስክ በመገኘት ዝርዝር ጥናት ተካሂዷል።

በመሆኑም በዚህ የጥናት ሪፖርት ከዝርዝር ጥናቱ የተገኙ የተሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ዝርዝር ተፈጥሮዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ሃብቶች፣ ስርዓተ ምህዳር ዓይነትና ሁኔታ፣ ማህበራዊና ኢከኖሚያዊ ሁኔታዎች፣ ቁልፍ ችግሮች እና ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ዝርዝር መረጃዎች ተካተዋል።

ስለሆነም ሪፖርቱ ከዳሰሳ እና ዝርዝር ጥናቱ የተገኙ መረጃዎችን፣ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን ለመከለልና ህጋዊ ለማድረግ የሚያስችሉ መረጃዎችን፣ ሊያሳክ የሚችላቸውን ዓላማዎች፣ ወደ ፊት መከናወን ያለባቸውን ስራዎች እና የባለድርሻ አካላትና የጉዳዩ ቀጥተኛ ባለቤቶችን ተግባርና ኃለፊነት በመለየት ውሰኔ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ ተዘጋጅቷል።

2. የጥናቱ መነሻ

በዓለምና አገር አቀፍ ደረጃ እየተባባሰ የመጣውን የሙቀት መጨመርና የአየር ንብረት መዛባት ለመከላከል የተፈጥሮ ሃብቶችን መጠበቅና ማልማት የወቅቱ ዋነኛ ትኩረት ሁኗል፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ የምክክር መድረኮችም ዋነኛ አጀንዳ ከመሆኑም በላይ በአካባቢ ጥበቃ ላይ ትኩረት ሰጥተው ለሚሰሩ እንደኛ ላሉ ድሃ ሀገራት ባላቸው የተፈጥሮ ወካይ ስርዓተ ምህዳር ስፋት መሰረት ድጎማ የሚደረግበት አሰራር እየተዘረጋ ይገኛል፡፡ ስለዚህ በክልል ደረጃ በአካባቢ ጥበቃ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራቱ እየደረሠ ያለውን አካባቢያዊ ለውጥና የአየር መዛባት ከመታደግም በላይ ሀገራችን ለድሃ ሀገራት የሚሰጠውን ድጎማ ከሌሎች ሀገሮች በተሻለ ሁኔታ እንድታገኝ የሚያስችል ከመሆኑም በላይ በክልሉ የሚገኘውን ወካይ የተፈጥሮ ስርዓተ ምዳህር ለማሳደግ የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡

ሌላው ለጥናቱ መነሻ የሆነው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ክልሉን በስድስት የልማት ቀጠናዎች በመክፈል በወጣው የአምስት አመት (2002-2007) ስትራቴጅክ እቅድ በመካከለኛዉ የልማት ቀጠና ውስጥ ትኩረት የተሰጣቸው የመንግስት ደኖች እና የብርቅዬ የዱር እንስሳት የሚኖሩባቸው ሌሎች የተፈጥሮ ደን ቦታዎች በእርሻ መስፋፋት፣ በልቅ ግጦሽና ደን ጭፍጨፋ ምክንያት ከፍተኛ ጥፋት እየተፈፀመባቸው ስለሆነ ጥበቃ እንደሚያስፈልጋቸው በመገለጹና ይህንንም በጥናት ማረጋገጥ በማስፈለጉ ነው፡፡

በተጨማሪም የአባይ ወንዝ ባለው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች የተነሳ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትኩረትና ዕውቅና የተቸረው አካባቢ ነው፡፡ ይሁን እንጅ የአባይ ሸለቆን ተከትሎ ያለው የዕጣን ዛፍ ደን በህገ-ወጥ መንገድ የእርሻ ማሳን ከማስፋፋት ጋር ተያይዞ በአብዛኛው በመጨፍጨፍ ላይ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ይህን በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና የተቸረውን አካባቢ የሚወክል ስርዓተ ምህዳር ማግኘት ሌላው የጥናቱ መነሻ በመሆኑ ጥናቱ ሊካሄድ ችሏል፡፡

3. የዝርዝር ጥናቱ አስፈላጊነት

በቀጣዮቹ 5 ዓመታት በክልሉ ያሉ የጥብቅ ስፍራዎችን ቁጥር ከ4 ወደ 11 በመጨመር በክልሉ የሚገኘውን ወካይ የተፈጥሮ ስርዓተ ምህዳር ማሳደግ በማስፈለጉ፣

በበቶ፣ ወለቃና አባይ ወንዞች አካባቢ የሚገኙ የተፈጥሮ ደኖች ውስጥ የሚገኙ ለመጥፋት የተቃረቡና እድሜ ጠገብ የሆኑ ዛፎች ለጣውላ ምርት ሲባል ከፍተኛ የደን ጭፍጨፋ የሚደርስባቸው በመሆኑ፣ በዚህ አካባቢ የሚገኘው የእጣንና የሙጫ ዛፎች ለእርሻ መስፋፋት ሲባል ከፍተኛ ጥፋት የሚደርስባቸው በመሆኑ፣ በብዙ ቦታዎች በክልሉ የአባይ ሸለቆን ሊወክል የሚችሉ ቦታዎች እየጠፉ ስለሆነ ይህንን አካባቢ ሊወክል የሚችል ስርዓት ምህዳር በማጥናት ተፈጥሮዊ ወካይ ስርዓተ ምህዳር ማግኘት አስፈላጊ ሁኖ በመገኘቱ ዝርዝር ጥናቱ ሊካሄድ ችሏል፡፡

4. ዝርዝር ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ አጠቃላይ ሁኔታ

4.1. ዝርዝር ጥናቱን ለማካሄድ የተመረጡ ቦታዎች፣ መገኛና ስፋት

የበቶ፣ ወለቃና አባይ ሸለቆዎች ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ የሚገኘው በደቡብ ወሎ ዞን በከላላ፣ ወግዲ እና ቦረና ወረዳዎች የበቶ፣ የወለቃና የአባይ ሸለቆዎችን ተከትሎ ነው። ሶስቱም ወረዳዎች በደቡብ ወሎ ዞን በምስራቅ አማራ አካባቢ የሚገኙ ሲሆን በመካከለኛው አማራ የልማት ቀጠና ከሚገኙ 31 ወረዳዎች ውስጥ ይጠቃለላሉ። የወግዲ ወረዳ ከአዲስ አበባ 582 ኪ.ሚ፣ ከባህር ዳር 662 ኪ.ሚ፣ ከደሴ 182 ኪ.ሜ፣ የከላላ ወረዳ ከአዲስ አበባ 562 ኪ.ሚ፣ ከባህር ዳር 642 ኪ.ሚ፣ ከደሴ 162 ኪ.ሜ እንዲሁም የቦረና ወረዳ ከአዲስ አበባ 580 ኪ.ሚ፣ ከባህር ዳር 660 ኪ.ሚ፣ ከደሴ 180 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ላይ ይገኛሉ።

ታሰቢ ብሄራዊ ፓርኩ ከወግዲ ወረዳ በኩል 11 ቀበሌዎች (03፣ 07፣ 08፣ 09፣ 013፣ 015፣ 016፣ 017፣ 018፣ 026 እና 034)፣ ከከላላ በኩል 3 ቀበሌዎች (017፣ 019 እና 020) ከቦረና ወረዳ በኩል ደግሞ 1 ቀበሌ (024) በአጠቃላይ በደቡብ ወሎ ዞን ከ15 ቀበሌዎች ጋር ይዋሰናል። የአባይ፣ ወለቃና በቶ ወንዝን ተከትሎ ከደቡብ ወሎ ዞን በተጨማሪ ፓርኩ ከምስራቅ ጎጃም ዞን የእነብሴ ሳር ምድር፣ የእናርጅና እናውጋ እና የሸበል በረንታ ወረዳዎች፣ ከኦሮምያ ክልል የደራ ወረዳ፣ ከሰሜን ሸዋ ዞን ደግሞ የሚዳ ወረሞ ወረዳ ጋር ይዋሰናል።

በ1993 ዓ.ም አቶ ጫኔ ገበየሁ ለሁለተኛ ድግሪ ማሞያ በወግዲ ወረዳ በ4 ቀበሌዎች ላይ (016፣ 017፣ 018 እና 026) ባደረጉት ጥናት በዚህ አካባቢ ያለው የተፈጥሮ ደኑ ሽፋን 8245 ሄ/ር ያህል ስፋት ሊኖረው እንደሚችል አስቀመጥዋል። ከዚህ ውስጥ 3478 ሄ/ር ያህል የሚሆነው የተፈጥሮ ደኑ ክፍል ከ1100 እስከ 1500 ሜ ከፍታ የሚገኝ ሲሆን 4767 ሄ/ር ያህል የሚሆነው ደግሞ ከ1500 እስከ 1800 ሜ ባለው ከፍታ ውስጥ ይገኛል። በተጨማሪም 42 ከመቶ የሚሆነው የደን ሽፋን ለእጣንና ሙጫ ምርት አገልግሎት ለሚውሉ ሀገር በቀል ዕፅዋቶች (*Boswellia papyrifera* and *Commiphora africana*) ተፈጥሮዊ መኖሪያ ቦታ እንደሆነ ታውቋል። ከሁሉም ወረዳዎች ግብርና እና አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤቶች ባገኘነው መረጃ መሰረት ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ከ40 እስከ 50 ሺህ ሄ/ር ያህል ስፋት ሊኖረው እንደሚችል ይገመታል። ይህ ቦታ ከወሎ-ጎጃም መሰመር ከአባይ ድልድይ ጀምሮ እስከ ከላላ-ጃማ መስመር የበቶ ወንዝ ድልድይ አጠገብ ድረስ በግምት ከ$10^0$39’47.8’’ እስከ $10^0$25’46.7’’ ሰሜን ላቲቲዩድና ከ$38^0$30’08’’ እስከ $39^0$06’13.5” ምስራቅ ሎንግቲውድ ላይ ይገኛል።

4.2. የአየር ንብረት

የመካከለኛው አማራ የልማት ቀጠና ባለው የመሬት አቀማመጥ ከፍታው ከባህር ወለል በላይ ከ1096-4261 ሜትር የሚደርስ ሲሆን አራቱን ዓይነት የአግሮ ኢኮሎጅ ዞን በውስጡ ይዞ ይገኛል (ውርጭ፣ ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆላ)። ይህ ቀጠና ካለው የቆዳ ስፋት 54.4 ከመቶ ደጋ፣ 38.3 ከመቶ ወይና ደጋ፣ 6.3 ከመቶ ቆላ እና 0.9 ከመቶ ደግሞ የውርጭ የአግሮ ኢኮሎጅ ዞን እንደ ሚሸፍን መረጃዎች ይጠቁማሉ። በቀጠናው 87 ከመቶ የሚሆነው አካባቢ ከ900-2000 ሚሜ ዝናብ የሚያገኝ ሲሆን

አማካይ አመታዊ የዝናብ መጠን ደግሞ 933.2 ሚሜ ነው፡፡ ቀጠናው የሁለት እርጥብ ወቅቶች- የመኸርና በልግ ወቅት ዝናብ /Bimodal Rain fall/ ተጠቃሚ በመሆኑ በአብዛኛው አካባቢ በዓመት ሁለት ጊዜ የሰብል ምርት ማምረት ይቻላል፡፡ እረጅሙ የእርጥብ ወቅት ከሰኔ እስከ መስከረም ያለው ወቅት ሲሆን ሌላው ከመጋቢት እስከ ግንቦት ያለው የበልግ ዝናብ ወቅት ነው፡፡ በተጨማሪም የቀጠናው አመታዊ ከፍተኛ አማካይ የሙቀት መጠን 22.2 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሲሆን ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ደግሞ 11.2 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ነው፡፡



ምስል 1. የበቶ፣ ወለቃና አባይ ሸለቆ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ የሚገኝባቸውን አካባቢዎች የሚሳይ ካርታ

ከግብርና እና አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤቶች ባገኘነው መረጃ መሰረት የከላላ አግሮ ኢኮሎጅ አብዛኛው ወይና ደጋ (87 ከመቶ) ሲሆን ቀሪው ቆላማ (13 ከመቶ) ነው፡፡ የወግዲ ወረዳ (ከፍታው ከባህር ወለል በላይ ከ1100 እስከ 2964 ሜ ይደርሳል) አየር ንብረት ደግሞ በ3 አግሮኢኮሎጅካል ዞን (ወይና ደጋ 59.45 ከመቶ፣ ቆላ 39.7 ከመቶ እና ደጋ 0.85 ከመቶ) የተከፈለ ነው፡፡ በአንፃሩ የቦረና ወረዳ ባለው የመሬት አቀማመጥ ከፍታው ከባህር ወለል በላይ ከ1100

(አባይ ሸለቆ) እስከ 4280 (ጎላቴ ተራራ) ሜ የሚደርስ ሲሆን አራቱንም የአግሮ ኢኮሎጅ ዞን ይዞ ይገኛል፡፡

የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ አግሮ ኢኮሎጅ ከባህር ወለል በላይ በሚገኝበት ከፍታ የሚወሰን ሲሆን ከፍታው ከ1108 ሜ (አባይና ወለቃ መጋጠሚያ ቀበሌ 016) እስከ 1821 ሜ ወይናያ ት/ቤት አጠገብ (ቀበሌ 015)፣ ከ1152 ሜ ከወሎ-ጎጃም መስመር አባይ ድልድይ አጠገብ እስከ 1845 ሜ በሰራት ጎጥ አባይና የሹም ወንዝ መገናኛ አጠገብ እንዲሁም ከ1233 ሜ (ወለቃና በቶ ወንዝ መገናኛ) እስከ 1508 ሜ የቱሉ ጅሌ ከፍተኛ ቦታ ድረስ ከቀበሌ 017 ጫፍ (በቶ ወንዝን ተከትሎ ከላላ ወረዳ)፣ ቀበሌ 03 ጫፍ (የወለቃ ወንዝን ተከትሎ ወግዲ ወረዳ) እስከ ቀበሌ 024 (ቦረና ወረዳ) የአባይ ወንዝን ተከትሎ የወሎና ጎጃም መስመር ከድልድዩ ዝቅ ብሎ ድረስ ያለውን ሜዳማ፣ ተራራማና ወጣገባ የደን መሬት የሚያጠቃልል በመሆኑ በአብዛኛው ቆላማ የአየር ንብረት አለው፡፡

ከግብርና ጽ/ቤት ባገኘነው መረጃ መሰረት የወግዲ ወረዳ ዓመታዊ የዝናብ መጠን ስርጭት ከ600 እስከ 1100 ሚ.ሚ የሚደርስ ሲሆን አማካይ ዓመታዊ የዝናብ መጠን 850 ሚ.ሚ ነው፡፡ የሙቀት መጠኑም 20 እስከ 27^0C ይደርሳል፡፡ ይሁን እንጅ እንደ አቶ ጫኔ ገበየሁ (1993) ከሆነ የተፈጥሮ የደን ክልሉ አማካይ ዓመታዊ የዝናብ መጠን ከ1200 እስከ 1400 ሚ.ሚ ይደርሳል፡፡ እንዲሁም አማካይ ዓመታዊ የሙቀት መጠን 18.5 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሲሆን ዝቅተኛው ዕለታዊ የሙቀት መጠን 11.4 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ከፍተኛው ደግሞ 25.5 ዲግሪ ሴንቲግሬድ እንደሚደርስ ይታመናል፡፡ የከላላ ወረዳ ዓመታዊ የዝናብ መጠን ስርጭት ደግሞ ከ700 እስከ 1200 ሚ.ሚ የሚደርስ ሲሆን እንደ አቶ አባተ ሽፈራው (2002) ከሆነ የቦረና ወረዳና አካባቢው በዓመት ከ889 እስከ 1500 ሚ.ሜ የሚደርስ የዝናብ መጠን የሚያገኝ ሲሆን አመታዊ አማካኝ የሙቀት መጠን ከ14 እስከ 19 ዲግሪ ሴንቲግሬድ እንደሚደርስ ይገመታል፡፡

4.3. የመሬት አቀማመጥ

የወግዲ ወረዳ የመሬት አቀማመጥ 50 ከመቶ ሜዳማ፣ 11 ከመቶ ሸለቆማ፣ 27 ከመቶ ወጣገባ፣ 12 ከመቶ ተራራማ፤ የከላላ ወረዳ የመሬት አቀማመጥ 10 ከመቶ ሜዳማ፣ 20 ከመቶ ሸለቆማ፣ 47 ከመቶ ተራራማ፣ 23 ከመቶ ወጣገባ፤ የቦረና ወረዳ የመሬት አቀማመጥ 20 ከመቶ ሜዳማ፣ 10 ከመቶ ተራራማ፣ 40 ከመቶ መጣገባ፣ 30 ሸለቆማ እንደሆነ ከግብርና ጽ/ቤት ያገኘነው መረጃ ያመላክታል፡፡ የበቶ፣ ወለቃና አባይ ሸለቆዎች ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ከፍታው ከ1108 ሜ ጀምሮ እስከ 1845 ሜ እየጨመረ የሚሔድ በመሆኑ በውስጡ የተለያዩ መልከአምድራዊ ገፅታዎች አሉት፡፡ የበቶ፣ የወለቃና አባይ ወንዞችን ተከትሎ የሚገኙ የውሃ ዳር ደኖችን (Riverine Vegetation) የሚወክል ስነ-ምህዳር የያዙ ስፍራዎች ሙሉ በሙሉ ሜዳማ ሲሆኑ እጅግ ማራኪ በመሆናቸው የቱሪስት መስህብነታቸው የጎላ ነው፡፡ አጋማይት፣ አቡ ጠንጠቃ፣ ደድሃሬ፣ ጠማሜ፣ መጋጠሚያ፣ ዲዳ ዋጮ፣ ቀዋ ዳባ፣ ጥቁር እንጨት፣ ወልጊሃ፣ ቡልቡል፣ አገዩና ሚራቱ እና ቱሉ ጅሌ ሜዳማ እና ከፍተኛ የደን ቦታዎች ከሆኑት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እነዚህ ደኖች በውስጣቸውም እጅግ በጣም ግዙፍና ዕድሜ ጠገብ የሆኑ ዛፎችን አቅፈው የያዙ በመሆናቸው ለዘቦታ ጥበቃ (In-situ Conservation) ጠቀሜታቸው የጎላ ነው፡፡ በተለይ የወለቃና የአባይ ወንዝ መጋጠሚ አካባቢ ያለው ቢች ከተፈጥሮ ደኖቹ

ጋር ተጣምሮ በሌላ አካባቢ የማይገኝ የተለየ መልከዓምድር ይጥራል። በተለይ በበጋ ወቅት የተለየ መዝናኛና መዋኛ መሆን ይችላል። የውሃው አቀማመጥ ለጀልባ ትራንፖርት አመቺ ነው። ከሜዳማ ቦታዎች ቀጥሎ የተፈጥሮ ደኑ ክፍታው እየጨመረ የሚሄድና ለአይን ማራኪ የሆኑ የተለያዩ ሰንሰለታማና ወጣገባ ኮረብታዎች ያሉት ሲሆን በውስጡም በዋናነት አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ ስርዓተ ምህዳርን (Acacia-Boswellia-Commiphora ecosystem) የሚወክል የተፈጥሮ ደን ይገኛል ።

5. የዝርዝር ጥናቱ ዓላማ

በደቡብ ወሎ ዞን በከላላ፣ ወግዲ አና ቦረና ወረዳዎች በበቶ፣ በወለቃና አባይ ሸለቆዎች አካባቢ የሚገኘውን የተፈጥሮ ደን ዝርዝር የብዝሃ ህይወት ሃብት፣ ተፈጥሮዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ መስህብ ሃብቶች ጥናት በማካሄድ አካባቢውን ጥብቅ ስፍራ ለማድረግ የሚያስችል መረጃ ማሰባሰብ እና ማደራጀት፣

5.1. ዝርዝር ዓላማ

- በበቶ፣ ወለቃና አባይ ሸለቆዎች ወስጥ የሚገኘውን የተፈጥሮ ደን ዝርዝር የብዝሃ- ህይወት ሃብትና የተፈጥሮ ገጽታ ይዘት ጥናት ማካሄድ፣
- በበቶ፣ ወለቃና አባይ ሸለቆዎች ወስጥ የሚገኘውን የተፈጥሮ ደን እና አካባቢው የሚገኙ የሶሽዮ ኢኮኖሚና የቱሪስት መስህብ ሃብቶችን በመለየት ለቱሪዝም ዕድገት ያላቸውን አቅም ማጥናት፣
- ጉዳዩ የሚመለከታቸው አጋር አካላት ሊኖራቸው የሚችለውን ተግባርና ኃላፊነት በመለየት ወደፊት አካባቢው ወደ ጥብቅ ስፋራነት የሚመጣበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

6. የጥናቱ ስልቶችና ቁሳቁሶች

6.1. ስልቶች

- በበቶ፣ ወለቃና አባይ ወንዞች አካባቢ የተፈጥሮ ደን ውስጥ የዳሰሳ ጥናት ለማረድግና የአካባቢውን ዋና ዋና የዱር እንስሳት፣ ዕፅዋት፣ ኢኮሲስተም፣ ተፈጥሮዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ መስህብ ሃብቶች ለመለየት ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት (አስተዳደር፣ ግብርናና ገጠር ልማት፣ አካባቢ ጥበቃ፣ ባህልና ቱሪዝምና አካባቢውን በደንብ የሚያውቁ ግለሰቦች) ድጋፍ ተጠቅመናል፣
- ዝርዝር ጥናቱን ለማካሄድ የጥናት መስመሮችን (Transect lines walk) ተጠቅመናል። የጉዞ መስመሮችን ቀኝት ከማድረጋችን በፊት በጥንቃቄ መርጠናል። የተመረጡ ሁሉም የጉዞ መስመሮች ቢያንስ አንድ ጊዜ ታይተዋል። በጉዞ መስመሩ ግራና ቀኝ እስከ 200 ሜትር ርቀት ድረስ የሚታዩ የዱር እንስሳት፣ ዕፅዋትና ኢኮሲስተም ተመዝገበዋል። በአጎራባች ቀበሌዎችም የሶሽዮ-ኢኮኖሚ መረጃዎች ተሰብስበዋል።
- በጉዞ መስመራችን መነሻና መድረሻችንን ጨምሮ አስፈላጊና የተመረጡ የጅፒኤስ መረጃዎችን ወስደናል። የዱር እንስሳት ቅኝት ለማካሄድና ለመለየት በዋናነት እይታችንን፣ በተለይም አእዋፋትን ለመለየት ባይኖኩላር እንዲሁም በቅኝታችን ወቅት ማግኘት ያልቻልናቸውን የዱር እንስሳት ለመለየት ፎቶግራፍ በመጠቀም የአካባቢውን ሰዎች ምስክርነት ተጠቅመናል።

በተጨማሪም ቀጥተኛ ያልሆኑ የዱር እንስሳት መለያ ዘዴዎችን እንደ በጠጥ፣ የእግር ዱካ፣ ድምፅ፣ ማደሪያ ቦታዎች፣ መመገቢያ ቦታዎችን ወዘተ ተጠቅመናል፡፡

- የዱር እንስሳትና ዕፅዋትን ለመለየት ፊልድ ጋይድ መፅሃፍትና የረጅም ጊዜ ተሞክሯችንን ተጠቅመናል፡፡ እንዲሁም ለተጨማሪ ማረጋገጫ በሁሉም የጉዞ መስመሮች የፎቶ ቀረፃ ተካሂዷል፡፡ የሶሽዮ-ኢኮኖሚ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ከሚመለከታቸው የወረዳና የቀበሌ አካላት ጋር የቡድን ውይይትና መጠይቅ ስልቶችን ተጠቅመናል፡፡
- በIUCN መስፈርት መሰረት የተቀመጡ መመዘኛ ነጥቦች በመጠቀም ታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎችን የመግለፅና መረጃዎችን የመተንተን ስራ ተሠርቷል፡፡
- የሚመለከታቸውን የዞንና የወረዳ የመንግስት መሣሪያ ቤት ኃላፊዎችና ባለሙያዎችን በማነጋገር ሁለተኛ ደረጃ መረጃ ለማሰባሰብና እንዲሁም ግብረ መልስ ለመስጠት ተሞክሯል፣
- በአካባቢው ላይ ከአሁን በፊት የተሰበሰቡና የተጠኑ መረጃዎችን ተጠቅመናል፣

ከላይ በተዘረዘሩት ስልቶች መሠረት የተፈጥሮ ደኑን ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም የሚያሟሉ መሰረታዊ እውነታዎች፣ ዓላማዎች፣ የባለድርሻ አካላት ተግባራት እና ወደ ፊት ተግባራዊ መሆን ያለባቸው ጉዳዮችን ለመለየት ተችሏል፡፡

6.2. በጥናቱ ጥቅም ላይ የዋሉ ቁሳቁሶች

ይህን ዝርዝር ጥናት ለማካሄድ እንደ ጂፒኤስ፣ ባይኖኩላር፣ ዲጂታል ፎቶ ካሜራ፣ ቪዲዮ ካሜራ፣ ጋይድ ቡክ (የአእዋፋት፣ የአጥቢዎችና ዕፅዋት ማረጋገጫ መጽሐፍት)፣ በዓለማቀፍ የተፈጥሮ ጥበቃ ህብረት (IUCN) ጥብቅ ሥፍራዎች ምደባ መስፈርት መሠረት ለመገምገም የሚያስችል የመረጃ መሰብሰቢያ ቅጽ ወዘተ የመሳሰሉ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ብዝሃ ህይወትና የተፈጥሮ ገጽታዎችን፣ በአካባቢው የሚገኙ ባህላዊ፣ ኃይማኖታዊና ታሪካዊ የቱሪዝም መስህብ ሀብቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት ዝርዝር ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

6.3. በመስክ ጥናቱ የተከናወኑ ተግባራት

- ❖ የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ስርዓተ ምህዳርና የብዝሃ ሕይወት ሃብቶች ተለይተዋል፣
- ❖ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በIUCN መስፈርት መሠረት ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅምና ደረጃ በሚገባ ተተንትኗል፣
- ❖ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥና ወጭ ለቱሪዝም ምቹ የሆኑ ተፈጥሮዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ ቅርሶች ተለይተዋል፣
- ❖ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና እንስሳትና ዕጽዋት ዝርዝርና ሳይንሣዊ መጠሪያ ተለይቷል፣
- ❖ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ የሚኖረውን ህብረተሰብ የሶሽዮ-ኢኮኖሚ መረጃዎች ተሰብስበዋል፣
- ❖ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ጥበቃ ላይ የሚደርሱ መሰረታዊ ችግሮች ተተንትነዋል፣
- ❖ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን ለመከለልና ህጋዊ ለማድረግ ወደ ፊት መከናወን ያለባቸው ተግባራት ተዘርዝረዋል፣
- ❖ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ጥብቅ ስፍራ ቢሆን የሚያሳካቸው ዓላማዎች ተለይተዋል፣

- የታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን ለመከለልና ህጋዊ ለማድረግ የአጋር አካላት ሚና ተተንትኗል፣

7. የዝርዝር ጥናቱ ሂደትና የተዳሰሱ አካባቢዎች

በ2003 ዓ.ም በወግዲ ወረዳ ከተካሄደው የዳሰሳ ጥናት መሰረት ከአጋር አካላት በጥናቱ የቦረና እና የከላላ ወረዳዎችም መካተት እንደነበረባቸው በግብረ መልስ ውይይታችን ወቅት አስተያየት አግኝተን ነበር። በመሆኑም በደሴ ከተማ ከአጋር አካላት ጋር በአደረግነው ውይይት በዚህ ዝርዝር ጥናት ከወግዲ ወረዳ በተጨማሪም የአባይ፣ ወለቃና እና በቶ ወንዞችን ተከትሎ ያሉ የከላላ እና ቦረና ወረዳ አካባቢዎችም መካተትና በዝርዝር መጠናት እንዳለባቸው ተስማምተን የጥናታችን የጉዞ አቅጣጫም የአባይ፣ ወለቃና እና በቶ ወንዞችን ተከትሎ መጀመሪያ የቦረና ወረዳ፣ ቀጥሎ ወግዲን በመጨረሻም የከላላ ወረዳ እንዲሆን ነገር ግን የጉዞ መሰመሮችን በተመለከተ ግን ከወረዳ አጋር አካላት ጋር በመሆን እየለየን እንድንሰራ ወስነናል። ስለሆነም በቅኝታችን ወቅት የተከተልናቸው ከፍተኛ የዱር እንስሳት መኖሪያ የሆኑና ለጥናት የሚያመቹ የጉዞ መስመሮችና የተዳሰሱ ቦታዎች የሚከተሉት ናቸው። በዝርዝር ጥናቱ ወቅት 6 ያህል የጉዞ መሰመሮችን ለይተናል። የእያንዳንዳቸው ርዝመትም ከ19 እስከ 69 ኪ.ሜ ሲሆን በIUCN መሰፈርት መሰረትም ሁሉንም አካባቢዎች ለመቃኘትና መረጃ ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል።

1. ከቦረና ወረዳ ዋና ከተማ መካነ ሰላም በመነሳት በዶክስ (016) ቀበሌ ከአባይና ደንቆሮ ወንዝ መገናኛ ጀምሮ ያለውን አካባቢ የተፈጥሮ ደን ሁኔታ መቃኘትና መረጃ መሰብሰብ (Transect Line One)
    - ይህ ቀበሌ የወረዳው ሩቁ ሲሆን ከመካነ ሰላም 32 ኪ.ሜ ይርቃል። ይህን ቆላማ አካባቢ የደንቆሮ ወንዝን ተከትሎ ከሚገኘው የደንቆሮ ጫካ (የቦረና ሳይንት ብሄራዊ ፓርክ) ጋር ለማገናኘት ቁልፍ ቦታ የነበረ ቢሆንም አብዛኛው ቦታ በእርሻና በመንደር መስፋፋት ተቆርጧል። ስለሆነም ከቦረና ሳይንት ብሄራዊ ፓርክ ጋር አያይዞ የአባይ ሸለቆ አካባቢዎችን በጥብቅ ስፍራነት ለማቋቋም ያለው አማራጭ ሃሳብ የሚታሰብ አይሆንም።
    - በቀበሌው ከፍተኛ የመሬት ችግር በመኖሩ ለወጣቶች ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ አባይ ወንዝ ጥግ ድረስ ካለው ደልዳላማ ቦታ ድረስ መሬት ተሰጥቷቸው በአካባበው በወቅቱ የነበረው የደን መሬት ወደ እርሻ መቀየሩን በአይናችን አረጋግጠናል። አልፎ አልፎ የደን መሬቶችን የተመለከትን ቢሆንም በእርሻ ምክንያት የተቆራረጠ መሆኑን አስተውለናል። ወደ ወንዙ ተጠግቶ የመጨረሻው መንደር ውስጥ የሚገኘው ህብረተሰብ የሚኖረው በወይና ደጋው አካባቢ ከ1900 ሜ ከፍታ በላይ ቢሆንም የእርሻ መሬታቸው ግን በቆላማው የአባይና ደንቆሮ ወንዝን ተከትሎ እስከ 1200 ሜ ከፍታ ደርስ ነው። በመሆኑም የእርሻ መስፋፋት እና ደን ጭፍጨፋ የአካባቢው ዋና ዋና ችግሮች ናቸው።
    - አካባቢው በከፍተኛ ሁኔታ በሰዎች ተፅዕኖ ውስጥ የሚኖር ቢሆንም ከዱር እንስሳት መካከል ነብር፣ ከርከሮ፣ ድኩላ፣ ሚዳቋ፣ የዱር ዓሳማ፣ ዝንጀሮ፣ ቀበሮ፣ ጅብ፣ ጭልፊት፣ ገዴ፣ ዝግራ እና ቆቅ የሚገኙ ሲሆን አንቃ፣ ጋባ፣ አደር፣ ደሬ፣ ግራር፣ ቆንጥር፣ ዋጫ፣ ሰፋ፣ ፎጭ፣ በአካባቢው ከሚገኙ ዕፅዋት መካከል ትቂቶች ናቸው።

- ከተፈጥሮ ሃብቱ በተጨማሪም አካባቢው ባለው የመሬት አቀማመጥ በጎጃምና ወሎ አስገራሚ ትዕይንት አለው፡፡ አባይና የደንቆሮ ወንዝ የሚገናኙበት ቦታ ላይ ሆኖ ከምሰራቅ ጎጃም ዞን እነበሴ ሳር ምደርን፣ ከደቡብ ወሎ ዞን መሃል ሳይንትንና ቦረና በአጠቃላይ የ3 ወረዳዎችን ማራኪ የመሬት አቀማመጥ መመልከት ያስችላል /x=449632 y=1193632/፡፡

2. ከቦረና ወረዳ ዋና ከተማ መካነ ሰላም በመነሳት በ018፣ 019፣ 024፣ 025 እና 036 ቀበሌዎች ወሎና ጎጃምን የሚያገናኘውን የመኪና መንገድ ተከትሎ ድልድዩ ድረስ ከዚያም የእናርጅ እናውጋና እነብሴ ሳር ምድር ወረዳዎችን ከሚለየው የጨዬ ወንዝ ድረስ ያለውን አካባቢ የተፈጥሮ ደን ሁኔታ መቃኘትና መረጃ መሰብሰብ (Transect Line Two)

- ይህ የጉዞ መስመር ከመካነ ሰላም እስከ ድልድዩ ድረስ 55 ኪሜ የሚርቅ ሲሆን የቀበሌ 018፣019፣ 024፣ 025 እና 036 አካባቢዎችን ሁሉ ያካትታል፡፡
- በመጀመሪያ በቀበሌ 025 የድፋርሳን ወንዝ ተከትሎ ከማራኪ የመሬት አቀማመጥ ጋር ቅሪት ደን ያለው ሰፊ የደን ቦታ የተመለከትን ቢሆንም ውስጡ ግን ህጋዊ በሆኑ የእርሻ ቦታዎች ተቆራርጧል፡፡ በውስጡ መንደሮች ስሌሉት አካባቢው ከእርሻ እና ከቤት እንስሳት ንክኪ ነፃ ቢደረግ በቀላሉ በማጋገም ወደ ነበረበት ሁኔታ ሊመለስ ይችላል፡፡ አሁን ባለበት ሁኔታ ግን ቦታውን በመከለል ወደ ጥብቅ ስፍራው ማካተት አይቻልም፡፡
- ቀጥሎ 019 ቀበሌን ከቀበሌ 025 እና 024 ድንበር ጀምሮ ያለውን የተፈጥሮ ደን የተመለከትን ሲሆን በሚያሳዝን ሁኔታ የአባይ ወንዝ ጥግ ድረስ በህጋዊ መንገድ ታርሷል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ልክ እንደ ቀበሌ 016 እና 019 ቀበሌዎች ወንዙን ተከትሎ በቀበሌ 018 እና 036 ያሉ ሰፊ የደን ቦታዎች ወደ ህጋዊ የእርሻ መሬትነት ተቀይረዋል፡፡ ከድልድዩ ከፍ ብሎ የቻይናዎች ካምፕ አጠገብ ከወንዙ ጥግ ለአንድ ግለሰብ ለአትክልት ቦታነት የተሰጠው 26.7 ሄ/ር መሬት ይገኛል፡፡



ምስል 2. በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ጥናት ወቅት የተሳተፉ የክልል፣ የዞንና የወረዳ ባለሙያዎች በመስክ ስራ ወቅት

- በመጨረሻም 024 ቀበሌን ከድልድዩ ጀምሮ የእናርጅ እናውጋና እነብሴ ሳር ምድር ወረዳዎችን ከሚለየው የጨዬ ወንዝ ድረስ በጎጃም እና በዚህ ቀበሌ በኩል ያለውን የተፈጥሮ ደን ሁኔታ የተመለከትን ሲሆን ከላይ ከተገለፁት ቀበሌዎች በተሻለ ሁኔታ የተፈጥሮ ደኑ በመልካም ሁኔታ ላይ ይገኛል፡፡ ስለሆነም ከድልድዩ ጀምሮ በቦረና በኩል ቀበሌ 024 የአምዴ፣ መጫሪያና ጨዬ አካባቢዎች ከጎጃም በኩል ደግሞ ታሪካዊ እና ሰፊ ቦታ የሚያካልለው የሶማ

በርሃ (የእናርጅ እናውጋና እነብሴ ሳር ምድር ወረዳዎች) አካባቢው ባለው ያልተቆራረጠ የደን ሽፋን፣ የዱር እንስሳት ዓይነት፣ የመሬት አቀማመጥ፣ ታሪካዊነት ወዘተ ምክንያት ተከልሎ መጠበቅ እንዳለበት ተረድተናል /x=442774 y= 1176366/።

- አካባቢው ማራኪ የመሬት አቀማመጥ፣ ታሪካዊ ዳራ እና የረጅም ጊዜ የጎጃምና የወሎ ህዝብ የመገናኘት ጥያቄ ምላሽ ያገኘበት ቦታ ሲሆን በውስጡ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ነብር፣ ድኩላ እና ከርከሮን ጨምሮ ዋና ዋና የዱር እንስሳት እንዲሁም በከላላ እና በወግዲ በኩል የበቶን፣ ወለቃና አባይ ሸለቆዎችን ተከትሎ ከሚገኘው ስርዓተ ምህዳር ጋር ተመሳሳይነት ያለው የደን ሽፋን (ጥቁር አንጨት፣ ሰምቦ፣ አንቃ፣ ቂልንጦ፣ ጋባ፣ ወዘተ) አለው።

3. ከቦረና ወረዳ ዋና ከተማ መካነ ሰላም በመነሳት 024 ቀበሌ ወግዲንና ቦረና ወረዳ ከሚለየው የየሹም ወንዝ በሰራት ጎጥ ፈሪ መቆሚያ እንዲሁም በጎጃም በኩል የሸበል በረንታ እና የእናርጅ እናውጋ ወረዳዎችን ከሚለየው የደብረ ወርቅ ወንዝ አካባቢ ከሶማ በረሃ ፊት ለፊት ድረስ ያለውን አካባቢ የተፈጥሮ ደን ሁኔታ መቃኘትና መረጃ መሰብሰብ (Transect Line Three)
    - ይህ የጉዞ መስመር 69 ኪሜ የሚረዝም ሲሆን በዋናነት ከቦረና ወረዳ ቀበሌ 024 በሰራት ጎጥ ፈሪ መቆሚያ፣ ከወግዲ ወረዳ የበላይ ዘለቀ የትውልድ ቦታ 034 ቀበሌን (ጎጣ ማሪያም) እና 026 ቀበሌን እንዲሁም ከጎጃም (እናርጅ እናውጋ ወረዳ) በኩል በደብረ ወርቅ እና ጨዬ ወንዝ መካከል ያለውን የሶማ በርሃ ሁሉ ያጠቃልላል።
    - በመጀመሪያ ከድልድዩ ጀምሮ የአባይን ወንዝ በመከተል ወደ ወግዲ ወረዳ አቅጣጫ ቀበሌ 024 ውስጥ በቅደም ተከተል ከአምደ ቀጥሎ የሚገኙትን የንፋሴ፣ ግልገል፣ ፈሪ መቆሚያ፣ ቅምባቅምቦ፣ አጋዘን መፎገሪያ፣ ሁዳድ አካበቢዎችን የተፈጥሮ ደንና የመሬት አቀማመጥ የተመለከትን ሲሆን አልፎ አልፎ በውስጡ ከሚገኙትና ህገወጥ ከሆኑት የእርሻ ቦታዎች በስተቀር የደን ሽፋኑ በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል።
    - ቀጥሎ በጎጃም በኩል ያለውን በደብረ ወርቅና ጨዬ ወንዝ መካከል የሚገኘውን ታሪካዊውን የሶማ በረሃ የደን ሽፋን ሁኔታ የቃኘን ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ አልፎ አልፎ በውስጡ ከሚገኙትና ህገውጥ ከሆኑት የእርሻ መሬቶች በስተቀር በሸበል በረንታ እና እነብሴ ሳር ምድር ካለው ደን የተሻለ ይዞታ አለው።
    - በመጨረሻም የወግዲና የቦረና ወረዳዎችን ከሚለየው የየሹም ወንዝ ጀምሮ የበላይ ዘለቀ የትውልድ ቦታ የሆነውን 034 ቀበሌ የጎጣ ማሪያም ጎጥ ከጎተራ ወንዝ ጀምሮ ወደ ቀበሌ 026 ዞሮ የሚገጥመውን የተፈጥሮ ደን ተመልክተናል። አልፎ አልፎ በውስጡ ከሚገኙትና ህገወጥ ከሆኑት የእርሻ ቦታዎች በስተቀር የደን ሽፋኑ በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል /x=442770 y= 1169738/።
    - ስለሆነም ይህ አካባቢ ባለው ያልተቆራረጠ የደን ሽፋን፣ የዱር እንስሳት ዓይነት፣ የመሬት አቀማመጥ፣ ታሪካዊነት ወዘተ ምክንያት ተከልሎ መጠበቅ እንዳለበት ተስማምተናል። አካባቢው ማራኪ የመሬት አቀማመጥ ያለው፣ በውስጡ ታሪካዊ የሆነውን የሶማ በረሃ እና የበላይ ዘለቀ የትውልድ ቦታ የያዘ እና ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ነብር፣ ድኩላ እና ከርከሮን ጨምሮ ዋና ዋና የዱር እንስሳት ያሉበት ሲሆን በከላላ እና በወግዲ በኩል የበቶን፣ ወለቃና አባይ ሸለቆዎችን ተከትሎ ከሚገኘው ስርዓተ ምህዳር ጋር ተመሳሳይነት ያለው የደን ሽፋን (ጥቁር አንጨት፣ ሰምቦ፣ አንቃ፣ ቂልንጦ፣ ጋባ፣ ወዘተ) አለው።

4. ወግዲ ወረዳ ቀበሌ 015 ከወይናያ ት/ቤት ጀምሮ በጥቁር እንጨት አድርጎና የወለቃና የአባይ ወንዞችን ተከትሎ እስከ ቀበሌ 016 የአባና ወለቃ ወንዝ መጋጠሚያ ደረስ ያለውን አካባቢ የተፈጥሮ ደን ሁኔታ በ2003 ዓ.ም ከተደረገው የዳሰሳ ጥናት አንፃር መገምገምና መረጃ መሰብሰብ (Transect Line Four)፣

- ይህ የጉዞ መስመር የሚሸፍነው 015 እና 016 ቀበሌዎችን ሲሆን 19 ኪሜ ያህል ይረዝማል፡፡
- በመጀመሪያ ከጥቁር እንጨት አካባቢ ጀምሮ የወለቃ ወንዝን በመከተል በቀበሌ 015 ውስጥ የሚገኙትን የደጋ እና ዲዳ ዋጮ አካባቢዎችን የተመለከትን ሲሆን በተራራማው አካባቢ ከኩሜ ገደል ዝቅ ብሎ ያለው ውድላንድ ሽፋን (አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ ስርዓተ ምህዳር) ከበፊቱ ጥናት ጋር ሲነፃፀር አሁንም በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አረጋግጠናል፡፡ ነገር ግን የወለቃ ወንዝ ሜዳማ አካባቢዎችን ተከትሎ በውስጣቸው እጅግ በጣም ግዙፍና ዕድሜ ጠገብ የሆኑ ዛፎችን (Riverine Vegetation) አቅፈው የሚገኙት የደጋ እና ዲዳ ዋጮ አካባቢዎች ግን በደረባ (የከብት ማደሪያ ቦታዎች) እና መስኖ ልማት ምክንያት የደን ሽፋናቸው ከበፊቱ ጥናት ጋር ሲነፃፀር በጣም የተጎዳ መሆኑን አይተናል፡፡ በተለይም ከሜጫ ወንዝ ቀጥሎ የሚገኘው የደጋ ሜዳማ አካባቢ በ6 ቡድን ለተደራጁ 101 ወጣቶች ለመስኖ እርሻ ልማት እንዲውል 31.5 ሄ/ር መሬት ተጠንቶ 7.125 ሄ/ር ተሰጥቷል፡፡ ይሁን እንጅ በመሰክ እንዳረጋገጥነው በአሁኑ ጊዜ በአባልነት የሚሳተፉ 57 ወጣቶች ሲሆኑ 14.5 ሄ/ር መሬት ለመስኖ እርሻ ደኑ ተመንጥሮ የታረሰ ቦታ አግኝተናል፡፡ የበፊቱ ጥናት አሁን ለወጣቶች የተሰጠው እና ለመስኖ እርሻ የተዘጋጀው ቦታ የደን ቦታ (Riverine Vegetation) እንደሆነ ያሳያል፡፡
- ቀጥሎ ከቀበሌ 015 እና 016 ድንበር ጎሆ ወንዝ ጀምሮ የወለቃ ወንዝን በመከተል የቀዋ ዳባ፣ ሰንበቶ ሜዳ እና መጋጠሚያው አካባቢዎችን የተመለከትን ሲሆን ከበፊቱ ጥናት ጋር ሲነፃፀር የሜዳማው እና የተራራማው አካባቢ የደን ሽፋን እስከ አሁንም ድረስ በመልካም ሁኔታ ላይ የሚገኝ ቢሆንም ከተራራዎቹ ጫፍ ጥግ ጥጉን ተከትሎ አዳዲስ ደን ጭፍጨፋና እሳት ቃጠሎ ተመልክተናል፡፡ ይህም እስከ አሁንም ድረስ በአካባቢው ህገ ወጥ የእርሻ መስፋፋት መኖሩን ያመላክታል፡፡
- በተጨማሪም በበፊቱ ጥናት ያልታዩ በአካባቢው በዱር እንስሳት ላይ ከፍተኛ አደን እንደሚካሄድ በቅኝታችን ወቅት በወለቃ ወንዝ ውስጥ ያገኘናቸው ከአካባቢው እንጨት የተሰሩ 17 ያህል የአዳኞች ማረፊያ ጎጆዎች ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ ጎጆዎች አዳኙን ከበርሃ ፀሐይና ከዕይታ ለመከለል የሚያገለግሉ ሲሆን እንስሳቱ ውሃ ሊጠጡ ወደ ወለቃ ወንዝ ሲመጡ በቀላሉ በአዳኞች ወጥመድ ውስጥ ይገቡና በጥይት ይገደላሉ፡፡ በቅኝታችን ወቅት የጥይት ድምፅ የሰማን ሲሆን ከጥቂት ጊዜ ቆይታ በኋላ በቦታው ስንደርስ ነፍሰ ጡር የሆነች ድኩላ ተገድላ የክላሽንኮቭ መሳሪያ የታጠቁ አዳኞችን፣ የተጣለ የድኩላ ሽል እና የእንስሳት ፈርስ አግኝተናል /x=452248 y= 1147315/፡፡ የአባይና ወለቃ ወንዝ መገናኛ አሸዋማ ዳርቻ የሰውን ልጅ ቀልብ የሚሰብ ቦታ ሲሆን ለቱሪዝም ልማት ሊውል የሚችል አካባቢ ነው /x=444805 y= 1146046/፡፡

5. ወግዲ ወረዳ ቀበሌ 015 ከወግዲ-ደራ መስመር ጥቁር እንጨት አካባቢ በመነሳት የወለቃ ወንዝን በመከተል በወለቃና በቶ ወንዝ መጋጠሚያ አድረጎ ወደ ሰሜን በመታጠፍ እስከ ቀበሌ 03 እና 06

ድንበር አባ ጋስጫ የተፈጥሮ ድልድይ ድረስ ያለውን አካባቢ የተፈጥሮ ደን ሁኔታ መቃኘትና መረጃ መሰብሰብ (Transect Line Five)፣

- **ይህ የጉዞ መስመር የሚሸፍናቸው በወግዲ ወረዳ በኩል የ**015፣ 013፣ 09፣ 08፣ 07 **እና** 03 **ቀበሌዎችን እንዲሁም በከላላ ወረዳ በኩል ደግሞ** 020 **ቀበሌን የሚያጠቃልል ሲሆን ርዝመቱም** 57 **ኪ.ሜ ይሆናል፡፡**
- **በመጀመሪያ ከጥቁር እንጨት በመነሳት እስከ ቀበሌ** 015 **እና** 013 **ደንበር የጭባንጭቦ ወንዝ ድርስ የውል አባዱ በር እና ቁምዱ ጎጥ አካባቢዎችን የደን ሽፋን ተመለክተናል፡፡ በአካባቢውም በተራራማው ሸለቆ ከአፋፉ ስር ጥግ ጥጉን ይዞ ከ**50-60 **ለሚሆኑ አርሶ አደሮች በ**1997 **የተሰጡ ህጋዊ የእርሻ መሬቶች ይገኛሉ፡፡ ከእርሻ መሬቶች በኋላ እስከ ወለቃ ወንዝ ድረስ ያለው የተፈጥሮ ደን ሽፋን አልፎ አልፎ ከሚገኙት ህገወጥ የእርሻ መሬቶች በስተቀር በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝና ከተጠበቀ በቀላሉ ወደ ተፈጥሮዊ ይዞታው መመልስ እንደሚችል አረጋግጠናል፡፡ ከዚህ ሌላ በወለቃ ወንዝ ላይ ተጨማሪ** 9 **የአዳኞች ማረፊያ ጎጆችን አግኝተናል፡፡**
- **በመቀጥል ቀበሌ** 013 **ከጭባንጭቦ ወንዝ ጀምሮ የቦሮ፣ ቀዋለንጫ፣ ሽፋታ ቀብር፣ ገብረ ጎሮ እስከ የደራ ሰዎች መሻገሪያ/መተላለፊያ/ኬላ ድረስ ያለውን የደን ሽፋን ሁኔታ የተመለከትን ሲሆን ከፍተኛ የሆነ ህገወጥ የእርሻ መስፋፋት እንዳለበት አስተውለናል፡፡ እንዲያውም የቦታ ሽሚያ ያለ ይመስላል፡፡ በየቦታው የእሳት ቃጠሎና አዲስ ለእርሻ የተዘጋጀ መሬት ይታያል፡፡ ደን ሲጨፈጭፉ፣ ሲያቃጥሉና ሲያርሱ አርሶ አደሮችን አስተውለናል፡፡ ሁሉም ህገ ወጥ ናቸው፡፡ አብዛኞቹ ከሌላ ቀበሌ የመጡና ከአካባቢው ሰዎች መሬቱን በግማሽ፣ ሲሶና እርቦ ለማግኘት የተከራዩ ናቸው፡፡ የተከራይ አከራይ ህገወጥ አርሶ አደሮችም እንዳሉ አስተውለናል (መሬቱን ለእኩል የተከራየው ግለሰብ ለሌላ ሶስተኛ ግለሰብ በሲሶና እርቦ ያከራያል)፡፡ በዚህ አካባቢ ቀደም ሲል በህገ ወጥ ይታረስ የነበረ መሬት ተነጥቆ በማህበር ለተደራጁ** 18 **ወጣቶች በኮንትራት የተሰጡ የእርሻ መሬቶችን አግኝተናል፡፡ ከዚህ ውስጥ ለመስኖ ልማት የሚውሉ ቦታዎችም ይገኙበታል፡፡ አካባቢው ከ**2001 **ዓ.ም በፊት ከእርሻ ተፅዕኖ ነፃ እንደነበር ከአካባቢው ሰዎች ያገኘነው መረጃ ያመልክታል፡፡ አካባቢው ተመሳሳይ ስርዓተ ምህዳር ሲኖረው በዋናነት ስምንት ልብ (ምሳር ገንፎ) እና የሙጫ ዛፍ በብዛት ይገኝበታል፡፡ በአካባቢው የ**7 **አባዎራዎች ከ**266-378 **ክብቶችን በአንድ ጊዜ የሚያስተናግድ የከብቶች ማደሪያ ደረባ አግኝተናል (እረኛ ግቢ ይባላል)፡፡ ከዚህ ሌላ በዚሁ አካባቢ በወለቃ ወንዝ ላይ ተጨማሪ** 2 **የአዳኞች ማረፊያ ጎጆችን አግኝተናል፡፡ በአጠቃላይ ይህ አካባቢ በቀበሌ** 013 **ንዑስ ሁለት ውስጥ ይጠቃለላል፡፡**
- **በመቀጠል ቀበሌ** 013 **ከጫንጮ ወንዝ ጀምሮ የተስኩራ አካባቢን ተመልክተናል፡፡ ይህ ደን የሆራ እና ጠሮ አካባቢን በማካለል እስከ የቡ እርማዚ፣ ሁምሲና ወረዋዩ ጎጥ የእርሻ ቦታ ድረስ ይደርሳል፡፡ ከዚያም ወለቃን ወንዝ ተከትሎ ጎሮ ደጋ እና ቅርጠ የበቶ እና ወለቃ ወንዝ መገናኛ አካባቢ ድረስ ያለውን የደን ሽፋን ተመልክተናል፡፡ አካባቢው ተመሳሳይ ስርዓተ ምህዳር ያለው ሲሆን ልክ ከላይ እንደተገለፁት አካባቢዎች የእርሻ መስፋፋትና ልቅ ግጦሽ የአካባቢው ዋነኛ ችግሮች እንደሆኑ አልፎ አልፎ አዲስ ለእርሻ የተዘጋጁ መሬቶችን እና የእሳት ቃጠሎዎችን በማየት አረጋግጠናል** /x=471042 y= 1148542/፡፡

- በመጨረሻም ከወለቃና በቶ ወንዝ በመጋጠሚያ/ወልጊሃ/ምድማር/ቡልቡል በመነሳት ከዚያም የበቶን ወንዝ (ከላላ ወረዳ ቀበሌ 020) ወደ ምስራቅ በመተው እና የወለቃን ወንዝ ወደ ሰሜን በመከተል በሁለቱም ወረዳዎች በኩል ያለውን የደን ሽፋን በመቃኘት፣ ከዚያም የ013 እና 09 ቀበሌ ድንበርን በማቋረጥ፣ ቀጥሎም የ09 እና 08 ቀበሌ ድንበር የደረቅ ወንዝን በማቋረጥ፣ ከዚያም የ08 እና 07 ቀበሌ ደንበር የኮኬ ወንዝን በማለፍ፣ ቀጥሎ የ07 እና 03 ቀበሌ ደንበር የአጅሃ ወንዝን በማቋረጥ፣ ከዚያም በመጨረሻ የ03 እና 06 ቀበሌ ድንበር አባ ጋስጫ የዓለት ድልድይ (የተፈጥሮ) ድረስ ያሉ አካባቢዎችን የደን ሽፋን ተመልክተናል፡፡ ፈሪ መቆሚያ እና የበራ ፈረስ መጋለቢያ (013 ቀበሌ)፣ ጎም ሰራሬ (08 ቀበሌ)፣ ዳሪሙ እና አርቂ (07 ቀበሌ)፣ ድብድቤ (03 ቀበሌ)፣ ከላላ (020 ቀበሌ-ወልጊሃ፣ መልካ ቡቂ፣ ገዋ ቡልቡል፣ ገዋ ጋስጫ፣ ቆላቲ፣ ለጋሃዳ ጋስጫ፣ ለገጢሮ፣ ሰርጢ ጅቦ፣ መልካ ቂሬምሳ፣ የዓለት ድልድይ) በጉዟችን የተመለከትናቸው የደን ቦታዎች ናቸው፡፡ በዚህ አካባቢ ከህገወጥ እርሻ መስፋፋት በተጨማሪ ለጣውላ፣ ከሰልና ማገዶ ሲባል ከፍተኛ ድን ጭፍጨፋ እንደሚፈፀም በቅኝታችን ወቅት ከተመለከትናቸው ከሰል አካሳዮች፣ እንጨት ነጋዴዎች፣ አዲስ ቃጠሎዎችና ለእርሻ የተዘጋጁ ቦታዎች ማረጋገጥ ችለናል፡፡ በተጨማሪም በከላላ ወረዳ በኩል አነስተኛ የእርሻ መስፋፋት ያየን ሲሆን የደን ሽፋኑም የተሻለ እንደሆነ አስተውለናል /x=479018 y= 1163464/፡፡

6. ከከላላ ወረዳ ቀበሌ 012 ከላላ-ጃማ መስመር ከድልድዩ ዝቅ ብሎ ከኮባ ሸለቆ በመነሳት ከዚያም የበቶ ወንዝን በመከተል እስከ ቀበሌ 019 እና 020 ድንበር የጎፎ ወንዝ ድረስ ያለውን አካባቢ የተፈጥሮ ደን ሁኔታ መቃኘትና መረጃ መሰብሰብ (Transect Line Six)፣

- ይህ የጉዞ መስመር የሚሸፍናቸው በዋናነት የ013 (አናራት)፣ 014 (ደገር)፣ 017 (ጆጆባና ልጮ)፣ 019 (አዲሰ አምባ) እና 020 (ጥራንጥር) ቀበሌዎችን የሚያጠቃልል ሲሆን ርዝመቱም 56 ኪ.ሜ ይሆናል፡፡
- የበቶ ወንዝን ተከትሎ በመጀመሪያ ቀበሌ 012 ከላላ-ጃማ መስመር ከድልድዩ ዝቅ ብሎ ከኮባ ሸለቆ በመነሳት የአሮጌ አዛባ ሸለቆን፣ የጀሬ ሸለቆን፣ የጎራ ሸለቆን፣ የማለሁዳድ ሸለቆን፣ የፎጭ ሸለቆን፣ የጅንጃግሪ ሸለቆን በማቋረጥ እስከ ቀበሌ 012 እና 013 ደንበር በሰቆ አካባቢ እንጣ ምህረት ወይም አረጉ ወንዝ የአትክልት ቦታ ድረስ ያለውን የደን ሽፋን የተመለከትን ሲሆን አብዛኛው ቦታ በእርሻ የተያዘ መሆኑን አረጋግጠናል፡፡ የአረጉ ወንዝን በመጠቀም ከረጅም ጊዜ በፊት ጅምሮ በአካባቢው ሎሚ፣ ቡና፣ ጫት፣ ብርቱካን፣ ፓፓያ፣ ሙዝ እና ጌሾ የሚመረትበት የአትክልት ቦታ አይተናል፡፡
- ቀጥሎ ከቀበሌ 012 እና 013 ድንበር አረጉ ወንዝ በመነሳት የቀይ ገደል እና የዳራ ጥብቅ ደኖችን በማቋረጥ እስከ 013 እና 014 ቀበሌ ድንበር አጤሳ ወንዝ ድረስ ያለውን የደን ሽፋን ተመልክተናል፡፡ ሁለቱም በቀበሌው የደን ቦታ ተብለው የተከለሉና ከእርሻና ሰፈራ ነፃ የሆኑ ቦታዎች ናቸው፡፡ የዳራ የቀበሌ ጥብቅ ደን ቀደም ሲል ከ3 ዓመት በፊት (በ2000) በህገወጥ መንገድ ለ2 ዓመት ታርሶ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ በቀበሌው የደን መሬት ሲከለል ተከልሎ እየተጠበቀ ይገኛል፡፡ሁለቱ ደኖች ከቀበሌ 017 (የቱሉ ጅሌ ደን) እና ቀበሌ 014 (ከብት መጠያና ለቡ አካባቢ) የደን ቦታዎች ጋር 4 አባላት ያሉበት ቡድን/ጉጅሌ/ሚሊሻዎች ተቋቁሞ

እየተጠበቁ ይገኛሉ፡፡ ቡድኑ በሴፍትነት ደመወዝ (ለአንዱ 700 ብር) የሚከፈላቸው ናቸው፡፡ ከቀይ ገደል ደን ይልቅ የዳራ ደን በደን ጭፍጨፋና በእርሻ ምክንያት ሽፋኑ የሳሳ ነው፡፡ ይሁን እንጅ የእነዚህ አካባቢዎች ደን እየተጨፈጨፈ ለማገዶና ከሰል እየዋለ ይገኛል፡፡ ጥበቃውም ከጉጅሌዎች አቅም በላይ ነው፡፡ ከሰል የሚያከስሉና የሚሸጡትን ግለሰቦች በደገር (014 ቀበሌ) የገጠር ቀበሌ ከተማ በመገኘት የሚይዙ ቢሆንም ችግሩን ማስቆም አልቻሉም፡፡ የእጣን ዛፍ (የአድሩስ እንጨት) አጨሳ ወንዝ ቆፍቱ ጎራ አካባቢ በብዛት ይገኛል፡፡ በእዚህ አካባቢ 2 የመስኖ እርሻ ቦታዎችን ያገኘን ሲሆን አንደኛው ቁምዱ አካባቢ 60 ሰዎች ተደራጅተው የያዙት (ለበቆሎ ምርት) ሲሆን ሌላው ሌንጮ ዋጮ (ቡርቃው ወይም ምንጩ) አካባቢ ከረጅም ጊዜ በፊት ተይዞ ለአትክልት (በዋናነትት ሽንኮራ አገዳ እና ሙዝ) እየዋለ ያለ ቦታ ነው፡፡

- ቀጥሎ ከቀበሌ 013 እና 014 ድንበር አጨሳ ወንዝ በመነሳት ከዚያም የደገር-ወረሞ የመኪና መስመር በመከትልና በማቋረጥ ከዚያም ከብት መጠያንና የለቡን አካባቢ በማለፍ እስከ ቀበሌ 014 እና 017 ድንበር መረቁ/ፍልፍል/ለቡ ወንዝ ደርስ ያለውን የደን ሽፋን ተመልክተናል፡፡ በእርግጥ 014 ቀበሌ በኩል የአጨሳን ወንዝ ተከትሎ የእጣን ዛፍ ያለበት ሰፊ ደን አይተናል፡፡ ሽፋኑም 013 ቀበሌ ካሉት የደን ቦታዎች የተሻለ ነው፡፡ የደገርና ሚዳ-አሮሞን የሚያገናኘው መንገድ የሚገነባውም በዚሁ አካባቢ ነው፡፡ የከብት መጠያ አካባቢ በፊት ታርሶ ነበር፡፡ አሁን ግን በቀበሌው በደን ቦታነት ተከልሎ እየተጠበቀ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጅ ደኑ ቀደም ሲል በደረሰበት የእርሻ ተፅዕኖ ሽፋኑ የሳሳ (sparsed Farm Trees) እንደሆነ አስተውለናል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የሚገኘው የለቡ አካባቢም የበለጠ በእርሻ ምክንያት የተጎዳ መሆኑን ተመልክተናል /x=492928 y= 1144199/፡፡
- በመጨረሻም ከቀበሌ 014 እና 017 ድንበር መረቁ ወንዝ በመነሳት የቱሉ ጅሌን (ለቡ) ደን በማለፍ ከዚያም በቶ እርሻ ልማት አክስዮን የእርሻ ቦታን በማየት ከዚያም የ017 እና 019 ቀበሌ ድንበር የጠቀኖ/ጀጀባና ልጮ/ ወንዝ በማቋረጥ ከዚያም በቀበሌ 019 ውስጥ የሚገኘውን የአገዩና ሚራቱ ደን አቋርጠን እስከ ቀበሌ 019 እና 020 ድንበር ጎፎ ወንዝ ድረስ ያለውን የደን ሽፋን ተመልክተናል፡፡ በዚህ መስመር ካየናቸው የደን ቦታዎች ሁሉ የቱሉ ጅሌ ደን በዋናነት ቀጥሎ የአገዩና ሚራቱ ደን የተሻለ ሽፋንና ተስፋ ያላቸው ሲሆን ከቀበሌ 020 ደን ጋር በማገናኘት በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ ማካተት ይቻላል፡፡ ያለው የዱር እንስሳት ሃብትም ከፍተኛ እንደሆነ ካገኘው የድኩላ፣ የሚዳቋ፣ የሰሳ በጠጥ መረዳት ችለናል፡፡ አካባቢው ጥሩ የመመልከቻ ቦታም ሆኖ ሊያገለግል እንደሚችል አይተናል /x=490328 y= 1146501/፡፡ ይሁን እንጅ በእነዚህ የደን ቦታዎች ከፍተኛ የሆነ የደን ጭፍጨፋና ህገወጥ የእርሻ መስፋፋት አስተውለናል፡፡ ከፍተኛ የሆነ የመሬት ሽሚያ ያለ መሆኑን አስተውለናል፡፡ አዲስ ቃጠሎ፣ ሲያርሱና ሲዘሩ ተመልክተናል፡፡ የሚያርሱትም አብዛኞቹ ከሌላ ቀበሌ የመጡ ሰዎች (ግማሽ፣ ሲሶና እርቦ ለማግኘት) ናቸው፡፡ ስለሆነም 017 እና 020 ቀበሌን ለማገናኘት ቀበሌ 019 ላይ ያለውን ከፍተኛ ደን ጭፍጨፋ እና የእርሻ መስፋፋት ማሰቆም የግድ ይላል፡፡ በአጠቃላይ ደኑ በአዳጋ ላይ ነው ያለው /x=488865 y= 1147034/፡፡

ከላይ በተገለፀው ቅደም ተከተል መሠረት ከፍተኛ የዱር እንስሳት መኖሪያ የሆኑና ለቅኝት የሚያመቹ 6 ያህል የጉዞ መሰመሮችን በመጠቀም የወለቃ፣ አባይና በቶ ሸለቆ ታሳቢ ጥበቅ ስፍራ ዝርዝር ጥናት ተካሂዶ በቀጣይ ለሚሰራው የክለላ ስራ አስፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

የጥናት ቡድኑ ከክልል ባህል፣ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ 3 ባለሙያዎችን፣ ከዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ 1 ባለሙያ፣ ከቦረና ወረዳ 2 ባለሙያዎችን፣ ከወግዲ ወረዳ 3 ባለሙያዎችን፣ ከከላላ ወረዳ 2 ባለሙያዎችን፣ ከሶስቱም ወረዳዎች 4 ፖሊሶችንና 3 ሚሊሻዎችን፣ 2 መንገድ መሪ እና ዕቃ ጫኝ ያካተተ ነበር፡፡ በአጠቃላይ በዝርዝር ጥናቱ ወቅት ወደ 245 ኪ.ሜ ርቀት በእግር ጉዞ ተሸፍኗል፡፡



ምስል 3. በወግዲ ወረዳ ቀበሌ 017 የሚገኘው የደድሃራ የውሃ ዳር ደን (Riverine Vegetation) እና በቀበሌ 015 የሚገኘው አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ (*Acacia-Boswellia-Commiphora* ecosystem) ስርዓተ ምህዳር

8. ከዝርዝር ጥናቱ የተገኙ ውጤቶች

8.1. የበቶ፣ ወለቃና አባይ ሸለቆዎች ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ ዝርዝር የተፈጥሮ ሃብት ሁኔታ ትንተና

የስርዓተ ምህዳር ሁኔታ

የተፈጥሮ ደኑ በዋናነት አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ ስርዓተ ምህዳርን (*Acacia-Boswellia-Commiphora* Ecosystem) የሚወክል ቢሆንም ቆላማና ሜዳማ የሆኑ የበቶ፣ የወለቃና አባይ ወንዞችን ተከትለው የሚገኙ የውሃ ዳር ደኖችን (Riverine Vegetation) የሚወክል ስነ ምህዳር የያዘ የተፈጥሮ ደን ማዕከል ነው፡፡

አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ (*Acacia-Boswellia-Commiphora* Ecosystem) ስርዓተ ምህዳርን የሚወክለው አካባቢ የሚገኘው በከላላ ወረዳ ቀበሌ 017፣ 019 እና 020፣ በወግዲ ወረዳ ቀበሌ 03፣ 07፣ 08፣ 09፣ 013፣ 015፣ 016፣ 017፣ 018፣ 026 እና 034 እና በቦረና ወረዳ ቀበሌ 024 ወጣገባማና ተራራማ በሆኑት ቦታዎች ውስጥ ነው፡፡ የውሃ ዳር ደኖችን (Riverine Vegetation) የሚወክለው ስነ ምህዳር ግን የሚገኘው ከሶማ በረሃ ከጨዬ እና አባይ ወንዞች መጋጠሚ ጀምሮ የአባይ፣ ወለቃና በቶ ወንዞችን ተከትሎ እስከ ከለላ ወረዳ ቀበሌ 017 መረቆ እና በቶ ወንዝ መገናኛ ድረስ ይዘልቃል፡፡ ወንዞችን እና ተራራማ ቦታዎችን ተከትለው ከሚገኙ የደን አካባቢዎች መካከልም አጋማይት፣ አቡ ጠንጠቃ፣ ደድሃሬ፣ ጠማሜ፣ መጋጠሚያ፣ ሰንበቶ፣ ዲዳ ዋጮ፣ ቀዋ ዳባ፣ ጥቁር እንጨት፣ ወልጊሃ፣ ቡልቡል፣ አገዩና ሚራቱ እና ቱሉ ጅሌ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡



ምስል 4. በከላላ ወረዳ በቀበሌ 017፣ 019 እና 020 የሚገኙ የተፈጥሮ ደኖች

ይሁን እንጅ የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ በወግዲ ወረዳ የወለቃ እና አባይ ወንዝን ተከትሎ በ1991 ዓ.ም **የኦፕን ውድላንድ ኤንድ ሽራብ ላንድ** (Open Woodland and Shrub Land) **ቅሪት ደን** (Remnant Vegetation) **እንደሆነ አስቀምጠው ነበር። በ**1993 ዓ.ም **አቶ ጫኔ ገበየሁ ለሁለተኛ ድግሪ ማሞያ በወግዲ ወረዳ የወለቃና አባይ ወንዝ ተከትሎ በ**4 **ቀበሌዎች ላይ** (016፣ 017፣ 018 **እና** 026) **ባደረጉት ጥናት የተፈጥሮ ደኑ የዕፅዋት ሽፋንና ስርጭት** (Vegetation Cover and Distribution) **የአፈር ዓይነት** (soil type)፣ **የከፍታ መጠን** (Elevation) **እና የቶፖግራፊ ልዩነትን** (Topographic Gradient) **መሰረት አድርጎ እንደሚለያይ ሪፖርት አድረገዋል። በዚህ መሰረትም የበቶ፣ ወለቃና አባይ ወንዞችን ተከትሎ የውሃ ዳር ደኖችን** (Riverine Vegetation) **የሚወክል ስነ ምህዳር የያዘ የተፈጥሮ ደን (ጥቁር እንጨት፣ ዋርካ፣ ሰምቦ፣ ችብሃ፣ ኮመር፣ እሸ፣ ዶቅማ፣ ቋራ፣ ሾላ፣ በደኖ እና አሏሬ)፣ ቀጥሎ ኮረብታዎችን ተከትሎ** (Hills of River Banks) **አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ** (*Acacia-Boswellia-Commiphora* Ecosystem) **ስርዓተ ምህዳርን (የግራር፣ የእጣን ዛፍ፣ አንቋ፣ ሰፋ፣ ጋሻ፣ ስምንት ልብ፣ የቆላ ዋንዛ ዝርያዎች) የያዘው ደን በዋናነት ይገኛል። ከዚያም በሸለቀው ከፍተኛ ቦታዎች አደር፣ ደሬ፣ ቆንጥር፣ ጠደቻ፣ አባሎ፣ ዋጫ ግራር እና ችፈሬ በብዛት የሚገኙበት ሽረብ ላንድስ** (Shrub Lands) **ይገኛል።**

በተለይ የበቶ፣ የወለቃና አባይ ወንዞች ሜዳማ አካባቢዎችን ተከትለው የሚገኙት እነዚህ ደኖች በውስጣቸው እጅግ በጣም ግዙፍና ዕድሜ ጠገብ የሆኑ ዛፎችን አቅፈው የያዙ ናቸው። ይህ ደን ምናልባትም በክልላችን የአባይ ሸለቆ በሚገኝባቸው በየትኛውም አካባቢዎች ጨርሰው የጠፉ ወይም የሌሉ ቅሪት ደኖችን የያዘ የተለየና ማራኪ ስፍራ ነው።



ምስል 5. በወግዲ ወረዳ በቀበሌ 015፣ 016 እና ወለቃ ወንዝ መካከል የሚገኙ የተፈጥሮ ደኖች

እነዚህ የደን ቦታዎች በጣም ሜዳማ፣ በዚህ ዓይነት፣ ቁመትና ውፍረት የትም ቦታ የማያገኙ ዛፎችን አቅፈው የሚገኙ ቢሆንም ሜዳማና ለመስኖ እርሻ አመቺ በመሆናቸው የተነሳ ለእርሻ ኢንቨስትመንት እንዲውሉ ለማድረግ ለኢንቨስተሮች እና ለወጣቶች ለመስጠት በመታሰቡ ከፍተኛ ችግር ያሉ

መሆናቸውን ተረድተናል። በአጠቃላይ ይህ የተፈጥሮ ደን በውስጡ በሀገራችን በማንኛውም ቦታ እንደልብ የማይገኙና ለመጥፋት የተቃረቡ እንደ ጥቁር እንጨት፣ የቆላ ዋንዛ፣ ኮመር፣ የእጣን ዛፍ፣ ዛና፣ በደኖ፣ ዳርሌ፣ አባሎ፣ ዋርካና ባምባ ያሉ ዕፅዋቶችን የያዘ ስለሆነና አነዚህን ዕፅዋቶች ለዘቦታ ጥበቃ(In-situ Conservation) ተፈጥሮዊ ቦታ በመሆኑ ጥብቅ ስፍራ ሊሆን እንደሚገባው ያመላክታል።


የዱር እንስሳት

በአጠቃላይ የመካከለኛው የአባይ ወንዝ ተፋሰስ ሽለቆዎች የተፈጥሮ ደኖች ውስጥ ያለው የብዝሃ ህይወት ሃብት ቦታው አመቺ ባለመሆኑ የተነሳ በዝርዝር እንዳልተጠናና እንደማይታወቅ ያሉ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይሁን እንጅ በዚህ የዳሰሳ ጥናት በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ከ25 በላይ ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት፣ ከ92 በላይ አዕዋፋት፣ 3 የዓሳ፣ 4 የተሣቢና ተራማጅ ዝርያዎች እንዳሉ ለማረጋገጥ ተችሏል። ከእነዚህም ውስጥ በአሁኑ ሰዓት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚታወቁት ነብር፣ ተራ ቀበሮ፣ አነር፣ የደልጋ አንበሳ፣ መጎዛ፣ ሽልምልም ጅም፣ ተራ ጅብ፣ ጃርት፣ ሚዳቋ፣ ሰሳ፣ ጉሬዛ፣ ተራ ዝንጅሮ፣ ሽክኮ፣ ከርከሮ፣ የዱር ዓሳማ፣ ተራ ጥንቸልና ተራ ድኩላ ጥቂቶቹ ናቸው።

በተጨማሪም እንደ

- ዝግራ (Vulturine guineafowl)፣
- የሶረኔ ቆቅ (Harwood's Francolin)፣
- ርኩም (Abyssinian ground hornbill)፣
- ክንፈ ጥቁር በቀቀን (Abyssinian Black-winged Lovebird)
- ዳክዬ (Egyptian goose)፣ African fish eagle (ንስር አሞራ)
- ገዴ (Augur buzzard)፣ ወዘተ የመሳሰሉ አዕዋፋት በተፈጥሮ ደኑ ውስጥ ይገኛሉ።

ከዚህ ሌላ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳትና የተፈጥሮ ታሪክ ማህበር (Ethiopian Wildlife and Natural History Society) እና በርድ ላይፍ ኢንተርናሽናል (Bird Life International) በሀገር አቀፍ ደረጃ በመካከለኛው ኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎች እንደሚክ ቢርድ ኤርያስ (Central Ethiopian Highlands Endemic Bird Areas) ክልል ውስጥ ከሚገኙ 4 የአዕዋፍት ዝርያዎች ሁሉም በሀገራችን ብቻ እንደሚገኙና ከእነዚህ ውስጥ 2 የአዕዋፍት ዝርያዎች በክልላችን በደቡብ ወሎ እና ሰሜን ሸዋ ዞን ውስጥ በጀማ እና ጃራ ሽለቆዎች እንዲሁም በመካከለኛው የአባይ ወንዝ ተፋሰስ ሽለቆዎች የተፈጥሮ ደኖች ውስጥ ተጠልለው እንደሚኖሩ አስቀምጠዋል።



ምስል 6. የበቲ፣ ወለቃና አባይ ወንዞችን ተከትለው ከሚገኙ ዕፅዋት መካከል በከፊል

በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ደረጃ በሱዳን ጉይንያ ሳቫና ባዮም (Sudan-Guinea Savanna

Biome) ክልል ውስጥ ከሚገኙ የአዕዋፍት ዝርያዎች ውስጥ 16 ያህሉ በሀገራችን እንደሚገኙና ከእነዚህ ውስጥ 6 የአዕዋፍት ዝርያዎች በጀማ እና ጃራ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደኖች ተጠልለው እንደሚኖሩ አስቀምጠዋል። እንዲሁም በአፍሮ ትሮፒካል ሃይላድ ባዮም (Afrotropical Highland Biome) ክልል ውስጥ ከሚገኙ የአዕዋፍት ዝርያዎች ውስጥ 49 ያህሉ በሀገራችን እንደሚገኙና ከእነዚህ ውስጥ 14 የአዕዋፍት ዝርያዎች በደን ክልሉ ተጠልለው እንደሚኖሩ አስቀምጠዋል። እነዚህ ወንዞች ደግሞ የአባይ ወንዝ ገባሮች ናቸው። በተጨማሪም በኢትዮጵያ የዱር እንስሳትና የተፈጥሮ ታሪክ ማህበር (Ethiopian Wildlife and Natural History Society) እና በበርድ ላይፍ ኢንተርናሽናል (Bird Life International) ሪፖርት ያልተደረጉ በአፍሮ ትሮፒካል ሃይላድ ባዮም (Afrotropical Highland Biome) ክልል ውስጥ የሚገኙ 3 የአዕዋፍት ዝርያዎችን አግኝተናል። በአጠቃላይ በዚህ ክልል ከሚገኙ 49 የአእዋፍት ዝርያዎች ውስጥ 17 የአዕዋፍት ዝርያዎች በደን ክልሉ ተጠልለው ይኖራሉ።



ምስል 7. በተሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ውስጥ በመስክ የታዩ የዱር እንስሳት ዝርያዎች

ስለሆነም በውል ባይጠናም የኢትዮጵያ የዱር እንስሳትና የተፈጥሮ ታሪክ ማህበር (Ethiopian Wildlife and Natural History Society) እና በርድ ላይፍ ኢንተርናሽናል (Bird Life International) በተመሳሳይ ሁኔታ የመካከለኛው የአባይ ወንዝ ተፋሰስ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደኖች ለሱዳን ጉይንያ ሳቫና ባዮም እና ለአፍሮ ትሮፒካል ሃይላድ ባዮም ክልል የአዕዋፍት ዝርያዎች ተፈጥሮዊ ቦታ ሊሆኑ እንደሚችሉ አሰቀምጠዋል።

ከዚህ ሌላ ቀደም ሲል የተደረጉ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳትና የተፈጥሮ ታሪክ ማህበር (Ethiopian Wildlife and Natural History Society) እና በርድ ላይፍ ኢንተርናሽናል (Bird Life International) ጥናቶች ባያረጋግጡልንም በሶማሌ ማሳይ ባዮም (Somali-Masai Biome) ክልል ውስጥ ከሚገኙ የአዕዋፍት ዝርያዎች ውስጥ 98 ያህሉ በሀገራችን እንደሚገኙና ከእነዚህ ውስጥ 2 የአዕዋፍት ዝርያዎች በደን ክልሉ ተጠልለው እንደሚኖሩ ጥናታችን ያሳያል።

ስለዚህ እነዘህ የአዕዋፍት ዝርያዎች ከአፍሮ ትሮፒካል ሃይላድ ባዮም (Afrotropical Highland Biome)፣ ከሱዳን ጉይንያ ሳቫና ባዮም (Sudan-Guinea Savanna Biome) እና ከሶማሌ ማሳይ ባዮም (Somali-Masai Biome) ክልል ውጭ በሌላ ባዮም (Biome) የማይገኙ በመሆኑ የተፈጥሮ ደኑ ከአእዋፍት ጥበቃ አንፃር ጥብቅ ስፍራ መሆን እንዳለበት ያመላክታል።

በዚህ መሰረትም ከአዕዋፍት ጥበቃ አንፃር ታሳቢ ጥብቅ ስፍራውና አካባቢው በአይ ቢ ኤ መስፈርት (IBA Criteria) **መሰረት ኤ ደረጃ** 2 **እና ኤ ደረጃ** 3 (A2 and A3)[1] **እንደሚያሟላ ታውቋል፡፡**

በተጨማሪም እነዘህ በሀገራችን ብቻ የሚገኙ 3 **የአዕዋፍት ዝርያዎች፡**

- ☞ **የሶረኔ ቆቅ** (Harwood's Francolin)፣
- ☞ **ሩፔልስ ቻት** (Rupell's chat)
- ☞ **ብላክ ሄድድ ፎሬስት ኦሪዮል** (Black-headed Oriole)
- ☞ **ክንፈ ጥቁር በቀቀን** (Abyssinian Black-winged Lovebird) **በኢትዮጵያና ኤርትራ ብቻ የሚገኝ**

ከሌሎች አካባቢዎች በተሻለ ሁኔታ ዋነኛ ተፈጥሮዊ መኖሪያቸው በመሆኑ የተፈጥሮ የደን ክልሉ ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም እንዳለው ያመላክታል፡፡ ስለሆነም ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በዱር እንስሳት ሃብት ክምችቱ እና IUCN **ለጥብቅ ስፍራዎች ማቋቋሚያ ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች** (Criteria for Protected Areas) **በቀጥታ የሚያሟላ በመሆኑ ጥብቅ ስፍራ ሆኖ እንዲከለልና እንዲጠበቅ ያስችለዋል፡፡**



ምስል 8. በወግዲ ወረዳ በቀበሌ 018፣ 026 **እና** 034 **እና በቦረና ወረዳ በቀበሌ** 024 **ውስጥ በጣቀት፣ የሹም እና አባይ ወንዞች መካከል የሚገኝ የተፈጥሮ ደን**

የዕፅዋት ሽፋንና ዓይነት

የበቶ፣ ወለቃና አባይ ሸለቆ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ በተፈጥሮ የበቀሉ ከቁጥቋጦ ጀምሮ እስከ ትላልቅና ዕድሜ ጠገብ ዛፎች ድረስ ከ85 **በላይ የሚሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎችን የያዘ የተፈጥሮ ደን ነው፡፡ የአባይና ወለቃ ወንዞችን ተከትሎ የሚገኘው ደን በአብዛኛው በረጃጅም፣ ዕደሜ ጠገብና ግዙፍ በሆኑ የዋርካ ዝርያ፣ የጥቁር እንጨት፣ ዋርካ፣ ሰምቦ፣ ችብሃ፣ ኮመር፣ እሸ፣ ዶቅማ፣ ቋራ፣ ሾላ፣ በደኖ እና አሏሬ ዛፎች የተሸፈነ ነው፡፡ ወጣ ገባና ተራራማ ቦታዎችን ተከትሎ ግን አንቃ፣ ዳርሌ፣ ደፊ፣ ዋጫና ነጭ ግራር፣ የእጣን ዛፍ፣ አደር፣ አባሎ፣ የመሳሰሉ ዕፅዋት ይገኛሉ፡፡**

1 A1= Globally threatened species, A2= Restricted-range/ Endemic species, A3= Biome-Restricted species (Global IBA Criteria).

ስለዚህ ይህ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ በየትኛውም ቦታ እንደልብ የማይገኙና ለመጥፋት የተቃረቡና መጠበቅ የሚገባቸው እንደ ጥቁር እንጨት፣ የቆላ ዋንዛ፣ ኮመር፣ የጣን ዛፍ፣ ላሎ፣ ዋርካና ባምባ ያሉ ዛፎች ለዘቦታ ጥበቃ /In-situ conservation/ አገልግሎት ሊውል የሚችል ቦታ ስለሆነ ጥብቅ ስፍራ ሊሆን የሚገባው ስፍራ ነው።

በተለይም በአማራ ክልል በተመሣሣይ ስርዓተ ምህዳር የዚህ ዓይነት የዕፅዋትና የደን ስብጥር በዚህ ሁኔታ ማግኘት አስቸጋሪ ነው።

8.2. የሶሽዮ ኢኮኖሚ ሁነቶች

የበቶ፣ ወለቃና አባይ ሸለቆ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ቆላማና ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማቶች በማይገኙባቸው የቦረና፣ የወግዲና ከለላ ወረዳ 15 ቀበሌዎች ውስጥ የሚገኝ ነው። የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ድንበር ክለላ ገና ያልተከናወነ የወደፊት ቀሪ ስራ ነው። በዚህ ምክንያት በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ውስጥና ደጀን አካባቢ ያለውን ማህበረ ኢኮኖሚ ለየብቻ ለመዳሰስ ባይቻልም ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ከሌሎች ተመሳሳይ የተፈጥሮ ቦታዎችጋር ሲነፃፀር አነስተኛ የሰው እንቅስቃሴና ንክኪ ያለበት ነው።

ይሁን እንጂ አሁን ባለው ተጨባጭ እውነታ የተፈጥሮ ኃብቱ ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም በድንበሩ ዙሪያ ቀበሌዎች ከሚኖረው ህዝብ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው። በዚህ ረገድ የጥናት ቡድኑ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎችን በማጠናቀር የተፈጥሮ ደኑ ከሚገኝባቸው ከላይ ከተገለፁት 15 ቀበሌዎች በተጨማሪ የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ አዋሳኝ የሆኑ በምስራቅ ጎጃም እና ሰሜን ሸዋ ዞኖች እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል 12 ቀበሌዎችን ለይቷል። ይህም ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ በአጠቃላይ በ29 ቀበሌ በሚኖሩ ህዝቦች መካከል እንደሚገኝ ያሳየናል።

በ2002 ዓ.ም በአገራቀፍ ደረጃ በተካሄደው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ መሰረት በ27ቱ ቀበሌዎች በ27,601 ቤተሰቦች ስር 58,802 ወንድና 59,054 ሴቶች (በድምሩ117,856 ሰዎች) ይኖራሉ። በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ዙሪያ ባሉ ወረዳዎችና ቀበሌዎች የሚኖረው ቤተሰብ እና ነዋሪ በየታ ተለይቶ በዕዝል 4 ላይ ተቀምጧል። በዚህ መረጃ መሰረት በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ዙሪያ ከሚኖረው ቤተሰብና ህዝብ 54 በመቶው የሚኖረው ተፈጥሮ ደኑ በሚገኝባቸው የደቡብ ወሎ 3 ወረዳዎች ውስጥ ነው። በዚህ ላይ በወግዲ፣ ከለላና ቦረና ወረዳ የሚኖረው ህዝብ ድርሻ እንደ ቅደም ተከተል አቀማመጣቸው 38.19፣11.51 እና 3.98 በመቶ ነው።

በሰንጠረዥ 1 ላይ የተቀመጠው መረጃ እንደሚያሳየው በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ዙሪያ ከሚኖረው ቤተሰብና ህዝብ 17.2 በመቶ የሚሆነው በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ስር ባሉ የደራ ወረዳ 3 ቀበሌዎች ይኖራሉ። ይህ መረጃ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩን ለመጠበቅና ለማልማት ወደፊት በሚደረጉ ጥረቶች ውስጥ ጎረቤት በሆነው የኦሮሚያ ክልል ደራ ወረዳ የሚገኘው የ3 ቀበሌ ህዝብ ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑን በግልጽ የሚያመለክት ነው።

ሰንጠረዥ 1. በበቶ፣ በወለቃና አባይ ሸለቆ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ድንበር ዙሪያ የሚኖረው ህዝብ ብዛት፣ በ2002 የህዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት፣

ተቁ	ዞንና ወረዳ	የቀበሌዎች ብዛት	የቤተሰብና ህዝብ ብዛት፣			
			የቤተሰብ ብዛት	%	የህዝብ ብዛት፣	%
1.	ደቡብ ወሎ ዞን					
1.1.	ወግዲ ወረዳ	11	10,629	38.51	45,008	38.19
1.2.	ከለላ ወረዳ	3	3177	11.51	13567	11.51
1.3.	ቦረና ወረዳ	1	1,065	3.86	4,693	3.98
	ድምር	15	14,871	53.88	63,268	53.68
2.	ምስራቅ ጎጃም ዞን					
2.1.	እነብሴ ሳር ምድር	1	679	2.46	2,880	2.44
2.2.	እናርጅ እናውጋ	1	783	2.84	3,397	2.88
2.3.	ሸበል በረንታ	4	2,944	10.67	12,741	10.81
	ድምር	6	4406	15.96	19018	16.14
3.	ሰሜን ሸዋ ዞን					
3.1.	ሚዳ ኦሮሞ	3	3,577	12.96	15,213	12.91
	ድምር	3	3577	12.96	15213	12.91
4.	ኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን					
4.1.	ደራ ወረዳ	3	4,747	17.2	20,357	17.27
	ድምር	3	4,747	17.2	20,357	17.27
	ጠቅላላ ድምር	27	27,601	100	117,856	100

የመረጃ ምንጭ፡ በአባሪ ላይ በተቀመጠው መረጃ መሰረት የተጠናቀረ

የአካባቢው ማህበረ ኢኮኖሚ

ከነዋሪው ህዝብ ጋር የአካባቢው ማህበረ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች፣ ለጥብቅ ቦታ አላማዎች ስኬት ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው። ከእነዚህ የጥናት ውጤቶች እና በአገራችን ካሉ ተመሳሳይ ቦታዎች ልምድ የሚያስገነዝቡን በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ዙሪያ ያለውን ማህበረ ኢኮኖሚን በአግባቡ መዳሰስ በፓርኩ ህልውና ላይ የተረጋገጡ ችግሮችን ከወዲሁ በተደራጁ የልማት እቅዶች ለማስወገድ እንደሚያግዝ ነው።

በዚሁ መሠረት የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩን ሁነት ስንመለከት በጅምር ላይ ከሚገኙ 3 የግል ኢንቨስትመንቶች ውጭ የአካባቢው ማህበረ ኢኮኖሚ በአነስተኛ የሰብል አዝመራና የቤት እንስሳት እርባታ ላይ የተመሰረተ ጥምር ግብርና መሆኑ ጎልቶ ይታያል። በግል ባለሀብቶች ከተጀመሩ 3 የግብርና ኢንቨስትመንቶች ውስጥ በአሁኑ ወቅት ውስን እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ የሚታየው የበቶ አክስዮን ማህበር ነው። ይህ አክስዮን በ1996 ዓ.ም በከለላ ወረዳ በአዲስ አምባ ቀበሌ ውስጥ በተሰጠው 91 ሄክታር (በልኬት ግን ከ420 ሄ/ር በላይ) መሬት ላይ ሰሊጥ በቆሎና ማሽላ

በማምረት ለገበያ ያቀርባል፡፡ ኢንቨስትመንቱ ለአካባቢው ማህበረ ኢኮኖሚ 5 ቋሚና 400 ጊዜያዊ የስራ እድሎችን እንደፈጠረ ከወረዳው ንግድና ኢንደስትሪ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

ሰንጠረዥ 2፡ በበቶ፣ ወለቃ እና አባይ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ አካባቢዎች የሚገኘው የግል ኢንቨስትመንት፣

ተ.ቁ		የኢንቨስትመንቱ		ፈቃድ ያገኘበት ዓ.ም
		የስራ ዘርፍ	ካፒታል	
1.	በቶ አክስዮን ማህበር	ሰብል ልማት	200,000	1996
2.	አቶ ይርጋ ተቀባ	ንብ እርባታ	75,000	2001
3.	ገዛኸኝ ኃይሉ	እጣን ምርት		2004

በወግዲና ቦረና ወረዳዎች የተመዘገቡ የእጣን እና ከብት እርባታ ኢንቨስትመንቶች በአካባቢው ውስጥ ያላቸውን የስራ እንቅስቃሴን ማየት ግን አልተቻለም፡፡ በተለይ፣ ከታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ የመጀመሪያ ደረጃ ጥናት ውጤት በኃላ፣ በወግዲ ወረዳ እጣን ለማምረት ባገኘው ቦታና ፈቃድ ስራ የጀመረው የአቶ ገዛኸኝ ኃይሉ አንቨስትመንት በምርት (በአቶ ጫኔ ገበየሁ ጥናት መሰረት 3462 ሄ/ር ይሆናል)፣ በስራ እድል፣ በቴክኖሎጂ ሽግግርና ወዘተ ጥቅሞችን ለማህበረ ኢኮኖሚው በመፍጠር ረገድ ያለውን አስተዋፅዖ የሚያሳይ ምንም አይነት የመስክና ሁለተኛ ደረጃ መረጃ አልተገኘም፡፡

በመሆኑም የአካባቢው ነዋሪ የምግብ ፍጆታውን ለማሟላት እና ለሌሎች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች የሚያስፈልገውን ወጪ የሚሸፍነው ከሰብል እርሻና ከቤት እንስሳት እርባታ ነው፡፡ በዚህ በኩል በመስክ ከታየው እውነታ ጋር ከወግዲ፣ ከለላና የቦረና ወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች ተሰብስበው በዕዝል 5 እና 6 ላይ የተቀመጡ መረጃዎች ለዚህ መልካም የሚባሉ ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡

ለአብነት በታሳቢ ፓርኩ 15 ቀበሌ ነዋሪ በ2003/04 የምርት ዘመን ከታረሰ 22,557 ሄክታር መሬት ላይ 478,714 ኩንታል ሰብል አምርቷል፡፡ በቤተሰብ ደረጃ በአማካኝ ባለው 1.5 ሄ/ር የእርሻ መሬት ላይ የሚመረተው በነዋሪው የአመጋገብ ስርአት ውስጥ ተመራጭ የሆኑ የሰብል አይነቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም አካባቢው በዚህ የእርሻ ዘመን በጠቅላላ ካመረተው ሰብል ውስጥ 41 % ማሽላ ነው፡፡

ከጠቅላላው የሰብል ምርት 18.9፣ 15.4 እና 12 በመቶ የሚሸፍነውን በቅደም ተከተል በቆሎ፣ ጤፍ እና ስንዴ በማምረት ይጠቀማል፡፡ በአንፃሩ ኑግ እና ተልባን የመሳሰሉ የቅባት እህሎች ምርት እጅግ በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ይህም በአካባቢው የእርሻ ስራ ውስጥ አትክልትና ፍራፍሬን ጨምሮ የገቢ ማስገኛ ተክሎች ምርት በአካባቢው ገና ያልተስፋፋ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

ሰንጠረዥ 3. የበቶ፣ ወለቃ እና አባይ ሸለቆ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ በሚገኝባቸው ቀበሌዎች በ2003/04 የምርት ዘመን የተመረቱ ሰብል በኩንታል፣

የሰብሉ አይነት	የተገኘ ምርት	
	በኩንታል	%
ማሽላ	197,454.00	41.25
በቆሎ	90,449.00	18.89
ጤፍ	73,812.00	15.42
ስንዴ	57,504.00	12.01
ገንያ	20,422.00	4.27
ሽንብራ	17,495.00	3.65
በሎቄ	16,235.00	3.39
ኑግ	3,728.00	0.78
ተልባ	641	0.13
ገብስ	330	0.07
ባቄላ	322	0.07
አተር	322	0.07
ድምር	478,714.00	100.00

ይሁን እንጂ ለዚህ ማህበረ ኢኮኖሚ የቤት እንስሳት ኃብት ከሚያስገኘው ተጨማሪ ገቢ በላይ ለአካባቢው የኃብትና ክብር መገለጫ ሆኖ በማገልገል ላይ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት፣ የአካባቢው ነዋሪ ኃብቱን በመኖሪያ መንደሩና በዙሪያው በሚገኙ ወንዞች ውስጥ በሚያሰራቸው ጊዜያዊ የደረባ በረቶች የቤት እንስሳቶችን በብዛት (በአንፃራዊነት) አርብቶ የመጠቀም ልምድ አለው፡፡

ምንም እንኳን፣ የቦታ ስርጭትና ብዛት መጠን ገላጭ የሆነ መረጃ ለማግኘት ባይቻልም፣ የጥናት ቡድኑ የወግዲ፣ ከለላና ደራ ወረዳ ነዋሪዎች ንብረት የሆኑ ከ54 በላይ ደረባ ቤቶችን በተፈጥሮ ደኑ ውስጥ ለመመልከት ችሏል፡፡ ከደረባው ጠባቂዎችና ከተለያዩ የአካባቢው ሰዎች ጋር የተደረጉ መደበኛ ያልሆኑ ውይይቶች በአንድ አካባቢ የ7 አባዎራዎች ከ266-378 የሚሆኑ ከብቶችን ማስተናገድ የሚችሉ የደረባ ቤቶችን ማግኘት እንደሚቻል ያመለክታል፡፡

ከዚህ ጋር ከወግዲ፣ ከለላና ቦረና ወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች በተሰበሰበ መረጃ ነዋሪው በዙሪያው ባለ የወንዝ ውኃና የተፈጥሮ ዕፅዋት ተጠቅሞ በብዛት የሚያረባቸውን የቤት እንስሳት የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ በ15 ቀበሌዎች በንብ መንጋ ከተሞሉ 6057 ባህላዊ፣ 403 የሽግግርና 72 ዘመናዊ ቀፎዎች በተጨማሪ፣ በቁጥር 122,797 የቤት እንስሳት (ዶሮን ሳይጨምር) ይገኛሉ (ዝርዝሩ ዕዝል 5 ላይ ተቀምጧል)፡፡

ሰንጠረዥ 4. የበቶ፣ ወለቃ እና አባይ ሸለቆ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ በሚገኝባቸው የወግዲ፣ ከለላና ቦረና ወረዳ 15 ቀበሌዎች የሚገኘው የቤት እንስሳት ኃብት በቁጥርና አይነት፣

ተቁ	ዝርዝር	የቤት እንስሳት ብዛት	
		በቁጥር	%
1	ላም	20,800.00	0.17
2	በሬ	22,126.00	0.18
3	ጊደርና	7,392.00	0.06
4	ወይፈን	9,637.00	0.08
5	ጥጃ	7,927.00	0.06
6	በግ	5,618.00	0.05
7	ፍየል	40,254.00	0.33
8	ፈረስ	15	0.00
9	በቅሎ	227	0.00
10	አህያ	8,801.00	0.07
	ድምር	122,797.00	100

በሌላ በኩልም የቤት እንስሳት ሀብት ክምችት በዝርያ አይነቶች ተለያይቶ ሲታይ ነዋሪው የዳልጋ ከብትና ፍየሎችን ማርባት ቀዳሚ ምርጫው መሆኑ ይታያል። ሁለቱ ዝርያዎች ከጠቅላላው የቤት እንስሳት 53 እና 33.7 በመቶ የሚሆነውን ብዛት ይይዛሉ። ከዚህ ጎን የአካባቢውን ኃብት በየወረዳዎቹ ከሚገኘው የቤት እንስሳት ጋር በማነፃፀር የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ማህበረ ኢኮኖሚ ከተፈጥሮ ኃብቱ ጋር ያለው ግንኙነት በቀላሉ ማየት ይቻላል። ለአብነት በወግዲና ከለላ ወረዳ ከሚገኘው የንብ ቀፎ፣ የዳልጋ ከብትና ፍየሎች ከ57 % በላይ የሚገኙት ለታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ በታጨ ቀበሌዎች ነው።

በተለይ በአባይ በወለቃና በቶ ወንዞች ውስጥ ያለው የከብት እርባታ፣ በተፈጥሮ ኃብቱ ላይ ከፍተኛ ጫናዎችን እያስከተለ ነው። እነዚህ ጫናዎች እንዳሉ ሆነው ግን ለረጅም አመታት በአካባቢው የተለመደው የከብት እርባታ በዙሪያው ባሉ ኦሮምያ ክልል (ደራ ወረዳ)፣ የደቡብ ወሎና ምስራቅ ጎጃም ዞን ነዋሪዎች እርስ በእርስ ተሳስበውና ተደጋግፈው እንዲኖሩ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል። የወግዲ፣ ከለላና ደራ ወረዳ ነዋሪዎች በሸለቆ ውስጥ የሚገኙ ከብቶችን ከዘራፊዎች ተባብረው ይጠብቃሉ። ይህ ጠንካራ ግንኙነት ወደፊት ለፓርኩ ጥበቃና ልማት ጥሩ መሰረት ሊሆን እንደሚችል ይታመናል።

8.3. የቱሪዝም አቅም

በዚህ ዝርዝር ጥናት ትኩረት የተሰጠው ሌላው አብይ ተግባር፣ የበቶ፣ ወለቃና አባይ ሸለቆ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ በክልሉ የጥብቅ ቦታ አስተዳደር ስርአት ለምቶ ለቱሪዝም ገበያ ለመቅረብ ያለውን

አቅም እና ለዘርፉ ልማት ወደፊት ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋጽኦ መዳሰስ ነው። ለዚህ አላማ ከመስክና በቢሮ የተሰባሰቡ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ፣

1. *ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ በቱሪዝም ገበያ ውስጥ ተፎካክሮ ጎብኚዎችን ለመሳብ ምን አይነት ልዩ መስህባዊ ሀብቶችን አሰባስቧል?*
2. *የዘርፉን ልማት ለማፋጠን ወደፊት ምን አይነት ድርሻ ሊኖረው ይችላል?*

የሚል ጥያቄዎችን መነሻ በማድረግ የተጠናቀሩ ዳሰሳዎች ቀጥለው ቀርበዋል።

ለቱሪዝም ገበያ የመቅረብ አቅሙ

አንድን ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ቅርስ ለአለም አቀፍና ለሀገር ውስጥ የቱሪዝም ገበያ ለማቅረብ ዋነኛው መሰረት በውስጡ አስባስቦ የያዛቸው ድንቃ ድንቅ መስህባዊ ሀብቶች ናቸው። ከዚህ አኳያ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ በአጭር ጊዜ በአገራችን የቱሪዝም ግብይት ውስጥ ቀዳሚ ተጠቃሽ ለመሆን የሚያበቁ በርካታ ልዩ መስህባዊ እሴቶች (Exceptional Values) ያሰባሰበ የተፈጥሮ ቅርስ ነው።

ከነዚህ አቅሞቹ መካከል ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ለቱሪዝም ገበያ የሚያቀርባቸው የአባይ ወንዝና በዙሪያ ያሉ መስህባዊ ሀብቶች በአለም አቀፍ ደረጃ ያላቸው ከፍተኛ እውቅናና አክብሮት አንዱ ተጠቃሽ ነው። በዚህ ረገድ በተለያዩ ጊዜና አጋጣሚዎች በአባይ ሸለቆ ውስጥ ጉብኝታዊ ጉዞ ያደረጉ በርካታ ታዋቂ ሰዎችና የአለም አቀፍ መገናኛ ብዙሀን ባለሙያዎች፣ ከአካባቢው ተፈጥሯዊ ፀጋዎች ጋር በዙሪያ የሚኖረውን ህዝብ ባህላዊ እሴትና እንግዳ ተቀባይነት በሚዳስሱ የህትመትና ተንቀሳቃሽ ፊልም ዘገባዎች በሰፊው እንዲታወቅ አድርገዋል።

ይህ ሰፊና ተደጋጋሚ የመገናኛ ብዙሀን ሽፋን አካባቢው በቱሪዝም ገበያ ውስጥ ለሚኖረው ተፎካካሪነት የመጀመሪያው ጠንካራ መሰረት ነው። በዚህ ልዩ የተፈጥሮ ቦታ የየቢቢሲ (2007)፣ ናሽናል ጆግራፊ (በ1997)፣ የናይል ሚስጢሮች “Mystery of the Nile” (2010) እና የሌሎች አለም አቀፍ ተቋማት ባለሙያዎች በፊልሞቻቸው ያስተጋቡትን ማራኪ የጀልባ ጉዞ የሚወክል መዝናኛ በማልማት የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ጎብኚዎች በበጋ ወቅት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል።

በዚህ የበጋ ወቅት በወንዞቹ ዳርቻ በአሸዋ ደለልና በጠጠር ድንጋዮች ተነጥፈው የሚገኙ ሰፋፊ መሬቶች አካባቢው ለውሀ መዝናኛ ያለውን ምቹነት ይበልጥ የሚያጎሉ ናቸው። በእነዚህ የወንዝ ዳርቻዎች ላይ ለእንግዶች የዋናና የጀልባ መመልከቻ፣ የአሳ ማጥመጃና ሌሎች ተያያዥ የእረፍት መዝናኛ አገልግሎቶች በማቅረብ፣ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩን በበርካታ የሀገር ውስጥና አለም አቀፍ ጎብኚዎች ተወዳጅ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል።

ከውኃ መዝናኛዎቹ ጎን ለጎን፣ የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ መልክአ ምድራዊ ውበትና የብዝሃ ህይወት ኃብት በዘርፉ ገበያ ውስጥ ተፎካክሮ የተለያየ ፍላጎትና ምርጫ ያላቸውን ጎብኚዎች ወደ አካባቢው ለመሳብ የሚያበቁ ልዩ መስህባዊ ኃብቶች ናቸው። ከልዩ ኃብቶቹ መካከል የአካባቢው ወንዞች፣ ሰንሰለታማ ተራራዎች፣ ትላልቅ የአለት ቋጥኞች፣ ሸለቆዎችና የተፈጥሮ ደኖች እርስ በእርስ ተሳስረው የፈጠሩት ማራኪ ውበት አንዱ ነው። ይህን ልዩ እሴት በወንዝ ዳርና በተራራማ

ቦታዎች የእግር ጉዞ በማድረግ ለሚረኩ ጎብኚዎች እና ለዱር ህይወት አፍቃሪ፣ ተመልካችና አድናቂዎች በማስተዋወቅ በርካታ የሀገር ውስጥና አለም አቀፍ ጎብኚዎችን መሳብ ይቻላል፡፡

የዚህ ውበት አካል የሆነው የተፈጥሮ ደን በተለያዩ ሰው ሰራሽ ጫናዎች ምክንያት ከአብዛኛው የአባይ መፍሰሻ አካባቢዎች በመጥፋት ላይ ያሉ እጽዋቶችን አሰባስቦ የያዘ ነው፡፡ ከላይ በተራ ቁጥር 8.1 ላይ እንደተዘረዘረው በቅሪት ሀብቱ ውስጥ ከትናንሽ ቁጥቋጦና ሐረጎች እስከ ግዙፍና ዕድሜ ጠገብ ዛፎች ድረስ ያሉ የእጽዋት ዝርያዎች በውኃና ከውኃ ውጭ የሚኖሩ አጥቢ፣ ተሳቢና ትናንሽ ነብሳት እና በተለያዩ ቀለማት ህብር የደመቁ በርካታ አእዋፋትና ቢራቢሮዎች ተሰባጥረው ይገኛሉ፡፡

በመሆኑም ቅሪት ሀብቱ በጥብቅ ቦታ አስተዳደራዊ ስርአት ለምቶ ለቱሪዝም ገበያ ሲቀርብ፡

- *በተፈጥሮ ኃብት ባለሙያዎች፣ አድናቂና ተመልካቾች*
- *በዩኒቨርስቲና በሌሎች ከፍተኛ ትምህርት ቤቶች ላለው የመማር ማስተማር ሒደት ደጋፊ የሆኑ መግለጫና ማስረጃዎችን ለማግኘት በሚፈልጉ ተቋማት ፣*
- *በአባይና ገባር ወንዞች ውሀና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ፣ ልማትና የጋራ አጠቃቀም ላይ የሚመክሩ አለም አቀፍና የሀገር ውስጥ አውደ ጥናት፣ ሰሚናርና ስብሰባ አደራጆች፣*

ተመራጭ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡


ከተፈጥሮ ቅርሶች ጋር የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ አካባቢ በበርካታ ቁሳዊና ቁሳዊ ባልሆኑ ባህላዊ እሴቶች የታደለ ነው፡፡ ለአብነት በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ደጀን በሆነው አካባቢ የሚኖረው ህዝብ የሰሜን ሸዋ፣ ደቡብ ወሎና የምስራቅ ጎጃም የሚኖረው የአማራ ህዝብ እንዲሁም የደቡብ ወሎና ሰሜን ሸዋ (በኦሮሚያ ክልል) ኦሮሞ ብሄረሰቦች ባህልና የአኗኗር ስርአት የሚንፀባረቅበት ነው፡፡ በአካባቢው ክርስቲያንና ሙስሊም አማኞች መካከል ያለው ጠንካራ ማህበራዊ ግንኙነትና የእርስ በእርስ መደጋገፍ ለመላው አለም አብነት የሚሆን ሌላው ልዩ እሴት ነው፡፡ ሁለቱ እምነቶች እርስ በእርስ ተከባብረው የመጽሐፍ ቅዱስና ቁራን ትምህርቶችን ለተከታዮቻቸው እያስተማሩ ለረጅም ዘመን አብረው ኖረዋል፡፡

እነዚህ ልዩ እሴቶች ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ በቱሪዝም ገበያ ውስጥ ወደፊት የሚያደርገውን ፉክክር የሚያጠናክሩ ተጨማሪ አቅሞች ናቸው፡፡

ለክልሉ የቱሪዝም እድገትና ልማት የሚኖረው አስተዋፅዖ

የበቶ፣ ወለቃ እና አባይ ሸለቆ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ በክልሉ የጥብቅ ቦታ አስተዳደር ስርአት ተጠብቆ ቢለማ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለአገራዊና አካባቢያዊ ማህበረ ኢኮኖሚ ልማት ጉልህ ሚና ማበርከት የሚችል ልዩ ሀብት ነው፡፡ ይህን ከወዲሁ ከሚያመላክቱ እውነታዎች አንዱ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ለክልላችን ጎብኚዎች ዋነኛ መተላለፊያ ከሆኑ መስመሮች ጋር በቀላሉ ለመተሳሰር በሚያመች ቦታ ላይ መገኘቱ ነው፡፡

ለአብነት የደሴ፣ ባህር ዳር፣ ጎንደር፣ ሰሜን ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ፣ ላሊበላና የአክሱም ቅርሶችን ለመጎብኘት በደብረ ብርሃን ወይም በደጀን ከተማ በኩል ለሚጓዙ ቱሪስቶች በእግረ መንገድ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩን ለመጎብኘት በርካታ አማራጮች አሏቸው፡፡ በተለይ በአካባቢው በአሁኑ ወቅት በፌደራል፣ በአማራና ኦሮሚያ ክልል ገጠር መንገድ ባለስልጣኖች በግንባታ ሒደት ላይ የሚገኙ ሶስት የመንገድ ፕሮጀክቶች በእቅዳቸው መሰረት ሲጠናቀቁ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ከአዲስ አበባ፣ ከደሴና ባህር ዳር ግማሽ ቀን ባልሞላ የመኪና ጉዞ ተደራሽ ይሆናል፡፡



ምስል 9. በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ አካባቢ የሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎችን የሚያስተሳስሩ ዋና ዋና መስመሮች

በመሆኑም በየትኛውም የቱሪስት መዳረሻ የማይተኩ የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ መስህባዊ እሴቶች ወደፊት ነባሩን የቱሪስት ጉዞ መስመር በማስፋትና በማጠናከር ለዘርፉ ልማት የሚኖረው ከፍተኛ ሚና ከወዲሁ ለመገመት አዳጋች አይሆንም፡፡

ጎን ለጎን ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ በጥብቅ ቦታ አስተዳደር ለምቶ ለቱሪዝም ገበያ ሲቀርብ፣ ከጎብኚዎች እይታ እስካሁን የራቁ ሌሎች የአካባቢው መስህቦች ከዘርፉ ገበያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያግዝ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ የዚህ ትሩፋት ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብለው ከሚጠቀሱ የአካባቢው ቅርሶች መካከል የቦረና ሳይንት ብሄራዊ ፓርክ ቀዳሚ ነው፡፡

በ2001ዓ.ም ከባህር ጠለል በላይ ከ1900 እስከ 4280 ሜ ከፍታ ባላቸው የቦረናና ሳይንት አካባቢዎች የተቋቋመው ይህ ብሄራዊ ፓርክ የጭላዳ ዝንጀሮ፣ ቀይ ቀበሮና የምኒሊክ ድኩላን የመሳሰሉ ብርቅዬ የዱር እንስሳትን አሰባስቦ የያዘ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ብሄራዊ ፓርኩ እስካሁን ከቱሪዝም ገበያ መጠቀም አልጀመረም፡፡

ስለዚህ የተለያየ ተፈጥሮ ኃብት ይዘትና ስነ ምህዳራዊ ውክልና ያላቸውን ተጎራባች ፓርኮች በአባይ ወንዝ በኩል በማስተሳሰር፣ ለአካባቢው የቱሪዝም እድገት ትልቅ ግብአት የሚሆን መልካም አጋጣሚን በቀላሉ መፍጠር ይቻላል፡፡

ከዚህ የተፈጥሮ ቦታ ጋር በበቶ፣ በወለቃ እና አባይ ሸለቆ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ የጉዞ መስመር ውስጥ ለሚገኙ ሌሎች ቁሳዊና ቁሳዊ ያልሆኑ መስህባዊ እሴቶች፣ የቱሪዝም እንቅስቃሴን ለማጠናከር የሚያግዝ ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር ይታመናል፡፡ በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ አካባቢ ከሚገኙ ታሪካዊና ኃማኖታዊ የመስህብ ሃብቶች መካከል፡-

ሰንጠረዥ 5፡ በታሳቢ ጥብቅ ቦታው ዙሪያ በግንባታ እቅድና ሒደት ላይ የሚገኙ የመንገድ ፕሮጀክቶች ዝርዝር

የበግንባታ ሒደት ላይ ያሉ የመንገድ ፕሮጀክቶች			
መነሻና መድረሻ	**ዋና ዋና መተላለፊያ**	**አሰሪ**	**ደረጃ**
ከግንደ ወይን እስከ ኮምቦልቻ	መርጦለ ማርያም - መካነ ሰላም - ለጋምቦ	የፌደራል መንገዶች ባለስልጣን	አስፓልት
ከሰቆጣ እስከ አለም ከተማ	ከለላ - በቶ ወንዝ	የፌደራል መንገዶች ባለስልጣን	ጠጠር
ከወግዲ እስከ ገብረ ጉራቻ	አብዬ ጎርባ - ወለቃ ወንዝ - ደራ (አደራ)	የአማራና ኦሮሚያ ክልል መንገዶች ባለስልጣን	ጠጠር

የመረጃ ምንጭ፡ መስክና የክልሉ መንገዶች ባለስልጣን

1. የአባ ጽጌ ድንግ አንድነት ገዳም

ይህ ውቅር አብየተ ክርስቲያን ከወግዲ ከተማ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በግምት 6 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። ገዳሙ የተመሰረተው በ14ኛዉ ክፍለ ዘመን ሲሆን መስራቹም አባ ጽጌ የማነ ይባላሉ። አባ ጽጌ የማነ /ጽጌ ድንግል/ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በለቅነታቸዉ የሚታወቁ የማህሌተ ጽጌ ደራሲ ናቸዉ። እኽህ አባት የእውቁ ነገረ መለኮት ጸሀፊ የአባ ጊዮርጊስ ዘ ጋስጫ የታሪክ አቻ እና የቅርብ ጓደኛ ሲሆኑ የአባ ጋስጫ /ሳግላ/ ዘ ጊዮርጊሰ እና የአባ ጽጌ ድንግል ገዳማትም በመካከላቸው ያለው ርቀትም ከ4 ኪሎ ሜትር ያልበለጠ ነው። ይህ ገዳም በ1530 በግራኝ ወረራ ወቅት ተዘግቶ እስከ 1912 ዓ.ም ባለው ጊዜ ለ350 አመታት በደን ተሸፍኖ ከቆየ በኋላ በአካባቢው ከብት ይጠብቁ የነበሩ እረኞች ባደረጉት ጥቆማ እንደገና በ1912 ሊከፈት ችሏል።

ሆኖም አገልሎት የሚሰጡ ካህናት በመታጣቸው በውስጡ የተገኙ ታቦታት እና ንዋየ ቅድሳት ወደ ሌላ ቦታ ተወስደው ገዳሙ መልሶ ለ80 አመታት በድጋሜ ተዘግቶ ከቆየ በኋላ በ1996 ዓ.ም በአካባቢው ህዝብ፣ መስተዳድርና በጎ አድራጊ ግለሰቦች ጥረት ለሁለተኛ ጊዜ ተከፍቶ መንበረ ታቦቱ ወደ ጥንት ቦታው ተመልሶ ግልጋሎት እየሰጠ ይገኛል። የአባ ጽጌ ድንግል አንድነት ገዳም በተራራ ጥግ ከአለት ተፈልፍሎ የተሰራ ውቅር አብያተ ክርስቲያን ነው። ቤተ ክርስቲያኑ የብረት በር የተገጠመላቸው ሁለት የመግቢያ በሮች አሉት። ከበሮቹ አንደኛው የወንዶች መግቢያ ሲሆን ወደቅኔ ማህሌት የሚያስገባ ነው። ሁለተኛው ወደ ቅድስት የሚወስደው የሴቶች መግቢያ ነው።

የህንጻው አሰራር የላሊበላ ውቅር አብየተ ክርስትያንን ንድፍ ተከትሎ የተሰራ ሲሆን በውስጡ ሰባት ክፍሎች አሉት። አነዚህ ክፍሎችም ደጀ ሰላም፣ ሁለት መቅደሶች፣ ቅኔ ማህሌት፣ ቅድስተ-ቅድሳት የአባጽጌ መኖሪያ እና አጽመ ቅዱሳን ማሳረፊያ ናቸው። በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ያሉ

ክፍሎች የተከፋፈሉት በአምዶች ነው፡፡ አምዶቹ እና የዋሻዉ ጣሪያ በሀረግ ጥልፈ ንድፍ ያገጡና ልዩ ስነ ጥበባዊ አሰራር የሚታይባቸው ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለቤተልሔም ግልጋሎት የሚሰጥ ሌላ ፍልፍል ከዋናው ቤተክርስቲየን ጎን አል፡፡

2. የቀዳሚት ግሸን ደብረ ከርቤ አባ ያዕቆብ አንድነት ገዳም

ይህ መካነ ቅርስ ከወግዲ ከተማ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ 1.5 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ወደ መካነ ቅርሱ የሚወስደው የእግር መንገድ ሰንሰለታማ ተራራ ሲሆን የአካባቢው ስነ-ምህዳር ከፍተኛ መስህብነት አለው፡፡ ቀዳሚት ግሸን ደብረ ከርቤ አባ ያዕቆብ አንድነት ገዳም የተመሰረተው በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደሆነ የገዳሙ ታሪክ ያስረዳል፡፡ የዚህ ገዳም መስራች አባ ያዕቆብ የተባሉ አባት ሲሆኑ እኝህ አባት በዚህ ገዳም ወንበር ዘርግተው ያስተምሩ እንደነበር ገድላቸው ይናገራል፡፡



ምስል 10. በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ አካባቢ ከሚገኙ ታሪካዊና ኃይማኖታዊ ቅርስቶች በከፊል

ግሸን ማለት ገስግሰን ደረስን ማለት እንደሆነ እና ደብረ ከርቤ ማለት ደግሞ የሸቶ እና እጣን ማዕዛ ያለው ደብር ማለት እንደሆነ የገዳሙ አባት ይናገራሉ፡፡ ገዳሙ ያለበት አካባቢ መልክአ ምድር የመስቀል ገጸ-ምስል የያዘ በመሆኑ አጼ ዘርዐ ያእቆብ ‘’መስቀሌን በመስቀለኛ ተራራ ላይ አስቀምጥ” በማለት የታያቸውን ራዕይ እውን ለማድረግ ክቡር መስቀሉን ይዘው ለ6 ወራት ወደ አሁኑ ግሸን ደብረ ከርቤ ከመሄዳቸው በፊት አርፈውበት ስለነበር ቀዳሚት ግሸን ደብረ_ከርቤ የሚል መጠሪያ እንደተሰጠው እና የመስራቹ አባት ስም ተጨምሮበት ቀዳሚት ግሸን ደብረ ከርቤ አባ ያዕቆብ አንድነት ገዳም ተብሎ ሊጠራ እንደቻለ የገዳሙ አበምኔት አባ ገብረ ጻድቅ ያስረዳሉ፡፡

ይህ ገዳም በ1530ዎቹ በግራኝ አህመድ ወረራ ወቅት እንደተዘጋ እና ካህናቱም በወረራው ወቅት ወደ ምስራቅ ትግራይ ዞን አጽቤ ደራሀ በመሸሸ በዛው አካባቢ የቀሩ ሲሆን ገዳሙም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ተዘግቶ ከቆየ በኋላ በ1905 ዓ.ም አካባቢ የገዳሙን ታሪክ ያነበቡ ካህን ከትግራይ /አፅቢ ደራ/ መጥተው ስለ ጥንታዊ የአባ ያዕቆብ ገዳም ያነበቡትን ታሪክ ለንጉሥ ሚካኤል ባደረጉት ጥቆማ መስረት እንደገና ለመከፈት ተችሎ ነበር፡፡ ሆኖም በጣሊያን ወረራ ዓ.ም ወቅት መልሶ በመዘጋቱ ለ67 አመት በድጋሜ ተዘግቶ ከቆየ በኋላ በ1995 ዓ.ም መልሶ ተከፍቶ መንበረ ታቦቱ ወደ ቦታው ተመልሶ ግለልጋሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

3. ምስካዬ ቅዱሳን ገዛዛ አቡነ ገ/መንፈሰ ገዳም

ምስካየ ቅዱሳን ገዛዛ ገ/መንፈስ ቅዱስ ገዳም በገዛዛ 018 ቀበሌ ከወግዲ ከተማ ምዕራብ አቅጣጫ 25 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። ምስካየ ማለት መጠጊያ ሲሆን ምስካየ ቅዱሳን ማለት የቅዱሳን መጠጊያ እንደማለት እንደሆነ አባቶች ያስረዳሉ። ይህ ገዳም አብየ ጉርባ ከሚባለው ንዑስ ጣቢያ አቅራቢያ የሚገኝ ሲሆን ወደ መካነ ቅርሱ ሙሉ በሙሉ በመኪና የሚወስድ መንገድ አለው። ገዳሙ የተመሰረተው በቅዱስ ላሊበላ ዘመን በራሳቸው በላሊበላ እንደሆነ የገዳሙ አባቶች ይናገራሉ። የገዳሙ ታሪክ እንደሚያስረዳው ቅ/ላሊበላ አሁን ያለውን ውቅር አብየተ ክርስቲያን በወርወር (ሮሀ) ላሊበላ መስራት ከመጀመራቸው በፊት በገዛዛ አርፈው ይህን መካነ ቅርስ ሰርተዋል።

በዚህ ቦታ እያንዳንዳቸው የተለያዩ ክፍሎች ያላቸው ስድት ውቅር አብያተ ክርስቲያናት አሉ። ከነዚህ መካከል ከታች ወደ ላይ ሲወጣ የመጀመሪያው የንፍሮ ገዳም ተብሎ የሚጠራው ሲሆን ይህ ህንጻ ለሰንበቴ እድመተኞች ግልጋሎት እየሰጠ የሚገኝ ነው። ሁለተኛው ለቅኔ ማህሌት የሚያገለግለው ውቅር አብያተ ህንጻ ሲሆን ሁለት በሮች አሉት 3ኛው መቅደስ ሲሆን ክብ ቅርጽ አለው። 4ኛው የማመስገኛ ክፍል ሲሆን አንድ መግቢያና መውጫ በር አለው። 5ኛው የመነኮሳት ክፍል እና 6ኛው የመቃብር (አጽም) ማሳረፊያ ናቸው።

4. ደብረ ባህርይ ጋስጫ አባ ጊዮርጊስና አባ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም

ደብረ ባህሪይ ጋስጫ አባ ጊዮርጊስ ገዳምና አባ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም በከለላ ወረዳ ጥራንጥር ቀበሌ ከከለላ ከተማ ምዕራብ አቅጣጫ 42 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ይገኛል። ወደ ገዳሙ አምባ ላይ ለመውጣት የሚቻለው እንደ ደብረ-ዳሞ ገዳም በገመድ፣ እንደ ጣና ገዳማት በጀልባ ሳይሆን በሁለት እርከን በተከፈሉ 46 ሜትር ከፍታ ያላቸው መሰላሎችን በመጠቀም በአንድ በር ብቻ ነው። ይህ መሰላል የተሰራው በቋጥኞች መካከል በተረበረቡ የጠደቻ (ግራር) እና ቅንጭብ እንጨቶች ነው።

ይህ በተፈጥሮአዊ ውበቱ እጅግ የሚማርከው ገዳም በታላቁ ሊቅ ደራሲ፣ አስተማሪ እና መሀንዲስ በሆኑት አባ ጊዮርጊስ በአፄ ይስሀቅ ዘመነ መንግስት (1399 -1414) ተመሰረተ። ይህ የበርካታ ተፈጥሮአዊና ሠው ሰራሽ ቅርሶች ባለቤት የሆነው ገዳም ከ600 አመት በላይ እንደኖር ይነገርለታል። ታላቁ ሊቅ አባ ጊዮርጊስ በዚህ ቦታ (ገዳም) በርካታ በዓለም ተደናቂነትን ያተረፋባቸውን ከ40 በላይ ድርሰቶች ደርሰውበታል። ከድርሰቶቻቸው መካከልም መጽሐፈ ምስጢር፣ አረጋኖን ቅዳሴ፣ እንዚራ ስብሀት፣ መጽሐፈ ስዓታት የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው።

በዚህ አምባ ላይ አባ ጊዮርጊስ የፈለፈሏቸው የተለያየ ክፍል ያላቸው የዋሻ ፍልፍል ህንፃዎች አሉ። ከእነዚህ የዋሻ ፍልፍል ህንፃዎች አንዱና ግዙፉ በራሳቸው ስም አገልግሎት እየሰጠ ያለው ቤተ ክርስቲያን ነው። ሌላውና እጅግ በጣም አስደናቂው ነገር ደግሞ በዚሁ አምባ ላይ ያሉት የውሃ ችግርን ለመቋቋም በአባ ጊዮርጊስ እጅ የተቆፈሩት የውሃ ማቆሪያዎች ናቸው።

5. ታላቁ የደገር ጌታው ሸህዬ መስጅድ

ታላቁ የደገር ጌታው ሸህዬ መስጅድ ከወረዳችን ርዕሰ ከተማ /ከለላ/ በስተደቡብ በ26 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል። የደገር ጌታው ሸህዬ መስጅድ በ1860 ዓ/ም ባቄሎ እየተባለ በሚጠራው ቦታ በሸህ ሸሪፍ እብራሂም /ሸረፈድን/ በተባሉ ታዋቂ የሀይማኖት አባት እንደተመሰረተ በቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ያመለክታል። ሸረፈድን ማለት የእስልምና ሃይማኖት ማወቂያንና ማፍለቂያ ማለት ነው ይላሉ የታሪክ ምንጮች /ሸህ ባህሩ/።

የዚህን የታላቁ የደገር ጌታው ሸህዬ በዓል በአራቱም ማዕዘን በሸህ የሚቆጠር ህዝብ በመምጣት በየአመቱ ጥቅምት 15 ቀን ይከበራል። ከኃይማኖታዊ ስነ ስርዓቱ ጋር ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ዙሪያ የሚኖሩ ሙስሊሞች ለረጅም ዘመናት ጠብቀው ያቆዩት ባህላዊ የቁራን ትምህርት (ደረሳ) የጎብኚዎችን ትኩረት የሚስብ ልዩ እሴት ነው።

እነዚህ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ተቋማት በክልላችን ካሉት ተመሳሳይ ታሪካዊ ቦታዎች አንፃር ሲታይ የማስተዋወቅ ስራ ከተሰራ በርካታ ጉብኝዎችን ሊስቡ እንደሚችል መገመት አያዳግትም።

በአጠቃላይ በ12 እና 14ተኛው ክፍለ ዘመን ከትላልቅ አለቶች ተፈልፍለው በተገነቡት በእነዚህ ገዳማት ውስጥ የቀደምት ስልጣኔ እና ባህል ውጤት የሆኑ በርካታ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ይገኛሉ። ወደ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ የሚመጡ ቱሪስቶች ቅርሶቹን ካለተጨማሪ ወጪና ድካም በየገዳማቱ ካሉ የመነኮሳት ህይወት፣ የቅኔና ተያያዥ ኃይማኖታዊ ትምህርቶችን በማስጎብኘት ይበልጥ በአካባቢው እንዲረኩ ያደርጋል።

የአካባቢው ሌላው ተጠቃሽ ቅርስ በ1928 ዓ.ም ጋር አገራችንን የወረረውን የጣልያን ጦር ወደ መጣበት ለመመለስ በተደረገው የአርበኞች ትግል ውስጥ ከፍተኛ ስምና ዝና ለነበራቸው የበላይ ዘለቀና ሽፈራው ገርባው ወታደሮች የጦር ሰፈር የነበረው የሶማ በረሃ/ደን ነው። በታሳቢ ፓርኩ ክልል ውስጥ የሚገኘው ይህን ደን ለሀገር ውስጥና ለአለም አቀፍ ጎብኚዎች የአርበኞቹን ጀግንነታዊ ተጋድሎዎች በመዘከር ይበልጥ እንዲዝናኑ ማድረግ ይቻላል።

በሌላ በኩል ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ የጉዞ መስመሮች ከቱሪዝም ገበያ እስካሁን በቂ ጥቅም ማፍራት ያልጀመሩ ቅርሶች አሉ። ለአብነት፡-

- *በ1297 ዓ.ም ተመስርቶ በደራሲ አዲስ አለማየሁ ፍቅር እስከ መቃብር መጽሐፍ በአብዛኛው የሀገራችን ህዝብ የሚታወቀው የዲማ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን፣*
- *በ4ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተሰርቶ በአሁኑ ወቅት ፈራርሶ የሚገኘው የመርጦ ለማርያም ገዳም፣*
- *በበንጉስ አጸበሃ ልጅ በአስፍሃ አጸበሃ በ351 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ የተመሰረተው የደብረ ወርቅ ገዳም እና በ1751 ዓ.ም የተገነባው የሞጣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን፣*

- *በበርካታ የነገስታት ገጸበረከቶች፣ ጥንታዊ የቤተክርስቲያን መገልገያ ቁሳቁሶችና የብራና መፀሐፍት የታደለችው ተድባበ ማርያም ቤተክርስቲያን፣*
- *የአፄ ቴዎድሮስ ጀግንነታዊ ተጋድሎዎች መገለጫ የሆነው የመቅደላ አምባን በማስተዋወቅ የአካባቢውን የቱሪዝም እንቅስቃሴ ማሳደግ ይቻላል።*



ምስል 11. ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ውስጥ ለጣውላና እርሻ ሲባል የሚፈፀም ህገ ወጥ ደን ጭፍጨፋ

8.4. የወለቃ፣ በቶና አባይ ሸለቆ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ላይ እየደረሱ ያሉ ችግሮች

የወለቃ በቶና አባይ ታሳቢጥብቅ ቦታ ሰፊ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት ክምችት ቢኖረውም በአሁኑ ስዓት እጅግ በጣም ውስብስብ እና እርስበርሳቸው በተሰናሰሉ ችግሮች ጫና ውስጥ ይገኛል። ከእነዚህም ውስጥ በታሳቢ ጥብቅ ቦታው የታዩ ዋና ዋና ችግሮችና ስጋቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ህገ ወጥ ደን ጭፍጨፋ

ሶስቱንም ወንዞች/አባይ፣ወለቃና በቶ/ ተከትሎ ባሉት ሁለት የስነ ምህዳር ስርዓቶች ላይ በህዝብና የቤት እንስሳት ቁጥር መጨመር፣ በእርሻ መስፋፋት በከሰል፣ ማገዶና በጣውላ ንግድ ምክንያት በተፈጥሮ ደኑ ላይ ከፍተኛ ጭፍጨፋ እየተካሄደበት ይገኛል።

በቦረና ወረዳ 6 ቀበሌዎች፣ በወግዲ ወረዳ 11 ቀበሌዎች፣ በከላላ ወረዳ 5 ቀበሌዎች ውስጥ ለጥናት ተሟሉረን ባየንበት ወቅት በሁሉም ቀበሌዎች ችግሩ እየተስፋፋ ያለ ቢሆንም ከችግሩ ግዝፈት አንጻር በዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ጥበቃ ህብረት/IUCN/ መሰፈርት መስረት የቦረና ወረዳ 5 ቀበሌዎች እና የከላላ ወረዳ 2 ቀበሌዎች ከጥብቅ ስፍራነት ውጭ ሆነዋል።



ምስል 12. በታሳቢው ብሄራዊ ፓርኩ ውስጥ ለከሰል፣ ደረባ ቤት መስሪያ እና የማገዶ እንጨት ሲባል የሚፈፀም ደን ጭፍጨፋ

የደን ጭፍጨፋ በዋናነት የሚካሄደው በእርሻ መስፋፋት ምክንያት እንደሆነ በጥናቱ ወቅት በተለይም አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ ስርዓተ ምህዳርን

(*Acacia-Boswellia-Commiphora* ecosystem) በሚወክለው የተፈጥሮ ደኑ አካባቢ ተመልክተናል፡፡ በቅርብ ጊዜ ደን የነበሩ የወል የደን መሬቶች ታርሰው ለእርሻ አገልግሎት ውለው ተመልክተናል፡፡

በተበጥናታችን ወቅት በደኑ ውስጥ ከ54 በላይ የከብት ማሳደሪያ የደረባ ቤቶችን አግኝተናል፡፡ እነዚህ የደረባ ቤቶች የሚዘጋጁት በአካባቢው የሚገኙ የተፈጥሮ ደኖች ተመንጥረው ነው፡፡ ለምስሌ በወግዲ ወረዳ ቀበሌ 013 ወደ ደራ መሻገሪያ/ኬላ በሚገኘው ደረባ ውስጥ የ7 አባዎራዎች ከ266-378 ከብቶችን በአንድ ጊዜ የሚያስተናግድ የከብቶች ማደሪያ ደረባ ቤቶችን አግኝተናል፡፡

በበቶ፣ በአባይና ወለቃ ወንዞች አካባቢ የሚገኙ ዕድሜ ጠገብ የሆኑ እንደ ዋርካና ጥቁር እንጨት ያሉ ዛፎች ተጨፍጭፈው ዕዕዋቶቹ ለጣውላ ምርት መሬቱ ደግሞ ለእርሻ እንደ ዋለ ማረጋጥ ችለናል፡፡ የከሰል ማክሰል እና የማገዶ እንጨት ምንጣሮዎች በሁሉም ወረዳዎችና ቀበሌዎች የሚከናወኑ ሲሆን በተለይም በወግዲ ወረዳ ቀበሌ 08 ብዛት ያላቸው አክሳዮችንና የማክሰያ ቦታዎችን እንዲሁም ለማገዶ የሚሆን እንጨት የሚጭኑ አህያዎችንና ቆራጮችን ከነመጥረቢያቸው አግኝተናል፡፡ በአጠቃላይ ይህ የደን ጭፍጨፋ የሚከናወነው በወረዳው ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆን በአብዛኛው ከምስራቅ ጎጃም ዞን እናርጅና እናውጋ፣ ሸበል በረንታ ወረዳዎች፣ ከኦሮሚያ ክልል ደራ ወረዳ እና ከሰሜን ሸዋ ዞን ሚዳ ኦሮሞ መራኛ ወረዳ በሚኖሩ አርሶ አደሮች መሆኑንም አረጋግጠናል፡፡



ምስል 13. በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ውስጥ እየተስፋፋ ያለው ህገ ወጥ እርሻ

የህገ ወጥ እርሻ መስፋፋት

አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ ስርዓተ ምህዳርን (*Acacia-Boswellia-Commiphora* ecosystem) ተከትሎ በሁሉም ቀበሌዎች በህገ ወጥ መንገድ ከፍተኛ የእርሻ መስፋፋት ይታያል፡፡ በተለይም በወግዲ ወረዳ ቀበሌ 013 እና 09 የወለቃን ወንዝ ተከትሎ እና በከላላ ወረዳ ቀበሌ 019 ደግሞ የበቶን ወንዝ ተከትሎ አገዩና ሚራቶ አካባቢ ያለው የዕጣን ዛፍ፣ የጥቁር እንጨት፣ ጠዬቻ፣ የአደርና ደሬ ዛፎችን በህገ-ወጥ መንገድ በመመንጠር የእርሻ ማሳን ከማስፋፋት ጋር ተያይዞ ደኑ በከፍተኛ የእሳት ቃጠሎ ወደ እርሻነት እየተቀየረ ይገኛል፡፡

በቦረና ወረዳ የምሳር መሬት ይዞታ (በህገወጥ መንገድ የደን መሬት ተመንጥሮ የተያዘ) የሚባል ህገወጥ የይዞታ ማስፋፋት ሲኖር በወግዲና ከላላ ወረዳዎች ደግሞ የቀበሌው ነዋሪዎች በሌላ ቀበሌ ለሚኖሩ ሰዎች በግማሽ፣ በሲሶ እና አንድ አራተኛ (እርቦ) እያከራዩ መሬት አስተዳደር የማያውቀው ሰፊ የሆነ ህገወጥ የመሬት ይዞታ እንዳላቸው አረጋግጠናል፡፡ በዚህ አካባቢ የሚታየው ፊውዳላዊ ህገወጥ እንቅስቃሴ ጉልህ የተፈጥሮ ሀብት ውድመት እና ከፍተኛ የሆነ የመሬት ኪራይ ሰብሳቢነት አባዜዎች



እንዳሉበት ታዝበናል፡፡ በዚህ ምክንያት ይህንን ለመከላከል ጉዳዩ የሚመለከታቸው የህግ አካላት የያዘ አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ በየቀበሌው በመዞር በህገ ወጥ መንገድ እርሻ ያረሱ ግለሰቦችንና እርሻዎቻቸውን የመለየትና አስፈላጊውን ቅጣት የማስወሰን እንዲሁም የደን፣ የግጦሽ እና የእርሻ መሬት አጠቃቀምን የመለየት ስራ ከወዲሁ መከናወን ይኖርበታል፡፡

ምስል 14. በታሳቢ ብሄሄራዊ ፓርኩ ውስጥ ያለው የልቅ ግጦሽ ተዕዕኖ

ልቅ ግጦሽ

ከህገ ወጥ እርሻ እና ደን ጭፍጨፋ ቀጥሎ የተፈጥሮ ደኑ ዋነኛ ችግር ነው፡፡ በጥናታችን ወቅት እኛ በሄድንበት መስመር ከ54 በላይ የከብት ማደሪያ የደረባ ቤቶችን ተመልክተናል፡፡ እነዚህ የቤት እንስሳት ከአዋሳኝ ቀበሌዎች በተጨማሪ ከሩቅ ቀበሌዎች አካባቢ የሚመጡ ናቸው፡፡

ይህ በመሆኑም ከፍተኛ ቁጥር ያለው የቤት እንስሳት በደኑ ውስጥ ይገኛል፡፡ ይህም በዱር እንስሳት የመመገቢያና መኖሪያ ቦታ ላይ ጫና በመፍጠሩ ምክንያት እንዲሰደዱ፣ አንዲታደኑና እንዲጠፉ አድርጓል፡፡

በተጨማሪም ለእርሻ መስፋፋት፣ ለጣውላ ንግድና ለደረባ ቤት ግባታ ደን ጭፍጨፋና ህገ ወጥ አደን እንዲስፋፋ አስተዋፅዖ አድረጓል፡፡ እንዲሁም በዕዕዋት እድገት ላይ አሉታዊ ተዕዕኖ ከማሳደሩም በላይ መጤ ዕዕዋት አካባቢው እንዲስፋፉ አድርጓል፡፡

ህገ ወጥ አደን

በከርከሮ፣ ቆቅ፣ ዝግራ፣ ድኩላ ወዘተ በመሳሰሉ የዱር እንስሳት ላይ ህገ ወጥ አደን ይፈፀማል፡፡ በሰብል ወቅት በሰውና በዱር እንስሳት በተለይም በዝንጀሮና በከርከሮ መካከል ግጭት ስለሚፈጠር ዝንጀሮን ጨምሮ በከርከሮ ላይ ከፍተኛ አደን እየተፈፀመ ይገኛል፡፡



ምስል 15. በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ውስጥ በድኩላ እና ዘንዶ የዱር እንስሳት ዝርዎች ላይ እየደረሰ ያለ ተዕዕኖ

በ2003 ዓ.ም ብቻ በቀበሌ 015 የሚኖር አንድ ግለሰብ 7 ከርከሮዎችን እንደ ገደለ ከአይን እማኞች ተነግሮናል፡፡ በተጨማሪም በወግዲ ወረዳ እና በደራ ወረዳ መካከል የወለቃ ወንዝን ተከትሎ ከ29 በላይ በዚህ ዓመት የተሰሩ የማደኛ ጎጆዎችን የቆጠርን ሲሆን የዱር እንስሳቱ ውሃ ለመጠጣት በሚመጡበት ጊዜ ይገድሏቸዋል ይህንንም ድርጊት ከደራ ወረዳ በመጡ ሁለት አ/አደሮች ነፍሰጡር/ክበድ/ የሆችውን ድኩላ ከገደሉ በኋላ የእናቲቱን ስጋ ወሰደው የልጅቱን ሽል እና ፈርስ አገኙተን በተግባር ሲከናወን ተመልክተናል፡፡

እነዚህ አ/አደሮች በዚህ ተግባር ተሰማርተው ባገኘናቸው ወቅት ጉዳዩን ቀርቦ በሰላማዊ መንገድ ከመነጋገርና ከመረዳዳት ይልቅ መሳሪያቸውን በመደገን እንተላለፍ በማለት ፍጥጫ ውስጥ በመግባታቸው መወያየትም ሆነ መነጋገር አልተቻለም፡፡

የእርሻ ኢንቨስትመንት

በወግዲ ወረዳ በተፈጥሮ ደኑ ውስጥ የአባይ እና ወለቃ ወንዞችን ተከትለው በሚገኙ 026፣ 018፣ 017፣ 016 እና 015 ቀበሌዎች ካሉ የደን አካባቢዎች መካከል አጋማይት፣ አቡ ጠንጠቃ፣ ደድሃሬ፣ ጠማሜ፣ መጋጠሚያ፣ ሰንበቶ፣ ዲዳ ዋጮ ቀዋ ዳባ እና ደጋ ዋናዎቹ ሲሆኑ እነዚህ የደን ቦታዎች በጣም ሜዳማ፣ በዚህ ዓይነት፣ ቁመትና ውፍረት የትም ቦታ የማይገኙ ዛፎችን አቅፈው የሚገኙ ቢሆንም ሜዳማና ለመስኖ እርሻ አመቺ በመሆናቸው የተነሳ ለእርሻ ኢንቨስትመንት እንዲውሉ ለማድረግ የተጠኑ መሆኑና ለኢንቨስተሮች ለመስጠት በመታሰቡ ከፍተኛ ችግር ላይ ያሉ መሆናቸውን ተረድተናል፡፡

በከለላ ወረዳ ደግሞ በቀበሌ 017 የሚገኘው የበቶ እርሻ ልማት አክሲዮን ማህበር (በስምምነት-91 ሄ/ር በልኬት ግን 420 ሄ/ር) በዚሁ ቀበሌ የሚገኘውን የቱሉ ጅሌ ሰፊ ደን እና የቀበሌ 019 ደንን መሃል ላይ የሚቆርጥ ከመሆኑም በላይ ወደ ፊት ሲከለል የዱር እንስሳቱን እንደልብ መዘዋወር የማያስችል በመሆኑ እና ከዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ህብረት/IUCN/ መስፈርት አንጻር እንዲህ ዓይነት የልማት እንቅስቃሴዎች በጥብቅ ቦታዎች መካከል መኖራቸውን ስለሚከለክል ከወዲሁ መፍትሄ ካልተሰጠው የታሰቢ ጥብቅ ቦታው ሌላ ችግር ሆኖ ታይቷል፡፡

በተጨማሪም በወግዲ ወረዳ ባሉት ቀበሌዎች 013፣ 015፣ 017፣ 018 እና 026 ላይ የእጣንና ሙጫ ኢንቨስትመንት በሚል ሰበብ የኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ እዝ ሰንሰለት ያልተከተለ በክልል ግብርና ቢሮ ብቻ ፈቃድ የተሰጣቸው አቶ ገዛኸኝ ኃይሉ የሚባሉ ግለሰብ የእጣን አመራረት ሳይንስ ግንዛቤውና ክህሎቱ የሌላቸው አ/አደሮችን በመቅጠር የሚያካሂዱት አንቅስቃሴ ቅሪት የእጣን ዛፎችን ለከፍተኛ ውድመት እየዳረጋቸው ይገኛል፡፡

የአካባቢው ወጣቶች መሬት አሰጣጥ ችግር

መንግሰት ስራ አጥነትን ለመቀነስና አምራቹን ኃይል የልማት ተዋናይ ለማድረግ ባስቀመጠው የዕድገትና ትራንፎርሜሽን ዕቅድ መሰረት የገጠር ወጣቶች የወል መሬቶችን በመስኖ እያለሙ ምርታማነትን ማሳደግ እና የስራ ዕድል መፍጠር የሚለውን እሳቤ በመያዝ ብቻ በህገወጥ አ/አደሮች የተያዙ ሰፊ የወል መሬቶች እያሉ ምንም ያልተነኩ የደን ቦታዎችን በመስጠት የተፈጥሮ ሀብት ውድመትና በቀጣይም

ለመስጠት መዘጋጀት እንዳለ መረዳት ችለናል፡፡ ለምሳሌ ወግዲ ወረዳ ቀበሌ 015 የሚገኝ 31.5 ሄ/ር መሬት ለ101 ወጣቶች የተከለለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 56 ወጣቶች በ6 ቡድን ተደራጅተው 7.125 ሄ/ር መሬት ተሰጧቸዋል፡፡ ይሁን እንጅ በመስክ እንዳረጋገጥነው የተፈቀደላቸውንና ስምምነት የወሰዱበትን 7.125 ሄ/ር ሳይሆን 14.5 ሄ/ር የደን መሬት በመጨፍጨፍ በመኸር ወቅት ማሽላና በርበሬ ለመዝራት ዝናብ እየጠበቁ ያገኘናቸው ሲሆን የከላላ ወረዳም በተመሳሳይ መልኩ ለታሳቢ ጥብቅ ስፍራ በሚከለሉ ቦታዎች ውስጥ ለወጣቶች መሬት ለመስጠት እንደተዘጋጀ በማረጋገጣችን ከአመራር አካላት ጋር ውይይት አካሄደናል፡፡ ይህ ችግር በህገ ወጥ የተያዙ መሬቶችን በማከፋፈል እስካልተፈታ ድረስ በቀሪ የደን ሀብቶች ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ ከፍተኛ ይሆናል፡፡

የአካባቢው ህብረተሰብ የግንዛቤ ችግር

የህዝብና የቤት እንስሳት ቁጥር መጨመር፣ በተፈጥሮ ደኑ አካባቢ ሰፈራና ህገ ወጥ እርሻ እንዲስፋፉ አድርጓል፡፡ አማራጭ የሀይል ምንጮችና የማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎች አለመስፋፋት፣ ከሰል ማክሰል፣ የማገዶ እንጨት ሽያጭና የጣውላ ምርት ችግሩ እንዲባባስ አድርጓል፡፡ ያለውን የተፈጥሮ ሃብት በመጠበቅና በማልማት ፈንታ በግንዛቤ ችግር ምክንያት በአንድ ወቅት ደን የነበረ ቦታ ወደ እርሻና መንደር እየተቀየረ መጥቷል፡፡ ለአብነት ወግዲ ወረዳ ቀበሌ 017፣ 013 እና 09 በከለላ ወረዳ ደግሞ በቀበሌ 019 መጥቀስ ይቻላል፡፡

የተቀናጀ የጥበቃ ስልት አለመኖሩ

ቀደም ሲል በ1980ዎቹ አካባቢ የደን ክልሉ የተከበረና ይጠበቅ እንደነበረ መረጃዎች የሚጠቁሙ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን በተጠናከረ መልኩ ጥበቃ ስለማይደረግለት ከኦሮምያ ክልል ከደራ ወረዳ፣ ከምስራቅ ጎጃም ዞን ከሸበል በረንታና እናርጅና እናውጋ ወረዳዎች፣ ከደቡብ ወሎ ዞን ከወግዲ፣ ቦረናና ከለላ ወረዳዎች እና ከሰሜን ሸዋ ዞን ከሚዳ ኦሮሞ መራኛ ወረዳ ነዋሪዎችና የቤት እንስሳት አማካኝነት ቦታው ከፍተኛ የሆነ የደን ጭፍጨፋና የህገወጥ አደን ጫና እየደረሰበት ይገኛል፡፡ በቀጣይም እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በየደረጃው ጥልቅ ውይይት ማካሄድ፣ መስማማት፣ የመፍትሄ ሀሳብ ማስቀመጥና ይህንን ተግባራዊ ማድረግ የግድ ይላል፡፡

8.5. ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች እና ጠቀሜታቸው

ከዳሰሳ እና ዝርዝር ጥናቶች የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክትው የበቶ፣ ወለቃና አባይ ሸለቆ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ ተፈጥሮዊ ደን ሲሆን በተለይ የወንዞችን ሜዳማ አካባቢዎች ተከትሎ የሚገኙት ደኖች በውስጣቸው እጅግ በጣም ግዙፍና ዕድሜ ጠገብ የሆኑ ዛፎችን አቅፈው የያዙ ናቸው፡፡ ይህ ደን ምናልባትም በክልላችን የአባይ ሸለቆ በሚገኝባቸው በየትኛውም አካባቢዎች ጨርሰው የጠፉ ወይም የሌሉ ቅሪት ደኖችን የያዘ የተለየና ማራኪ ስፍራ ነው፡፡ አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ ስርዓተ ምህዳርን የሚወክል ሲሆን ይህ አካባቢ በየትኛውም ቦታ እንደልብ የማይገኙና ለመጥፋት የተቃረቡና መጠበቅ የሚገባቸው እንደ ጥቁር እንጨት፣ የዕጣን ዛፍ፣ ዋርካ፣ ዛና፣ በደኖ፣ ኮመር፣ ሾላ፣ አባሎ፣ ዳርሌ፣ ባምባ እና የቆላ ዋንዛ ያሉ ዛፎች ለዘቦታ ጥበቃ /In-situ conservation/ አገልግሎት ሊውል የሚችል ቦታ

ስለሆነ ጥብቅ ስፍራ ሊሆን የሚገባው ስፍራ ነው፡፡ በተለይም በአማራ ክልል በተመሣሣይ ስርዓተ ምህዳር የዚህ ዓይነት የዕፅዋትና የደን ስብጥር በዚህ ሁኔታ ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡

ስለዚህ ይህ የተፈጥሮ ደን ተገቢው ጥበቃ እና እንክብካቤ ቢደረግለት ለዱር እንስሳት ደህንነት፣ ለስርዓተ ምህዳር ጥበቃና ለቱሪዝም ልማት ከሚሰጠው ጥቅም ባሻገር ለትምህርትና ለበርካታ ሳይንሳዊ ምርምሮች በሚኖረው አስተዋፅዖ ጥብቅ ስፍራ ሊሆን የሚገባው የተፈጥሮ ደን ነው፡፡

8.5.1. የበቶ፣ ወለቃና አባይ ሸለቆ የተፈጥሮ ደን ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም

የዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ጥበቃ ህብረት (IUCN) ለጥብቅ ስፍራነት ባስቀመጠው መስፈርት መሰረት የበቶ፣ የወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደን ጥብቅ ስፍራ እንዲሆን የሚያስችለውን ነጥቦች የሚያሟላ የተፈጥሮ ዕፅዋትና የዱር እንስሳት ማዕከል እንደሆነ በሚከተለው ሁኔታ ተዘርዝሮ ቀርቧል፡፡

1. ወካይ የሆነ ስነ ምህዳር (REPRESENTATIVENESS)

የተፈጥሮ ደኑ በልቅ ግጦሽ፣ በደን ጭፍጨፋና በእርሻ መስፋፋት እየተጎዳ ያለ ቢሆንም አካባቢው አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራና የውሃ ዳርቻ ስርዓተ-ምህዳርን እንዲሁም የአፍሮ ትሮፒካል ሃይላንድ እና የሱዳኖ ጉይና ባዮምን የሚወክል ስለሆነ በጥብቅ ስፍራነት ቢከለል በልማት ቀጠናው ቆላማ አካባቢዎችን የሚወክል ጥበቃ ቦታ ሊሆን ይችላል፡፡ ከስርዓተ-ምህዳር ውክልና በተጨማሪ ሶረኔ ቆቅ፣ ሩፔልስ ቻት፣ ብላክ ሄድድ ፎሬስት ኦሪዮል እና ክንፈ ጥቁር በቀቀን የመሳሰሉ ብርቅየ የዱር እንስሳት እንዲሁም የተለያዩ አዕዋፋትና አጥቢዎችንን ለመጠበቅ ወካይ አካባቢ ነው፡፡ የበቶ፣ ወለቃ እና አባይ ወንዝ የተፈጥሮ ደን በጣም ረጃጅምና ከፍተኛ ውፍረት ያላቸዉ ጥቁር እንጨትና ዋርካ ዛፎች ያሉበት ነዉ፡፡ ስለሆነም ተመሳሳይ ስርዓተ-ምህዳር ባላቸው ሌሎች ደኖች ከ20 ሜትር በላይ ቁመትና ከ8ሜትር በላይ መጠነ ዙሪያ ያላቸዉ ዛፎች ማግኘት አስቸጋሪ ነዉ::

2.የብዝሃ ህይወት ክምችት (DIVERSITY)

ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በውስጡ ከ25 በላይ ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት፣ ከ92 በላይ የአዕዋፍት ዝርዎች እና ከ85 በላይ የተለያዩ የዕፅዋት ዝርዎችን ያቀፈ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የግራር፣ ጥቁር እንጨት፣ ዋርካ፣ የዕጣን ዛፍ፣ በደኖ፣ ሰፋ፣ ወዘተ የመሳሰሉት ዛፎች በብዛት ይገኙበታል፡፡ አካባቢው በርካታ የብዝሃ-ህይወትንና የደረቅ ወይና ደጋውንና የቆላማውን ስርዓተ-ምህዳር ስለያዘ የድንቅየና ብርቅየ የዱር እንስሳት መናኸሪያ በመሆን ያገለግላል፡፡

ለምሳሌ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙትን

- ሶረኔ ቆቅ/*Francolinus harwoodi*/
- ሩፔልስ ቻት (Rupell's chat)
- ብላክ ሄድድ ፎሬስት ኦሪዮል (Black headed forest oriole) *የያዘ በመሆኑ፣*

3. ማራኪና ለየት ያለ የተፈጥሮ ገፅታ (DISTINCTIVENESS)

ከፍታን መሰረት ያደረገ የተያያዘ የዕፅዋት ስብጥርን በአብዛኛው የደረቅ ቆለማውንና በተወሰነ መልኩ ደግሞ የወይና ደጋ ስርዓተ-ምህዳርን አካቶ የያዘ በመሆኑ ረጃጅምና ከፍተኛ ውፍረት ባላቸዉ ዛፎችም ጭምር የተሸፈነ ነዉ፡፡ በውስጡ ለጥናትና ምርምር የሚያገለግሉ የተለያዩ ዕፅዋትንና የዱር እንስሳትን ይዟል፡፡ የአባይ ወንዝን ተከትሎ የጀልባ ትራንስፖርት ለማካሄድ ያስችላል፡፡ የአባይ፣ ወለቃ እና በቶ ወንዞችን ተከትሎ የበጋ ወቅት መዝናኛዎችን ማስፋፋትና የአካባቢውን ማህበረሰብ ከእርሻ ውጭ ገቢ እንዲፈጥሩ ያስችላል፡፡ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች (የበላይ ዘለቀ የትውልድ ቦታና የተለያዩ ገዳማት ቅርሶች) በቅርብ ርቀት መኖራቸው የበቶ፣ ወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደንን ልዩ ያደርጉታል፡፡

4. ስነ ምህዳራዊ ጠቀሜታ (ECOLOGICAL IMPORTANCE)

በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥና በአካባቢው ያለው ስርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋል ማለትም ከአካባቢው በተለየ የተሻለ የደን ሽፋን ስላለው የዝናብ ስርጭት የተስተካከለ እንዲሆን አስችሏል፡፡ ይህ አካባቢ በክልሉ ውስጥ ለመጥፋት የተቃረቡትን ጥቁር እንጨት፣ የዕጣን ዛፍ፣ ዋርካ፣ ዛና፣ በደኖ፣ ኮመር፣ ሾላ፣ አባሎ፣ ዳርሌ፣ ባምባ እና የቆላ ዋንዛ የመሳሰሉ ዕፅዋቶችን ለመጠበቅ ያስችላል፡፡ በአካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሳትና ዕፅዋት በዓይነትም ሆነ በብዛት በተፈጥሮዊ ገፅታቸው ይጠበቃሉ፡፡ ብርቅየ የዱር እንስሳትና ዕፅዋት በቦታቸው እንዲጠበቁና እንዳይጠፉ ይረዳል፡፡ የተስተካከለ የውሃ ሃብት እንዲኖር ያስችላል፡፡

5. በታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች ላይ እየደረሱ ያለ አሉታዊ ተፅዕኖዎች (DEGREE OF INTERFERENCE)

- ህገ ወጥ ደን ጭፍጨፋ
- የህገ ወጥ እርሻ መስፋፋት
- ልቅ ግጦሽ እና የደረባ ቤቶች መኖር፣
- ህገ ወጥ አደን፣
- የእርሻ ኢንቨስትመንት፣
- የአካባቢው ወጣቶች መሬት አሰጣጥ ችግር፣
- የአካባቢው ህብረተሰብ የግንዛቤ ችግር፣
- የተቀናጀ የጥበቃ ስልት አለመኖሩ፣

6. የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ሳይንሳዊ ጠቀሜታ (SCIENTIFIC AND MONITORING USES)

የዕፅዋትንና የዱር እንሰሳትን የተፈጥሮ አካባቢቸውን ለማጥናት በሞዴልነት ያገለግላል፡፡ የዱር እንስሳት በሽታ ክስተትንና በቤትና በዱር እንስሳት መካከል ያለውን ስርጭት ለማወቅ ያግዛል፡፡ ለአካባቢ ክትትል በሚኖረው ጠቀሜታ የተፈጥሮ ሚዛን ለውጥን መለካት ያስችላል፡፡ የዱር ዕፅዋት ናሙናና ተፈጥሮዊ ዕድገትንና በሰዎች ጣልቃ ገብነት የሚመጣውን ለውጥ ለማየት ያስችላል፡፡

7. የቦታ ስፋት (AREA SIZE)

ታሳቢ ጥብቅ ቦታው በጥብቅ ስፍራነት ተመዝግቦ በውስጡ ያሉትን የተፈጥሮ ሃብቶች ለመያዝ ቢያንስ 1000 ሄ/ር ስፋት ሊኖረው ይገባል የሚለውን የIUCN መስፈርት የሚያሟላና ስፋቱ ከ40000 እስከ 50000 ሄ/ር በላይ የሚሸፍን ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙትን የሶረኔ ቆቅ፣ ሩፔልስ ቻት እና ብላክ ሄድድ ፎሬስት ኦሪዮል የአዕዋፍት ዝርዎች መኖሪያ ነው። የበቶ፣ ወለቃ እና አባይ ሸለቆ ታሳቢ ጥብቅ ቦታ የበቶ፣ ወለቃና አባይ ወንዞችን ተከትሎ በሶስት ወረዳዎች (ቦረና፣ ወግዲ እና ከላላ) በ15 ቀበሌዎች ውስጥ ይገኛል።

8. ቅርፅ ወይም መጠነ ዙሪያ (SHAPE)

ጥብቅ ስፍራዎች በሚቋቋሙበት ወቅት በተቻለ መጠን ዝቅተኛ መጠነ ዙሪያ እንዲኖራቸው ይጠበቃል። ነገር ግን የበቶ፣ የወለቃ እና አባይ የተፈጥሮ ደን ወንዞችን ተከትሎ በዋይ ቅርፅ (y) በሸለቆዎች ውስጥ የሚገኘውን ወጣገባ፣ ገደላማና ተራራማ ስፍራዎችን ይዞ የሚገኝ ሲሆን ቅርጹም ሾጣጣ ሆኖ ከስፋቱ አንጻር ሲታይ ረጅም መጠነ ዙሪያ ያለው በመሆኑ ለጥበቃ እና ቁጥጥር አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። አካባቢው በአንድ ጎኑ ተራራ፣ ኮረብታ፣ ገደልና ተዳፋት የሚበዛበት፣ የዳር ድንበር ወጣገባነት የማይበዛበት እና በሌላ ጎኑ በወንዞች የተከለለ በመሆኑ በቂ የደጀን መሬት ሊኖረው የሚችል ቦታ ነው። ሆኖም አካባቢው በቀጠናው ቆላማውን አካባቢ የሚወክል ስርዓተ ምህዳር የያዘ በመሆኑና ለህዳሴው ግድብ ዘለቄታዊ ደህንነት አስተዋፅዖ የሚያድርግ በመሆኑ ጥብቅ ሰፍራ መሆን ይገባዋል።

9. በውስጡ የሚገኙ ብርቅየና ድንቅየ ዝርያዎች (ENDEMICITY)

ከታለላቅ አጥቢዎች ውስጥ አብዛኞቹ የሚገኙበት ሲሆን ከአዕዋፍት ዝርያዎች የሶረኔ ቆቅ፣ ሩፔልስ ቻት እና ብላክ ሄድድ ፎሬስት ኦሪዮል የሚገኙበት በመሆኑ ጥብቅ ስፍራ ሊሆን ይገባዋል።

8.5.2. ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚኖረው ጠቀሜታ

1. ስርዓተ ምህዳራዊ ጠቀሜታ (ECOSYSTEM VALUES)

በደኑ ውስጥና በአካባቢው ያለው ስርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋፆ ያደርጋል። በሀገራችን በማንኛውም ቦታ እንደልብ የማይገኙ እና ለመጥፋት የተቃረቡትን ጥቁር እንጨት፣ የዕጣን ዛፍ፣ ዋርካ፣ ዛና፣ በደኖ፣ ኮመር፣ ሾላ፣ አባሎ፣ ዳርሌ፣ ባምባ እና የቆላ ዋንዛ የመሳሰሉ ዕፅዋትን በዘቦታ ለመጠበቅ ያስችላል። በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ ያለው ብዝሃ ህይወት ሳይጠፋ እንዲኖር ያደርጋል። የአካባቢውን የአየር ሚዛን እንዲጠበቅ ያስችላል። የዱር እንስሳትና ዕፅዋት በቦታቸው እንዲጠበቁና እንዳይጠፉ ይረዳል።

2. ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ (ECONOMICAL VALUES)

በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ከጉብኝዎች ጋር ተያይዞ ከቱሪዝም አማራጭ ገቢዎች ለህብረተሰቡና ለመንግስት ገቢ ያስገኛል። በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ጥበቃ ሠራተኝነትና ባለሙያነት እንዲሁም

በተፈቀደ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ በመሣተፍ የአካባቢው ህብረተሰብ ቀጥተኛ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ ከምርምርና ሣይንሳዊ ጥናት እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ የአካባቢውን ገቢና አቅም ያጐለብታል፡፡ የኢኮቱሪዝም እንቅስቃሴ ስለሚስፋፋ ለአካባቢው ህብረተሰብ አንድ የገቢ ማስገኛ ምንጭ ይሆናል፡፡ የአካባቢው የአየር ሚዛን ስለሚጠበቅ ከእርሻ ስራ የሚገኘው ገቢ ዘላቂና አስተማማኝ ይሆናል፡፡ በሆቴልና አገልግሎት በመስጠት በርካታ ነዋሪዎች ኑሮአቸዉን ማሻሻል ይችላሉ፡፡ ለም አፈርን በማስቀረትና የሚከማቸውን ደለል ለማስወገድ የሚወጣውን ወጭን በመቀነስ ለታላቁ የህዳሴ ግድብ ዘለቄታዊ ጠቀሜታ አስተዋፅዖ ያደርጋል፡፡

3. ማህበራዊ ጠቀሜታ (SOCIAL VALUES)

ዓለም ዓቀፋዊና ማህበረሰባዊ የሆኑ ጠቃሚ የባህልና ልምድ ልውውጥ ይኖራል፡፡ ከታሳቢ ጥብቅ ስፍራው መቋቋም ጋር ተያይዞ የመሠረተ ልማቶች መስፋፋት ት/ቤት፣ የኢኮቱሪዝም ማህበራት መደራጀት የሰውና የእንስሳት ጤና ኬላዎች ይገነባሉ፡፡ በአካባቢው የሚገኙ ነዋሪዎች ደኑን ለመጠበቅም ሆነ በአገባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ የበቶ፣ አባይና ወለቃ ወንዞችን በማልማት፣ ለዋናና የጀልባ ጉዞ መዝናኛ እንዲውሉ ማድረግ ይቻላል፡፡

4. ሳይንሳዊ ጠቀሜታ (SCIENTIFIC VALUES)

የዱር እንስሳትና ዕፅዋትን ባሉበት ሁኔታና በተፈጥሮዊ አኗኗራቸዉ ለሚደረግ ምርምር በማዕከልነት ያገለግላል፡፡ የባህላዊ መድሃኒቶችን ደህንነት በመጠበቅና በመንከባከብ ጥቅም ላይ በማዋል ሣይንሳዊ ጥናትንም ለማካሄድ ይረዳል፡፡ በመጥፋት ላሉ የዱር እንስሳትና ዕፅዋት ላይ ሳይንሳዊ ምርምር ሊድረግ ያስችላል፡፡ የተፈጥሮ ደኑና ገጽታዉ ለከባቢያዊ ደህንነት፣ ለብዝሃ ህይወትና ለስርዓተ ምህዳር መስተካከል ያላቸዉ አስተዋፅዖ ይታወቃል በዚህ ረገድ ለሚደረጉ ምርምሮች የመስክ ላቦራቶር ሊሆን ይችላል፡፡

5. የተፈጥሮዊነት ጠቀሜታ (NATURALNESS)

ምንም እንኳን አካባቢው ከሰው ልጆች ተፅዕኖ ነጻ ባይሆንም በአንፃራዊነት ከአካባቢው የተሻለ በመሆኑ ተፈጥሮዊነትን ጠብቆ ለመቆየት ያስችላል፡፡ በውስጡ ያሉትን ብዝሃ ህይወትና ሌሎች (አፈር፣ ውሃና የመሬት አቀማመጥ) በተፈጥሮዊ ገጽታቸዉ ቆይተው ዘለቄታ ባለዉ መልክ ጥቅም እንዲሰጡና ተፈጥሮዊ ይዘታቸዉ እንዳይጓደል ይረዳል፡፡

6. የመስህብነት ጠቀሜታ (AESTHETIC VALUES)

አካባቢው በተፈጥሮዊ ይዘቱ የሰው ልጅን (የጎብኝዎችን) ቀልብ ሊስቡ የሚችሉ ማራኪ ገጽታዎች፣ እርካታ የሚሰጡ የወንዝ ዳር ምቹ መዝናኛዎችና መመልከቻ ቦታዎች ያሉት ሲሆን ከተፈጥሮዊ መስህብነቱ በተጨማሪ አካባቢው ፖለቲካዊ፣ ኃይማኖታዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ እምቅ የቱሪዝም ፖቴንሻል ሃብቶችን የያዘ ነው፡፡

8.6. የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ጠቀሜታና ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች ጥምረት ዝምድና

የበቶ፣ የወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደን ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ ቢሆን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለውና ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ ከተጠበቀ የሚሰጣቸው ጠቀሜታዎች አካባቢያዊ፣ አገራዊና ዓለማቀፋዊ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል። በተለይም ያለው የደን ሽፋንና መልካአምድራዊ አቀማመጥ የብዝሃ ህወትና ተፈጥሮዊ ገፅታ ከመጠበቅ አልፎ የዓለም ሙቀትን፣ የካርቦን ልቀትን እና የአፈር ክለትን ለመቀነስ እና የህዳሴው ግድብ በደለል እንዳይሞላ ለመጠበቅ የጎላ አስተዋፅዖ ይኖረዋል።

ስለሆነም የተፈጥሮ ደኑ ጥብቅ ስፍራ ቢሆን የሚሰጠውን ጠቀሜታ (Values) በIUCN ጥብቅ ስፍራ ለመሆን ማሟላት ከሚገባው መስፈርቶች (Quality Criteria) ጋር በማነፃፀር የቦታውን ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም መፈተሽ ያስፈልጋል። ስለዚህ ከዚህ በታች የተቀመጠው ሰንጠረዥ 6 የበቶ፣ የወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደን የሚሰጠውን ጠቀሜታ ጥብቅ ስፍራ ለመሆን ማሟላት ከሚገባው መስፈርቶች ጋር በማነፃፀር ሊጠበቅ የሚገባውን ደረጃ (Protected Area Category) ለመወሰን ያስችላል። ይህም የመመዘኛ መስፈርቶች በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ላይ ያላቸውን ጠቀሜታ ያመላክታል።

አንድ የተፈጥሮ ደን ጥብቅ ስፍራ ለመሆን ቦታው ጥብቅ ስፍራ ቢሆን የሚሰጠው ጠቀሜታ (Values) በIUCN ጥብቅ ስፍራ ለመሆን ማሟላት ከሚገባው መስፈርቶች (Quality Criteria) ጋር ሲነፃፀር ቢያንስ 75 ከመቶ በላይ ውጤት ማሳየት ይኖርበታል። ከሠንጠረዡ ላይ ማየት እንደሚቻለው ንፅፅሩ ወደ ጎንም ሆነ ወደ ታች 75 ከመቶ በላይ የሚያሳይ በመሆኑ የተፈጥሮ ደኑ ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም እንዳለው ያመላክታል።

8.7. የበቶ፣ የወለቃ እና አባይ ሸለቆ የተፈጥሮ ደን ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ የመሆን ዋና ዓላማ

የተፈጥሮ ደኑ ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ባለው የብዝሃ ህይወት ሃብት፣ ከሚሰጠው ጠቀሜታና በIUCN ጥብቅ ስፍራ ለመሆን ማሟላት ከሚገባው መስፈርቶች (Quality Criteria) አንፃር ተረጋግጧል። ይሁን እንጅ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በIUCN የጥብቅ ስፍራዎች ደረጃ (protected area category) መሰረት የትኛውን ምድብ (Protected area category I-VI) ሊያሟላ እንደሚችል እና የጥብቅ ስፍራውን የመጀመሪያ ደረጃ ዓለማዎች (Primary management objectives) መለየትና መወሰን ያስፈልጋል። ስለዚህ ለውሳኔ ያመች ዘንድ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በየትኛው ደረጃ ሊመደብ እንደሚችል ያሉ አማራጮች (possibilities) በሰንጠረዥ 7 መሰረት ተመላክቷል።

ሰንጠረዥ 6. የበቶ፣ የወለቃ እና አባይ ሸለቆ የተፈጥሮ ደን ጠቀሜታና ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም መመዘኛ መስፈርቶች ንፅፅር

	ውሳኔነት	ብዝሃ ህይወት	ልዩ መገለጫ	ኢኮሎጂያዊ ጠቀሜታ	በአካባቢው ላይ ያለ ጫና	የአካባቢው ሳይንሳዊ ጠቀሜታ	የቦታ ስፋት	ቅርፅ /መጠነ ዙሪያ/	ብርቅየና ድንቅየ ዝርያዎች	ደረጃ ከፍተኛ %
ሥነ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ	ከ	ከ[2]	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	100
የተፈጥሯዊነት ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ዝ[3]	ከ	ከ	ዝ	ከ	78
ኢኮኖሚያው ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	100
ማህበራዊ ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ዝ	89
ሳይንሳዊ ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	100
የመስህብነት ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	100
ደረጃ ከፍተኛ በ%	100	100	100	100	83	100	100	83	83	**94**

አንድ የተፈጥሮ ደን በየትኛው የጥብቅ ስፍራ ደረጃ (protected area category) **እንደሚመደብ ለመወሰን ደኑ ጥብቅ ስፍራ ቢሆን ማሳካት ያለበትን የመጀመሪያ ደረጃ ዓላማዎችን** (Primary management objective) **በመለየትና በማወቅ መሆን ይኖርበታል። ሠንጠረዥ 7 ላይ ማየት እንደሚቻለው ደኑ በደረጃ ሁለት** (protected area category II) **መሰረት ጥብቅ ስፍራ ቢሆን ከተራ ቁጥር 8 በስተቀር ሁሉንም የመጀመሪያ ደረጃ ዓላማዎች የሚያሳካ ይሆናል። ስለዚህ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን በብሄራዊ ፓርክ ደረጃ ማቋቋም ይቻላል። ይሁን እንጅ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በአሁኑ ወቅት ያሉ ፈታኝ ሁኔታዎችን ለመፍታት የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት እና ቦታው ህጋዊ ዕውቅና እስኪያገኝ ድረስ በአግባቡ ማስጠበቅ ይገባቸዋል። ስለዚህ በተፈጥሮ ደኑ ላይ እየተፈፀሙ ያሉ ችግሮችን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ እስከተቻለ ድረስ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚከተሉትን የመጀመሪያ ደረጃ ዓላማዎች** (Primary management objective) **የሚያሳካ ይሆናል።**

ለብዝሃ ህይወትና ስርዓተ ምህዳር ጥበቃ

በአኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ እና ወንዞችን ተከትለው የሚገኙ የውሃ ዳር ደኖች ስርዓተ-ምህዳር ውስጥ በሚገኘው የብዝሃ ህይወት ሃብት የዘቦታ ልማትና ጥበቃ ለማካሄድ የሚያስችል የዕጽዋትና እንሰሳት ስብጥር በማልማትና በመጠበቅ ለተተኪ ትዉልደ ማስተላለፍ፣

ሰንጠረዥ 7. Matrix for protected area categories and Management objectives (IUCN, 1994)[4]

[2] *ከ፡- ከፍተኛ 1-2 ችግሮችና የማያሟላቸዉ ነጥቦች ካሉ*

[3] *ዝ፡- ዝቅተኛ ከሁለት በላይ ችግሮችና የማያሟላቸዉ ነጥቦች ካሉ*

[4] **Note:** √=can meet Management Objectives, 0=Can't meet Management Objective

No.	Management categories	IUCN protected area categories							Total
		Ia	Ib	II	III	IV	V	VI	
		Strict natural reserve	Wilderness area	National Park	Natural Monument	Habitat/Species Management Area	Protected Landscape/Seascape	Managed Resource Protected Area	
1	Scientific research	√	√	√	√	√	√	√	
2	Wilderness protection	√	√	√	√	0	0	0	
3	Preservation of species and genetic diversity	√	√	√	√	√	√	√	
4	Maintenance of environmental services	√	√	√	0	√	√	√	
5	Protection of species, natural /culture features	0	0	√	√	√	√	√	
6	Tourism and recreation	0	√	√	√	√	√	√	
7	Education	0	0	√	√		√	√	
8	Sustainable use of resources from natural ecosystems	0	√	√	0	√	√	√	
9	Maintenance of natural/cultural/traditional attributes	0	0	0	0	0	√	√	
	Total	4	6	8	6	7	8	8	

የተፈጥሮ፣ ባህላዊና ታሪካዊ መስህቦችን በመጠበቅና በማልማት ለቱሪዝም መጠቀም

ተፈጥሮአዊና ማረኪ የሆነዉን የመሬት አቀማመጥ፣ ታሪካዊና ባህላዊ መስህቦችን በመጠበቅና በማልማት ለሰዉ ልጆች አእምሮ ማደሻ በማድረግ የመዝናኛ እድሎችን መፍጠርና ከነተፈጥሮዊ ገፅታዉ በማቆየት በውስጡ ያሉትን ተፈጥሮዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ ሃብቶች በዘለቄታዊ ቱሪዝም ልማት ጥቅም ላይ ማዋል፣

ለትምህርትና ሳይንሳዊ ምርምር

ብዝሃ ህይወትን፣ አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ ስርዓተ ምህዳርን (*Acacia-Boswellia-Commiphora* ecosystem) እና ወንዞችን ተከትለው የሚገኙ የውሃ ዳር ደኖችን (Riverine Vegetation) የሚወክል ስነ ምህዳር ለትምህርትና ምርምር ማዕከል በማድረግ በዘርፉ የሚጠበቀውን ሳይንሳዊ ዕድገት ማምጣትና የተፈጥሮ ሃብታችንን አግባብ ባለው መንገድ ማልማትና መጠቀም፣

9. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

1. **የመስክ ደንብ ልብስና ጫማ አለመኖር፡-** የተፈጥሮ ደኖችን እምቅ ሃብትና ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ለማጥናት ጊዜ ወስዶ በጫካ ውስጥ ረጅም ርቀት በእግር መጓዝን ይጠይቃል፡፡ በተጨማሪም ጥቅጥቅ ባሉ ጫካዎች ውስጥ ማለፍን ይጠይቃል፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመቋቋምና የባለሙያዎችን ደህንነት ለማረጋገጥ ለዚህ ዓይነት ስራዎች ተብለው የሚዘጋጁ አልባሳትንና ጫማዎችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ይሁን እንጅ እነዚህ የመስክ መገልገያ ቁሳቁሶች ለተቋሙ ባለመፈቀዳቸው ባለሙያዎች ለረጅም ጊዜ በተመሳሳይ የመስክ ስራዎች ወቅት ለችግር ሲጋለጡ ይስተዋላል፡፡
2. **በመንግስት ለባለሙያዎች የተፈቀደው አበል በቂ አለመሆን፡-** በአሁኑ ወቅት በኑሮ ውድነት ምክንያት ለባለሙዎች ከመንግስት በጀት የሚፈቀደው 70 ብር የቀን አበል በቂ አይደለም፡፡ ስራው በበሃሪው ጉልበትንና አቅምን የሚፈታተን በመሆኑ በበቂ ሁኔታ መመገብና ዕረፍት ማድረግን (ተመጣጣኝ አልጋ ማግኘትን) ይጠይቃል፡፡ እንደ አለመታደል ሆኖ እነዚህን ነገሮች ከሚከፈለን የቀን አበል አንፃር ማግኘት ያስቸግራል፡፡ ይህ ችግርም በስራችን ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እየፈጠረ ይገኛል፡፡
3. ***በቂ መረጃ አለማግኘት፡-*** የወለቃ፣ በቶ እና አባይ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክን ለማጥናት ስንቀሳቀስ የሁለተኛ ደረጃ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚመለከታቸውን አጋር አካላት ለማነጋገር ሞክረናል ነገርግን በአብዛኞቹ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በጉዳዩ ዙሪያ ከግንዛቤ ጀምሮ በቂ የሆነ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ከባቢያዊ ስነ ምህዳርን የሚገልጽ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በተለይም በአካባቢ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤቶች የየቀበሌዎች መሬት አጠቃቀም መረጃ ተደራጅተው ባለማግኘታችን ችግሩ ጎልቶ ይታይ ነበር፡፡

10. ወደፊት መከናወን ያለባቸው ስራዎች

በዚህ ዝርዝር ጥናት የተዳሰሱ የተፈጥሮ ደን ቦታዎችን ተፈጥሮዊና ስርዓተ ምህዳራዊ ወሳይነታቸው ሳይቀየር ጠብቆ ለማቆየትና አግባብ ባለዉ መልኩ በዘላቂነት ለማልማትና ለመጠቀም በጥብቅ ስፍራነት ተካተው እንዲከለሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህም በክልሉ መኖር ያለበትን ወሳይ ስርዓተ ምህዳር ከነበረበት 2 ከመቶ ከፍ እንዲልና በ5 ዓመቱ እውን ማድረግ ካለብን 7 ጥብቅ ስፍራዎች አንዱን እንድናሳካ የሚያደርግ ስራ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ይህ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ዳር ድንበሩ ተከልሎ በአዋጅ ህጋዊ ሰውነት የሚያገኝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ወደ ፊት መከናውን ያለባቸው ተግባራት በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፡፡

10.1. የጥናቱን ውጤት ለአጋር አካላት መላክና አስተያየት መቀበል

የዚህን ጥናት ውጤት ለቢሮዉ በማቅረብ ዝርዝር ዉጤቱን በማሳዎቅ በቢሮ ደረጃ በማጠቃለያ ሃሳቦቹ ላይ የጋራ መግባባት መፍጠርና የጥናቱን ውጤት ለሚመለከታቸዉ አካላት መላክና አስተያየት መቀበል፣

10.2. ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በየትኛው የጥብቅ ስፍራ ደረጃ (Protected Area Category) እንደሚመደብ በመጀመሪያው ጥናት ስምምነት ላይ የተደረሰበትን ውሳኔ ማጠናከር፣

የዝርዝር ጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ አካባቢው ለተፈጥሮ ጥብቅ ስፍራነት ያለውን ጠቀሜታ፣ ተስማሚውን የጥብቅ ስፍራ ደረጃ በIUCN የጥብቅ ስፍራዎች ደረጃ (Protected Area Category) መሰረት የትኛውን ምድብ (Protected Area Category I-VI) ሊያሟላ እንደሚችል በመጀወሪያው ጥናት ስምምነት ላይ የተደረሰበትን ውሳኔ ማጠናከር እና ቀጣይ ስራዎችን በፍጥነት ማከናወን፣

10.3. የክለላ ስራ ማከናወን

በመጀመሪያ ደረጃ የፖቴንሽያል የዳሰሳ ጥናት፣ በሁለተኛ ደረጃ ዝርዝር ጥናት፣ በመጨረሻም ክለላና ህጋዊ ዕውቅና ማሰጠት አንድን የተፈጥሮ ደን ወደ ጥብቅ ስፍራ ለማምጣት በቅደም ተከተል የሚከናወኑ የጥናት ስራዎች ናቸው። ይሁን እንጅ ይህ አካሄድና አሰራር ረጅም ጊዜ (ከ2 ዓመት በላይ) የሚወስድና በዳሰሳ ጥናት እና በሁለተኛ ደረጃ ዝርዝር ጥናት ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም እንዳላቸው የተለዩ አካባቢዎች በእርሻ፣ በሰፈራና በሌሎች ሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት እንድናጣቸው እያደረገ ይገኛል። ስለሆነም በሁለቱ ጥናቶች ምክንያት ረጅም ጊዜ የወሰደ በመሆኑ እና ቦታውን ሳናጣው በፍጥነት የክላላ ስራ እንዲሰራ ማድረግ፣

10.4. ሕጋዊ እውቅና ማሰጠት

በዳሰሳ፣ ዝርዝርና ክለላ ጥናቶች የተገኙትን ማጠቃለያዎች መነሻ በማድረግ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጠቀሜታዎች ለተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና ለቱሪዝም ልማት ያላቸውን አስተዋፅዖ በማረጋገጥ የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ዳር ደንበር በህግ እንዲወሰን ከዳሰሳ፣ ዝርዝርና ክለላ ስራዎች የተገኙ የማጠቃለያ ሃሳቦችን የያዘ ደጋፊ ሰነድና ረቂቅ አዋጅ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ለውሣኔ ማቅረብና ሕጋዊ ሰውነት ማሰጠት፣

10.5. የመሠረተ ልማትና የግንባታ ቦታዎችን መለየትና ግብዓት ማፈላለግ

ለጥበቃና ልማት በሚያመቸው የጥብቅ ስፍራዎች ደረጃ (IUCN Criteria for Protected Area Category (I-VI) Selection) መሰረት ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ሲከለልና በአዋጅ በጥብቅ ስፍራነት ሲቋቋም ከጽ/ቤት ግንባታ ጀምሮ ለጥበቃና ለቱሪዝም ልማት አስፈላጊ የሆኑ የመሠረተ ልማትና የግንባታ ቦታዎችን በጥናት መለየትና አስፈላጊውን ግብዓት ለማሟላት የገንዘብ ድጋፍ ማፈላለግ፣

10.6. የምክክር አውደ ጥናት/ፎረም ማዘጋጀት

በተፈጥሮ ደኑ ላይ የሚደርሰውን ጫና በተለይም ህገ ወጥ አደንን ለመከላከል በክልል፣ ዞንና ወረዳ የሚገኙ የአስተዳደር፣ ግብርና፣ ባህልና ቱሪዝም፣ አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም እና ኢንቨስትመንት የመንግስት ሴክተር መ/ቤቶች (ምስራቅ ጎጃም ዞን-እነብሴ ሳር ምድር፣ እናርጅና እናውጋ እና የሸበል በረንታ፤ ዞሮምያ ክልል/ዞን/ደራ ወረዳ፤ ሰሜን ሸዋ ዞን/ሚዳ

ኦሮሞ መራኛ፤ ደቡብ ወሎ ዞን/ቦረና፣ ወግዲ እና ከላላ) በተገኙበት ውሳኔ የሚሰጥበት እና በአጋር አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሰራርን ለመፍጠር የሚያስችል በክልል/ዞን ደረጃ ትልቅ የምክክር መድረክ ማዘጋጀት ፣

10.6. የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ፣ ተግባራትና ኃላፊነቶች መለየትና ማሳወቅ

በተለያዩ የጥናት፣ የክለላና የመሠረተ ልማት ግንባታዎች የሚመለከታቸው አጋር አካላት ማሣተፍ፣ ማሳወቅና ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ በማድረግ ዘላቂ አጋርነታቸውን ለማረጋገጥ ወቅታዊ ግንኙነትና ተግባራዊ እንቅስቀሴ ማድረግ፣

11. የጉዳዩ ቀጥተኛ ባለቤቶችና የባለድርሻ አካላት ተግባራትና ኃላፊነት ትንተና

ከላይ በዝርዝር የተቀመጡና ወደፊት መከናወን ያለባቸው ሌሎች አስፈላጊ ስራዎችን ለማሳካት የጉዳዩ ቀጥተኛ ባለቤቶችና ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን ተግባርና ኃላፊነት በተፈለገዉ መጠን መወጣት ይኖረባቸዋል፡፡ ስለዚህ ከላይ በዝርዝር ለተቀመጡና ወደ ፊት መስራት ላለባቸው ስራዎች ወሳኝና አጋር ናቸው ተብለው የተመረጡ ባለድርሻ አካላትና የጉዳዩ ቀጥተኛ ባለቤቶች ተግባርና ኃለፊነት ተለይተው እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፡፡

11.1. ክልል፣ ዞን እና ወረዳ ባህልና ቱሪዝም

በአዋጅ በተሠጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት በቢሮው ለስራዉ ቀጥተኛና ተጠሪነት ያለዉ የዱር እንሰሳት ጥናት፣ ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የስራ ሂደት በዋናነት ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6 የተዘረዘሩ ወደ ፊት መከናወን ያለባቸውን ተግባራት ኃላፊነት ወስዶ ማስፈፀም አለበት፡፡

- ❖ የጥናቱን ውጤት ለአጋር አካላት መላክና አስተያየት መቀበል፣
- ❖ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በየትኛው የጥብቅ ስፍራ ደረጃ (protected area category) እንደሚመደብ መወሰን (ክልል)፣
- ❖ በተፈጥሮ ሃብቱ ላይ አሉታዊ ስጋቶች ከተወገዱ በኋላ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የክለላ ስራ መስራት፣
- ❖ ከቀበሌ አመራር አከላት ጋር በመሆን ለአካባቢው ማህበረሰብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት (ዞንና ወረዳ)፣
- ❖ ከክለላ ስራ በኋላ የተፈጥሮ ደኑ በአዋጅ ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኝ ማስቻል (ክልል)፣
- ❖ የመሠረተ ልማትና የግንባታ ቦታዎችን መለየትና ግብዓት ማፈላለግ፣
- ❖ የምክክር አውደ ጥናት/ፎረም ማዛጋጀት

11.2. ዞንና ወረዳ መስተዳደር

ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ የዳር ድንበር ክላለ ተሰርቶለት ህጋዊ ሰውነት እስኪያገኝ ድረስ፡-

- በአሁኑ ወቅት በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ውስጥ እየተፈፀሙ ባሉ ችግሮች ዙሪያ በየደረጃው ከሚመለከታቸዉ አመራርና ፈጻሚ አካላት ጋር በመወያየት ከወዲሁ መፍትሄ ማፈላለግ እና የቀበሌ አመራሮችንና ማህበረሰቡን የማሳመን ስራ መስራት፣
- በወግዲ ወረዳ በወለቃና አባይ ወንዞችን ተከትለው ከሚገኙ የደን አካባቢዎች መካከል አጋማይት፣ አቡ ጠንጠቃ፣ ደድሃሬ፣ ጠማሜ፣ መጋጠሚያ፣ ሰንበቶ፣ ዲዳ ዋጮ፣ ቀዋ ዳባ የመሳሰሉ ቦታዎች ለኢንቨስትመንት ሊውሉ እና ለወጣቶች ሊሰጡ የተጠኑ መሆኑ ይታወሳል፡፡ በቦረና ወረዳ የአምዴ፣ ጨዬ፣ ንፋሴ፣ ፈሪ መቆሚያ፣ አጋዘን መፎገሪያ እና ሁዳድ አካበቢዎች ህገ ወጥ እርሻ በስፋት ከሚታይባቸው ቦታዎች ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ በከላላ ወረዳ ደግሞ የቱሉ ጅሌ፣ አገዩና ሚራቱ ደኖች ከፍተኛ የእርሻ መስፋፋት የሚታይባቸው አካባቢዎች ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ እነዚህ የደን ቦታዎች በውስጣቸው በሀገራችን በማንኛውም ቦታ እንደልብ የማይገኙና ለመጥፋት የተቃረቡ እንደ ጥቁር እንጨት፣ የቆላ ዋንዛ፣ ኮመር፣ የዕጣን ዛፍ፣ ዛና፣ በደኖ፣ ዋርካና ባምባ ያሉ ዕፅዋቶችን የያዙ ስለሆነና አነዚህን ዕፅዋቶች ለዘቦታ ጥበቃ In-situ Conservation) ተፈጥሮዊ ቦታ በመሆኑ ቦታዎቹ ለኢንቨስትመንት እርሻ፣ ለዕጣንና ሙጫ ምርት እንዳይውሉ እና ህገወጥ እርሻ እንዳይስፋፋ ክልከላ ማድረግ እንዲሁም በክልሉና በዞኑ በኩል የኢንቨስትመንት ፍቃድ እንዳይሰጥ አስፈላጊውን ግፊት ማድረግ፣
- የክለላው ስራ እስኪጠናቀቅ በደኑ አዋሳኝ በሆኑ ቀበሌዎች የሚኖሩ የቀበሌ አመራሮች በቅንጅት የተፈጥሮ ደኑን ለመጠበቅ በጥበቃ ስራው ላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ አቅጣጫ መስጠትና አፈፃጸሙን መከታተል፣
- የክልላው ስራ እስኪከናወን በየቀበሌው የተቋቋሙ የደን ግብረ ኃይሎችንና ሚሊሻዎችን (ጉጅሌዎችን) በመጠቀም የተጠናከረ ጥበቃና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች እንዲካሄዱ ማስተባበር፣
- የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩን ህልውና ለመታደግ በቀጣይ በጀት ዓመት አስፈላጊውን በጀት በማፈላለግ ጊዜዊ የጥበቃ ሰራተኞችን በመቅጠር የጥበቃ ስራውን ማጠናከር፣ ማስተባበርና አፈፃጸሙን መከታተል፣
- በአጎራባች ቀበሌዎች ያለው የመሬት አጠቃቀም በውል ስለማይታወቅ እና የታሳቢ ፓርኩ ክለላ ሲካሄድ አስቸጋሪ ሁኔታ ስለሚፈጥር በተለይም የእርሻ፣ የግጦሽ እና የደን ቦታዎችን የመለየት ስራ እንዲሰራ ማስተባበር/ማመቻቸት (ወረዳ)፣

11.3. ክልል፣ ዞንና ወረዳ ግብርና

ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ የዳር ድንበር ክላለ ተሰርቶለት ህጋዊ ሰውነት እስኪያገኝ ድረስ፡-

- በአጎራባች ቀበሌዎች አካባቢ የሚገኙ የቤት እንስሳት ዝርያዎችን በማሻሻል ቁጥራቸውን መቀነስ እና ዘመናዊ የቤት እንስሳት እርባታ ዘዴዎችን ማስፋፋት (ወረዳ)፣
    - ዝርያዎችን ማሻሻል፣
    - መኖ ማልማት፣

- እንስሳት ጤና ጥበቃ፣
- ዘመናዊ ቀፎ
- ግባዕት አቅርቦት፣
- ዓሳ እርባታ፣

❖ በየቀበሌዎች የተቋቋሙ የደን ግብረ ኃይሎችን ማጠናከርና ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ (ወረዳ)፣

❖ በአጎራባች ቀበሌዎች የደን ልማት ስራ በስፋት ማካሄድ (ወረዳ)፣

❖ በአጎራባች ቀበሌዎች የእርሻና የግጦሽ መሬቶችን ምርታማነት ማሳደግ (ወረዳ)፣

❖ ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በመሆን የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት (ወረዳ)፣

❖ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራውና በውስጡ የሚኖሩ የዱር እንስሳት ሁኔታና ያሉበት ደረጃ በደን ግብረኃይል እየተገመገመ በየጊዜው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ፣ ለዚህ ደግሞ የወረዳውን የደን ግብረ ኃይል በሰው ኃይል፣ በማቴሪያልና ገንዘብ ማጠናከርና መደገፍ፣

11.3. ዞንና ወረዳ አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም

ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የዳር ድንበር ክለላ ተሰርቶሎት ህጋዊ ሰውነት እስኪያገኝ ድረስ፡

❖ መስል የተፈጥሮ ደኖች አጠቃቀምን የመከታተል ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ የሚደረገውን የእርሻ መስፋፋት ለመቆጣጠር በደኑ ውስጥና ዙሪያ ያሉ ህጋዊና ህጋዊ ያልሆኑ እንዲሁም የወል መሬቶች በአግባቡ ለይቶ መመዝገብ፣ የወል መሬቶች እንዳይታረሱ መከልከል እና የድንበር ውዝግቦች እንዳይፈጠሩ የደኑን ዳር ድንበር፣ ስፋትና ሽፋን መለየትና ካርታ ማንሳት፣

❖ በአጎራባች ቀበሌዎች ያለው የመሬት አጠቃቀም በውል ስለማይታወቅ እና የታሳቢ ፓርኩ ክለላ ሲካሄድ አስቸጋሪ ሁኔታ ስለሚፈጥር በተለይም የእርሻ፣ የግጦሽ እና የደን ቦታዎችን የመለየት ስራ እንዲሰራ ማድረግ (ወረዳ)፣

❖ የበቶ፣ ወለቃና አባይ ሸለቆ የተፈጥሮ ደኖች ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ውስጥ ለኢንቨስትመንት ምቹ የሆኑ አካባቢዎች የተጠኑና ጥያቄም የቀረበባቸው ስፍራዎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጅ እነዚህ አካባቢዎች ብርቅየና የትም ቦታ የማይገኙና ለመጥፋት የተቃረቡ የብዝሃ ህይወት ሃብቶች ተፈጥሮዊ መኖሪያና መራቢያ በመሆናቸው ልዩ ጥበቃ የሚስፈልጋቸው ናቸው፡፡ ስለዚህ ቦታው ለኢንቨስትመንት ተግባር ከሚውል ይልቅ ለብዝሃ ህይወት ሃብቶች ጥበቃ አገልግሎት ቢውል የበለጠ ጠቀሜታ ስላለው ክልከላ ማድረግና ለኢንቨስትመንት ለመስጠት በሂደት ላይ ያሉ ካሉም ፍቃድ አሰጣጡን ማስቆም፣

❖ የአጎራባች ቀበሌ አማራሮችና ህብረተሰቡን በማስተባበርና አቅጣጫ በመስጠት ደኑ በትብብርና በህበረት እየተጠበቀ እንዲቆይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት (ወረዳ)፣

- በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ የሚካሄዱ ህገወጥ የእርሻ መስፋፋት፣ ደን ጭፍጨፋ፣ መንደር ግንባታ፣ ወዘተ የመሳሰሉ ህገ ወጥ ተግባራትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በበደኑ አካባቢ የሚገኘውን ህብረተሰብ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካለት ጋር በመሆን ማስተማርና ለጥበቃ ስራው ተሣትፎ እንዲያደርግ ማበረታታት፣ ህገወጦችን በመከታተል ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ማስወሰን፣
- በት/ቤቶች የአካባቢ እንክብካቤ ክበባት እንዲስፋፉ፣ እንዲጠናከሩና ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ (ወረዳ)፣
- የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ማካሄድ (ዞንና ወረዳ)፣

11.4. ወረዳ አስተዳደር ፀጥታ (ፖሊስና ሚሊሻ)

- በክለላ ስራው ወቅት አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ፣
- በተፈጥሮ ደኑና በአካባቢው የሚፈፀሙ ህገውጥ የተፈጥሮ ሃብት ውድመት (ህገወጥ አደን፣ ልቅ ግጦሽ፣ ደን ጭፍጨፋ፣ ህገወጥ እርሻ፣ ከሰል ማክሰል) መከላከልና መቆጣጠር፣
- ለግጦሽ ከተለያዩ አካባቢዎች (ኦሮምያ ክልል፣ ሰሜን ሸዋ ዞን እና ምስራቅ ጎጃም ዞን) የሚመጡ እንስሳትን መከላከል፣

11.5. ወረዳ ፍትህ

- በአጎራባች ቀበሌዎች ለሚገኘው ማህበረሰብ የንቃተ ህግ ትምህርት መስጠት፣
- በተፈጥሮ ደኑና አካባቢው በሚገኘው የተፈጥሮ ሃብት ላይ ህገ ወጥ ድርጊት (ህገወጥ አደን፣ ልቅ ግጦሽ፣ ደን ጭፍጨፋ፣ ህገወጥ እርሻ፣ ከሰል ማክሰል) የሚፈፅሙ ግለሰቦች ፈጣንና አስተማሪ የሆነ ውሳኔ ማሰጠት፣
- 11.6. ወረዳ ውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጅ
- ማገዶ ቆጣቢ ምድጃና አማራጭ የኃይል ምንጮችን አጠቃቀምን ማስፋፋት፣
- ንፁህ የመጠጥ ውሃ ለሰውና ለእንስሳት በስፋት ማድረስ፣

12. ማጠቃለያ

በዚህ ዝርዝር ጥናት በደቡብ ወሎ ዞን በከላላ ወረዳ በ3 ቀበሌዎች፣ በወግዲ ወረዳ በ11 ቀበሌዎች እንዲሁም በቦረና ወረዳ በ1 ቀበሌ ውስጥ የሚገኘውን የበቶ፣ የወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደን ታሰቢ ብሄራዊ ፓርክ ዝርዝር ጥናት ተካሂዷል። በጥናቱም፡-

- ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ ስርዓተ ምህዳርን እና የውሃ ዳር ደኖችን ስነ ምህዳር የሚወክል ያልተቆራረጠ ደን የያዘ ሲሆን በውስጡ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ፣ ለመጥፋ የተቃረቡና ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው የብዝሃ ህይወት ሃብቶች እንደሚገኙበት ታውቋል።

- ከ25 በላይ የአጥቢ የዱር እንስሳት ዝርያዎች፣ ከ91 በላይ የአእዋፋት ዝርያዎች፣ ከ85 በላይ የዕፅዋት ዝርያዎች፣ 3 የዓሳ ዝርያዎች፣ ከ4 በላይ የተሳቢ እና ተራማጅ ዝርያዎች ተመዝግበዋል።

❖ የበቶ፣ የወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደን ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ በዙሪያው ከሚገኙ ተፈጥሮዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ መሰህቦች ጋር በመሆን ለብዝሃ ህይወት ጥበቃ፣ ለትምህርትና ሳይንሳዊ ምርምር እና ለቱሪዝም ልማት ሊውል የሚችል ተፈጥሮዊ የመስህብ ቦታ እንደሆነ ማረጋገጥ ተችሏል፣

❖ በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ውስጥና ውጭ የሚገኙ ተፈጥሮዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ ሃብቶች ተለይተዋል፣

ታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን ለመከለልና በብሄራዊ ፓርክነት ለማቋቋም ወደፊት የሚከናወኑ ተግባራትና ከዚህ አንፃር የአጋር አካላት ድርሻና የሚያከናውኗቸው ተግባራት ተለይተዋል፣

13. ዋቢ መጽሐፍት (References)

1. Azene Bekele Tesema (1993). Useful Trees and Shrubs for Ethiopia: Identification, Propagation and World Agroforestry Center, RELMA, ICRAF Eastern Africa Region, Nairobi, Kenya .
2. Azene Bekele Tesema (2007). Useful Trees and Shrubs for Ethiopia: Identification, Propagation and Management for 17 agroclimatic zones. World Agroforestry Center, RELMA, ICRAF Eastern Africa Region, Nairobi, Kenya.
3. Abate Shiferaw (2010). An Appraisal of the challenges that affect sustainability and productivity of the land use in the Borena woreda of south Woll Highlands: Ethiopia
4. W/Michael Kelecha (1987). A glossary of Ethiopian plant names 4th edition Addis Ababa, Ethiopia.
5. FAO of UN (1984). Vegetation and Natural region and their significance for land use planning: report paper for the government of Ethiopia, United Nations development program, technical report 4. AG: DP/ETH178/0031 Rome Italy.
6. IUCN (1994). The IUCN Guideline for protected area management categories.
7. IUCN (1996). Managing protected area in the tropics.
8. John G.Williams and N. Arlott, (1980). A field Guide to the birds of East Africa. Collins St James place, London.
9. Kumera Wkjira and Zelalem Tefera (eds) (2005). Wildlife Management. Parks Development and protection Authority: Compendium of notes on wildlife conservation and Management A training manual for park management and project experts, Bahir dar, Ethiopia.
10. Chane Gebeyehu (2000). Land Use and Spatial Distribution of Two Gum and Incense producing Tree Species. A Thesis Submitted in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Master of Science in Range Management in the Faculty of Agriculture University of Nairobi. Wogidi, Ethiopia.

11. ሰለሞን ይርጋ (2000) አጥቢዎች አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
12. የአብክመ ፓርኮች ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን (1998) የደንቆሮ ጫካ የዳር ድንበር ክለላ ሪፖርት፣ ባህር ዳር፣ ኢትዮጵያ
13. የአብክመ ፓርኮች ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን (1999) የአባይ ሸለቆ የተፈጥሮ ጥብቅ ሥፍራ የመሆን አቅምን ለማረጋገጥ የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት፣ ባህር ዳር፣ ኢትዮጵያ
14. የአብክመ ፓርኮች ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን (2001) የባኩሳ ማሪያምን የተፈጥሮ ደን ጥብቅ ሥፍራ የመሆን አቅም ለማረጋገጥ የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት፣ ባህር ዳር፣ ኢትዮጵያ
15. የአብክመ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ (2002) የወፍ ዋሻ ጥብቅ የመንግስት ደን ጥብቅ ሥፍራ የመሆን አቅም ለማረጋገጥ የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት፣ ባህር ዳር፣ ኢትዮጵያ
16. የአብክመ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ (2003) ወለቃና አባይ ሸለቆ የተፈጥሮ ደን ጥብቅ ሥፍራ የመሆን አቅም ለማረጋገጥ የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት፣ ባህር ዳር፣ ኢትዮጵያ
17. በአብክመ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የመካከለኛው አማራ የልማት ቀጠና (2001) ተፋሰስንና የውሃ ሃብትን መሰረት ያደረገ የስድስት ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ (2002-2007)፣ ባህርዳር፣ ኢትዮጵያ
18. ከበደ ታደሰ (2000) የኢትዮጵያ መካከለኛው ስምጥ ሸለቆ ወፎች የኪስ መፅሐፍ፣

ዕዝል 1. የተመዘገቡ ዋና ዋና እፅዋት መረጃ

No	Vernacular Name	Scientific Name	Remark
1.	ባዝራ ግራር	*Acacia abyssinica*	
2.	ደሬ	*Acacia lahai*	
3.	ሽፈሬ/ችፈሬ	*Acacia albida*	
4.	ግርማዳ	*Acacia polycantha*	
5.	ቆንጥር/ጅበ ቆንጥጥ	*Acacia Senegal*	
6.	ዋጫ ግራር	*Acacia seyal*	
7.	ጠያቻ	*Acacia tortolis*	
8.	ነጭ ግራር	*Acacia sieberiana*	
9.	ቃጫ	*Agave sisalana*	
10.	እሬት/አልጌ	*Aloe spp*	
11.	ሸምበቆ	*Arundo donax*	
12.	የሴት ቀስት	*Asparagus aethiopicus*	
13.	ደሞ (በደኖ)	*Balanites aegyptiaca*	
14.	የሴት አፍ	*Berberis holstii*	
15.	ዘማት/ጅብጃባ	*Berchemia discolor*	
16.	ቀረሪ/የጣን ዛፍ/የአድሩስ እንጨት	*Boswellia popyrifera*	
17.	ጦቢያ/ቅምጣ	*Calotropis procera*	
18.	ጉመሮ	*Capparis tomentosa*	
19.	አጋም	*Carssa sapinarum*	
20.	ጉፋያ/ጉፋ	*Cassia singueana*	
21.	ጉፍያ	*Cassia singueana*	ቁጥቋጦ

No	Vernacular Name	Scientific Name	Remark
22.	ጫሪያ (ቃውት)	*Celtis kraussiana*	
23.	ዝንፉቅ	*Combretum aculeatum*	
24.	አቫሎ	*Combretum molle*	
25.	አንቋ /ከርቤ	*Commiphora africana*	
26.	አንቃ/ሃንቃ	*Commiphora habessinica*	
27.	የቆላ ፍየለ ፈጅ	*Croton dichogamum*	
28.	ሉቂ/እልብ/የጅብ ምርኩዝ	*Cussonia hoistii*	
29.	አስተናግር	*Datura stramonium*	አረም
30.	አደር	*Dichrostachys cinerea*	
31.	ክትክታ	*Dodonaea viscosa*	
32.	ሰምዐ/ሎል	*Ekebergia capensis*	
33.	ኮርች/ቁራ	*Erythina abysinica*	
34.	ደደሆ	*Euclea schimperi*	
35.	ቁልቋል	Euphorbia abyssinica	
36.	ቅንጭብ	*Euphorbia tirucalli*	
37.	ልጎ/በለስ/ቆለቆል/ባህር መዝ	*Ficus carica*	
38.	አቧራ (ባቧ)	*Ficus gnaphalocarpa*	
39.	ሾላ	*Ficus sur*	
40.	መዳሌ/ቧቧ/ባንባ	*Ficus sycomorus*	
41.	ችብሃ	*Ficus thonningii*	
42.	ዋርካ	*Ficus vasta*	
43.	ጭቅላል	*Flueggia virosa*	
44.	ጥፍሬና	*Gomphocarpus fruticosus*	
45.	ሰፋ/ሱማያ/በትረ መሴ	*Grewia bicolor*	
46.	ችርንችር	*Grewiwa ferruginea*	
47.	ለንቋጣ	*Grewiwa villosa*	
48.	ቋንጫ	*Hibiscus micranthus*	
49.	ቂልንጦ/ምሳር ገንፎ/	*Ilex mitis*	
50.	አጣጥ	*Maytenus ovatus*	
51.	ኩምበል	*Maytenus undata*	
52.	እሸ	*Mimusops kummel*	
53.	ቀረጥ/ጭረት	Osyris quadripartita	
54.	ጥንጁት	*Otostegia integrifolia*	
55.	የቆላ ዋንዛ/ጨው ዋንዛ	*Piliostigma thonningii*	
56.	ጥቁር አንጨት/ቡትጅ	*Prunus africanus*	
57.	ቀንጠፋ	*Pterlobium stellatum*	
58.	ጣጤሳ/ጣኩማ	*Rhus natalesis*	
59.	ትለም	*Rhus retinorrhoea*	
60.	እንጆሪ	*Rubus pinnatus*	
61.	አለልቱ/ካያ/አካያ/ወንዝ አድምቅ	*Salix subserrata*	
62.	የቆላ ችፍርግ	*Sida ovata*	
63.	ዶቅማ	*Sizygium guineese*	
64.	ስምንት ልብ/ዳርሌ	*Sterculia Africana*	
65.	ዋሽንት/ዛና	*Stereosprmum kunthianum*	
66.	አቀራሮ/መረንዝ	*Strychnos innocua*	
67.	ቀጠጥና	*Verbascum sinaticum*	
68.	አለሌ/ሃለሌ/ዞግዶም	*Warburgia ugandensis*	
69.	እንካይ	*Ximenia americana*	
70.	ፎጭ	*Ziziphus mucronata*	

No	Vernacular Name	Scientific Name	Remark
71.	ጋቫ/ገበያ/ቁርቁራ	*Ziziphus spp.*	
72.	ቋንቋ		
73.	አርጡማ/ባርጨሜ/ሸግት		የፊረንጂ ዕድ የሚመስል
74.	ኮኖ		ፍሬው የሚበላ
75.	እንጠጢ		
76.	ቋቋቴ		
77.	አለንጫቆ		
78.	አሲንባሮ		
79.	ሌባ ገመድ		
80.	ደሚት		
81.	ቆሌ		
82.	ውጣጤ		
83.	ለዲ		
84.	ልቅሜ		
85.	ሶቢላ		ቀፎ ማጠኛ/ቁጥቋጦ
86.	ቀንጦ		ለጭስ የሚያገለግል
87.	አብሾ/ጨጎጊት		አረም
88.	ደርሶ ቦግ		አረም
89.	ዝንጀሮ/ሶቢላ		
90.	ቁጢማ		ሣር
91.	የቆቅ ሳር		
92.	ሰርዶ		
93.	እግጫ		
94.	ጎመጭ		
95.	ቃምቢል		
96.	ወይጫ		
97.	የውሻ ለንደዶ		
98.	ዋንጋ		
99.	ሚጨራ		
100.	ሉት		
101.	ገታ		
102.	የአንበጣ አር		አረም
103.	የሽኮኮ ጎመን		አረም
104.	ባንዳ		አረም
105.	ነጭላ		አረም
106.	ኩርንችት		አረም
107.	ዝሪንጥ		አረም
108.	አሉማ/አልማ		አረም
109.	እንሱ-ሰረጢጥ		አረም
110.	ነጨጭላ		አረም

ዕዝል 2. የተመዘገቡ ዋና ዋና የአዕዋፍት ዝርያዎች መረጃ

No	Common Name	Scientific name	Amharic Name	Remark
1.	Abyssinian Black-winged Lovebird	*Agapornis taranta*	ክንፈ ጥቁር በቀቀን	C & A07
2.	Abyssinian ground hornbill	*Bucorvus abyssinicus*	እርኩም	*B*

No	Common Name	Scientific name	Amharic Name	Remark
3.	Abyssinian roller	*Coracias abyssinica*		*B*
4.	African firefinch	*Lagonosticta rubricata*	ቀይ ድንቢጥ	*B*
5.	African fish eagle	*Haliaeetus vocifer*	አሳ አዳኝ ንስር	C
6.	African hoopoe	*Upupa epops africana*	ጁንጁላቴ	*B*
7.	African mourning dove	*Streptopelia decipiens*	ሐዘንተኛ ዋኔ	C
8.	African scimitarbill	*Phoeniculus minor*		B
9.	African grey hornbill	*Tockus nasutus*		C
10.	Augur buzzard	*Bueto rufofuscus*		*B*
11.	Baglafecht weaver	*Ploceus baglafecht*		A & A07
12.	Black-headed Oriole	*Oriolus larvatus*		C
13.	Black-throated Firefinch	*Lagonosticta larvata*		A & A04
14.	Blue-eared Glossy-starling	*Lamprotornis chalybaeus*	ሰማያዊ ጆሮ ዋርዳ	C
15.	Blue-naped Mousebird	*Urocolius macrourus*	ገፀ ቀይ ሞገጥ ወፍ	C
16.	Bush petronia	*Petronia dentata*		A & A04
17.	Cape rook	*Carvus capensis*		B
18.	Carmine bee-eater	*Merops nubicus*		*B*
19.	Cattle egret	*Ardeola ibis*	የወንዝ ሳቢሳ	*B*
20.	Chestnut sparrow	*Passer eminibey*		C
21.	Chestnut-crowned Sparrow-weaver	*Plocepasser superciliosus*		A & A04
22.	Cinnamon-chested bee-eater	*Merops oreobates*	ደረተ ወይባ ንበበል ወፍ	C
23.	Drongo	*Dicrurus adsimilis*		*B*
24.	Dusky turtled dove	*Streptopelia lugens*		A & A07
25.	Eastern Yellow-billed Hornbill	*Tockus flavirostris*		C & A08
26.	Egyptian goose	*Alopchen aegyptiaca*	አይነ ቀይ ዝይ	*B*
27.	Egyptian plover	*Pluvianus aegyptius*		B
28.	Erckel's francolin	*Francolinus erckelii*		ABC & A07
29.	Fan-tailed Raven	*Corvus rhipidurus*	ድንክዬ ቁራ	C
30.	Fischer's starling	*Spreo fischeri*		B
31.	Fox kestrel	*Falco aplex*		A & A04
32.	Foxy cisticola	*Cisticola troglodytes*		A & A04
33.	Giant king fisher	*Ceryle maxima*		*B*
34.	Golden breasted starling	*Cosmopsarus regius*		B
35.	Great white egret	*Egretta alba*	ታላቋ ሳቢሳ	C
36.	Greater honey guide	*Indicator indicator*		*B*
37.	Grey heron	*Ardea cinerea*	ግራጫ ሽመላ	B
38.	Grey-headed Kingfisher	*Halcyon leucocephala*		C
39.	Hamerkop	*Scopus umbretta*	የወንዝ አመቴ	*B*
40.	Harwood francolin	*Francolinus harwoodi*		ABC & A07
41.	Hooded vulture	*Necrosyrtes monachus*	አፍሮ አይገባ/ጆፌ አሞራ	C
42.	Laughing dove	*Streptopelia senegalensis*	አንግተ ፍንጥቅ ዋኔ	*B*
43.	Lesser honey guide	*Indicator minor*		*B*
44.	Little egret	*Egretta garzetta*	ትንሹ ሳቢሳ	C
45.	Little Rock-thrush	*Monticola rufocinereus*		A & A07
46.	Long-crested eagle	*Lophaetus occipitalis*	ባለቁንጮ ንስር	*B*
47.	Montane White-eye	*Zosterops poliogaster*		A & A07
48.	Northern White-crowned Shrike	*Eurocephalus rueppelli*		C
49.	Nyanza swift	*Apus niansae*		A & A07

No	Common Name	Scientific name	Amharic Name	Remark
50.	Oriole finch	*Linurgus olivaceus*		C
51.	Pale chanting goshawk	*Melierax poliopterus*		D & A08
52.	Paradise whydah	*Steganura paradisaea*		C
53.	Pied crow	*Carvus albus*	ጥቁርና ነጭ ቁራ	B
54.	Pied kingfisher	*Ceryle rudis*	ጥቁርና ነጭ አሳ አመቱ	*B*
55.	Pin-tailed-whydah	*Vidua macroura*		*B*
56.	Red bishop	*Euplectes orix*	ቀይ የመስቀል ወፍ	C
57.	Red checked cordon-bleu	*Uraeginthus bengalus*	ሰማያዊ ድንቢጥ	*B*
58.	Red-billed firefinch	*Lagonosticta senegala*	መንቆረ ቀይ ድንቢጥ	*B*
59.	Red-billed hornbill	*Tockus erythrochynchus*	መንቆረ ቀይ ሾለቅ	*B*
60.	Red-billed Oxpecker	*Buphagus erythrorhynchus*	ምንቆረ ቀይ ጭሪ	C
61.	Red-headed Bluebill	*Spermophaga ruficapilla*		C
62.	Red-winged Pytilia	*Pytilia phoenicoptera*		A & A04
63.	Red-winged Starling	*Onychognathus morio*		C
64.	Ring-necked Dove	*Streptopelia capicola*		C
65.	Rueppell's Robin-chat	*Cossypha semirufa*		A & A07
66.	Ruppell's Black Chat	*Myrmecocichla melaena*		A /C & A07
67.	Ruppelss's long-tailed starling	*Lamprotornis purpuropterus*	ጅራተ ረጅም ዋርዳ	*B*
68.	Sacred ibis	*Threskiornis aethiopicus*	ቅዱስ ጋጋኖ	C
69.	Schalow's wheatear	*Oenanthe lugubris*		C
70.	Senegal coucal	*Centropus senegalensis*		C
71.	Speckled pigeon	*Columba guinea*	ባለ ቀይ ቀለበተ አይን ርግብ	*B*
72.	Spectacled weaver	*Ploceus ocularis*		C
73.	Spur winged plover	*Vanellus spinosus*	ጥቁርና ነጭ ኩልሊት	B
74.	Squacco heron	*Ardeola ralloides*		C
75.	Streaky seedeater	*Serinus striolatus*		C & A07
76.	Swainson's sparrow	*Passer swainsonii*		ABC & A07
77.	Tacazze sunbird	*Nectarinia tacazze*		C & A07
78.	Tawny eagle	*Aquila rapox*	ቀይ ንስር	*B*
79.	Temminck's courser	*Cursorius temminckii*		C
80.	The Black-crowned Night Heron	*Nycticorax nycticorax*		C
81.	Three-banded plover	*Charadrius tricollaris*		C
82.	Tropical boubou	*Laniarius aethiopicus*	የትሮፒክስ ሹሻይ	B
83.	Vulturine guinea fowl	*Acryllium vulturinum*		B
84.	White headed vulture	*Trigonoceps occipitalis*		B
85.	White-backed Vulture	*Gyps africanus*		C
86.	White-billed Starling	*Onychognathus albirostris*		A& A07
87.	White-black backed Tit	*Parus leuconotus*		A & A07
88.	White-winged Cliff-Chat	*Thamnolaea semirufa*		A/C & A07
89.	Wire-tailed swallow	*Hirundo daurica*		*B*
90.	Woolly-necked stork	*Cieonia episcopus*	አንገተ ጥጥ ራሣ	*B*
91.	Yellow-billed Stork	*Mycteria ibis*	መንቆረ ቢጫ ራሣ	C
92.	Yellow-rumped Serin	*Serinus xanthopygius*		A & A07

Note:

A= IBA (important Bird Area) recorded in 1996 and categorized as R3 Biome

B=Observation during the fieldwork (2010)

C=Observation during the fieldwork (2012)
D= Recent observation by locals
A04= Sudan-Guinea Savanna Biome Restricted species
A07= Afrotropical Highland Biome Restricted species
A08=Somali-Masai Biome Restricted species

ዕዝል 3. የተመዘገቡ ዋና ዋና የአጥቢ እንስሳት ዝርያዎች መረጃ

No	Common name	Scientific Name	Coservation Status	Remark
1.	Common/Golden Jackal	*Canis aureus*	LR/lc	A
2.	Black backed jackal	*Canis mesomelas*	LR/lc	B
3.	Caracal	*Caracal caracal*	LR/lc	A
4.	Vervet monkey	*Cercopithecus aethiops*	DD	A
5.	Abyssinian colobus	*Colobus guereza*	LR/lc	A
6.	Spotted Hyena	*Crocuta crocuta*	LR/lc	A
7.	Serval Cat	*Felis serval*	LR/lc	A
8.	African wildcat	*Felis silvestris*	LR/lc	A
9.	Stripped hyena	*Hyaena hyaena*	LR/nt	A
10.	Porcupine	*Hystrix cristata*	LR/nt	A
11.	Common hare	*Lepus timidus*	LR/lc	A
12.	Honey Badger/Ratel	*Mellivora capensis*	V	A
13.	Klipspringer	*Oreotragus oreotragus*	LR/lc	A
14.	Aardvark	*Orycteropus afer*	EN	A
15.	Oribi	*Ourebia ourebi*	LR/cd	A
16.	Leopard	*Panthera pardus*	LR/lc	A
17.	Anubis baboon	*Papio Anubis*	LR/cd	A
18.	Common warthog	*Phacochoerus aethiopicus*	LR/lc	A
19.	Rock Hyrax	*Procavia capensis*	LR/lc	A
20.	Wild pig	*Sus scrofa*	LR/lc	A
21.	Common duiker	*Sylvicapra grimmia*	LR/lc	A
22.	Common bushbuck	*Tragelaphus scriptus*	LR/lc	A
23.	Mole rat	NI		A
24.	Tree Squirrel species	NI		A
25.	Bat species	NI		A
26.	Crocodile	NI		A
27.	Monitor Lizard	NI		A
28.	Python	NI		A
29.	Snakes –different spp.	NI		A
30.	Turtle	NI		A
31.	Nile tilapia	*Oreochromis niloticus*		A
32.	Cat fish	*Clarias gariepinus*		A
33.	Barbus	*Barbus barbus*		A

Note:
A=Observation during the fieldwork
B= Recent observation by locals,
EN= Endangered
V= Vulnerable
LR= Lower risk with three subcategories:- cd= conservation dependent, nt= near threatened, lc=least concern

DD= Data deficient
NI= Not Identified

ዕዝል 4፡ በ2002 የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት መሰረት በበቶ፣ ወለቃና አባይ ሸለቆ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ዙሪያ በሚገኙ ቀበሌዎች የሚኖረው ቤተሰብና ህዝብ ብዛት በቁጥር፣

የአስተዳደር ዞን፣	ወረዳና ቀበሌ				
		የነዋሪ ቤተሰብና ህዝብ ብዛት፣			
		ቤተሰብ	ወንድ	ሴት	ድምር
ደቡብ ወሎ	ቦረና				
	በታ መንደጋ	1,065	2,383	2,310	4,693
	የቦረና ድምር	1,065	2,383	2,310	4,693
	ወግዲ				
	ለምለም አምባ	864	1,819	1,826	3,645
	አዲስ አምባ	579	1,273	1,243	2,516
	ከራባ ጎዳና	978	1,963	1,998	3,961
	አብዬ ጎርባ	1,398	2,763	2,994	5,757
	አበሆች	1,012	2,149	2,093	4,242
	ጊንዶ	1,051	2,225	2,197	4,422
	ወረዋዩ	975	2,000	2,093	4,093
	ጎሊ	635	1,298	1,409	2,707
	ሎሚ ውኃ	944	1,937	1,984	3,921
	ወረአቡ	1,154	2,486	2,453	4,939
	አብይ	1,039	2,406	2,399	4,805
	የወግዲ ንኡስ ድምር	10,629	22,319	22,689	45,008
	ከለላ				
	ጀጀባና ሌንጮ	1,160	2,530	2,502	5,032
	ጥራንጥር	978	2,058	2,014	4,072
	አዲስ አምባ	1,039	2,229	2,234	4,463
	የከለላ ንኡስ ድምር፣	3,177	6,817	6,750	13,567
	ሚዳ ኦሮሞ				
	ሪማና ድሬ	1,566	3,453	3,462	6,915
	አዝማና ሽፈሬ አምባ	1,134	2,404	2,326	4,730
	ድጎቢያ ጎባቢት	877	1,780	1,788	3,568
	የሚዳ ኦሮሞ ንኡስ ድምር	3,577	7,637	7,576	15,213
	እነብሴ ሳር ምድር				
	ዞባር ይኳንዳ	679	1,467	1,413	2,880
	የእነብሴ ሳር ምድር ንኡስ ድምር	679	1,467	1,413	2,880
	እናርጅ እናውጋ				
	ሶማ	783	1,678	1,719	3,397
	የእናርጅ እናውጋ ንኡስ ድምር	783	1,678	1,719	3,397
	ሸበል በረንታ				
	አንሸብና ዙጭር	860	1,849	1,872	3,721
	አባራ	415	918	953	1,871
	ቦናያና ሳቃላ	1,088	2,295	2,357	4,652

የአስተዳደር ዞን፣	ወረዳና ቀበሌ				
		የነዋሪ ቤተሰብና ህዝብ ብዛት፣			
		ቤተሰብ	ወንድ	ሴት	ድምር
	አባ ሰላማና ደቦጭ	581	1,220	1,277	2,497
	የሸበል በረንታ ንኡስ ድምር	2,944	6,282	6,459	12,741
	ደራ				
	ሆማ ቦንያ	1,796	3,998	3,915	7,913
	ገብሮ በራሳ	1887	3907	3797	7704
	ደንቢ ብርጀ	1,064	2,314	2,426	4,740
	የደራ ወረዳ ንኡስ ድምር	4,747	10,219	10,138	20,357
	የጠቅላላ ነዋሪ ብዛት	27,601	58,802	59,054	117,856

የመረጃ ምንጭ፡ የወግዲ፣ ከለላና ቦረና ወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች

ዕዝል 5፡ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ በሚገኝባቸው ቀበሌዎች ያሉ የቤት እንስሳት መጠን በቁጥር

ወረዳ/ቀበሌ	ላም	በሬ	ጊደር	ወይፈን	ጥጃ	በግ	ፍየል	አህያ	በቅሎ	ፈረስ	ንብ የገባበት ቀፎ ብዛት		
											ባህላዊ	ዘመናዊ	የሽግግር
ቦረና													
በታ መንደጋ	1153	1385	642	997	582	407	3311	975	19		427	14	
ወግዲ													
ለምለም አምባ	915	1035	335	279	405	29	828	524	34		301	14	
አዲስ አምባ	683	690	319	227	385		1738	483	16		28	3	
ከራባ ጎዳና	1020	1235	693	527	789		2403	667	7		625	15	7
አብዬ ጎርባ	2120	2025	800	704	1008	60	4328	865	8		504	35	4
አበሆች	4100	5200	295	2150	520	130	4689	422	10	1	810	60	5
ጊንዶ	702	1033	373	342	325	61	2286	522	8		950	135	4
ወረዋዩ	1105	1127	246	334	319	52	2403	367	4			15	4
ጎሊ	701	1253	219	289	355	568	984	674	5		250	10	1
ሎሚ ውኃ	401	829	127	176	162	326	469	416	9	11	293	19	2
ወረአቡ	1750	1490	345	280	164	604	2138	457	4	2	345	29	39
አብይ	1352	1469	585	882	607	2140	3027	614	17		124	42	4
ንኡስ ድምር	14849	17386	4337	6190	5039	3970	25293	6011	122	14	4230	377	70
ከለላ													
ጀጀባና ሌንጮ	1345	1522	972	1150	645	391	4750	980	55	1	450		
ጥራንጥር	1800	915	918	700	926	150	6100	415	21		500	7	1
አዲስ አምባ	1653	918	523	600	735	700	800	420	10		450	5	1
ንኡስ ድምር	4798	3355	2413	2450	2306	1241	11650	1815	86	1	1400	12	2

ወረዳ/ቀበሌ	ላም	በሬ	ጊደር	ወይፈን	ጥጃ	በግ	ፍየል	አህያ	በቅሎ	ፈረስ	ንብ የገባበት ቀፎ ብዛት		
											ባህላዊ	ዘመናዊ	የሽግግር
ጠቅላላ ድምር	20800	22126	7392	9637	7927	5618	40254	8801	227	15	6057	403	72

የመረጃ ምንጭ፡ የወግዲ፣ ከለላና ቦረና ወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች

ዕዝል 6፡ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ በሚገኝባቸው ቀበሌዎች በ2003/04 የምርት ዘመት የተገኘ የሰብል ምርት፣

	በ2003/04 የተገኘ ምርት በኩንታል፣												
	ጤፍ	ማሽላ	ስንዴ	በቆሎ	ገብስ	ባቄላ	አተር	ሽንብራ	ጓያ	ቦሎቄ	ኑግ	ተልባ	ጠቅላላ ምርት በኩ/ል
ቦረና													
24	5,214	10,670	3,797	748	330	322	322	222	160	312			22,097
ወግዲ													
ለምለም አምባ	23,237	64,547	19,180	31,167				6,197	5,975	5,164	1,033	57	156,556
አዲስ አምባ	1,979	5,498	1,634	2,655				528	509	440	88	5	13,334
ከራባ ጎዳና	3,209	8,913	2,648	4,304				856	825	713	143	8	21,617
አብዬ ጎርባ	2,876	7,988	2,374	3,857				767	739	639	128	7	19,374
አበሆች	3,107	8,631	2,565	4,168				829	799	690	138	8	20,934
ጊንዶ	3,039	8,441	2,508	4,076				810	781	675	135	7	20,474
ወረዋዩ	3,387	9,408	2,796	4,543				903	871	753	151	8	22,819
ጎሊ	2,478	6,883	2,045	3,323				661	637	551	110	6	16,694
ሎሚ ውኃ	3,719	10,330	3,070	4,988				992	956	826	165	9	25,056
ወረአቡ	3,743	10,397	3,089	5,020				998	962	832	166	9	25,217
አብይ	2,525	7,014	2,084	3,387				673	649	561	112	6	17,013
	53,298	148,049	43,992	71,487	0	0	0	14,213	13,705	11,844	2,369	130	359,087
ከለላ													
ጀጀባና ሌንጮ	5,810	14,709	3,689	6,917				1,162	2,490	1,549	516	194	37,036
ጥራንጥር	4,221	10,685	2,680	5,024				844	1,809	1,125	375	141	26,904
አዲስ አምባ	5,269	13,341	3,346	6,273				1,054	2,258	1,405	468	176	33,590
ንኡስ ድምር	15,300	38,735	9,715	18,214	0	0	0	3,060	6,557	4,079	1,359	511	97,530
ጠቅላላ ድምር	73,812	197,454	57,504	90,449	330	322	322	17,495	20,422	16,235	3,728	641	478,714

የመረጃ ምንጭ፡ የወግዲ፣ ከለላና ቦረና ወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች

ዕዝል 7. ዋና ዋና የጅኦኤስ መረጃዎች

ተቁ	X-Coordinate	Y-Coordinate	Altitude	ልዩ መጠሪያ	ማብራሪያ
1.	449632	1193632	1480 m	የአባይና ደንቆሮ ወንዝ መገናኛ	

ተቁ	X-Coordinate	Y-Coordinate	Altitude	ልዩ መጠሪያ	ማብራሪያ
2.	455400	1191701	1925 m	አርብ ገበያ	ዶክስ ቀበሌ
3.	473620	1187976	2675 m	መካነ ሰላም	ቦረና ወረዳ ከተማ
4.	460851	1183863	2436 m	አባይ በር-የገጠር ከተማ	ቦረና ወሎ ጎጃም መስመር
5.	442774	1176366	1287 m	የአባይና ጨዬ ወንዝ መገናኛ	የእነብሴ ሳር ምደርና እናርጅ እናውጋ
6.	445564	1178684	1152 m	የአባይ ድልድይ	ወሎ ጎጃም መስመር ዋና መሻገሪያ/55 ኪ.ሜ
7.	462958	1184763	2399 m	የ ቀበሌ 024/በታ/ መገንጠያ	ቦረና ወሎ ጎጃም መስመር/12 ኪ.ሜ
8.	454652	1177184	2373 m	የ ቀበሌ 024/በታ/ ማዕከል	ጤና ኬላው አጠገብ/31 ኪ.ሜ
9.	442770	1169738	1587 m	አባይና የሹም መገናኛ አጠገብ	በሰራት ጎት ፈሪ መቆሚያ አካባቢ
10.	443630	1171526	1725 m	ቀበሌ 024	የደኑ ደንበር
11.	444597	1172567	1845 m	ቀበሌ 024	በሰራት
12.	445063	1173882	2012 m	ደብር አባይ ማሪም ቤ/ክ አጠገብ	መመልከቻ ቦታ
13.	452568	1176823	2384 m	ወግዲ ከተማ	የወረዳ ከተማ
14.	454971	1159029	2206 m	ገዛዛ አቦ ገዳም	29 ኪ.ሜ
15.	456435	1157073	2267 m	ገዛዛ አቦ ገዳም መገንጠያ	26 ኪ.ሜ
16.	444805	1146046	1108 m	የአባይና ወለቃ ወንዝ መገናኛ	ቀበሌ 016
17.	454942	1147168	1131 m	ጥቁር እንጨት	ቀበሌ 015
18.	459037	1147579	1171 m	የቀበሌ 015 እና 013 ድንበር	ጭባንጭቦ ወንዝ የድንበር ምልክት ነው
19.	463841	1147043	1215 m	የደራሞች መሻገሪያ	ደረባ ያለበት ቀበሌ 013
20.	471042	1148542	1233 m	የወለቃና በቶ ወንዝ መገናኛ	ቀበሌ 013
21.	471805	1150348	1258 m	የቀበሌ 013 እና 09 ድንበር	
22.	471903	1150549	1258 m	የቀበሌ 09 እና 08 ድንበር	ደረቅ ወንዝ የድንበር ምልክት ነው
23.	474726	1155372	1326 m	የቀበሌ 08 እና 07 ድንበር	ኮኪ ወንዝ የድንበር ምልክት ነው
24.	479018	1163464	1423 m	የተፈጥሮ ደኑ የመጨረሻ ድንበር	የቀበሌ 03 እና 06 ድንበር
25.	473626	1170844	2378 m	የተፈጥሮ የአለት ድልድይ	ቀበሌ 06 ወለቃ ወንዝ ወግዲና ከላላን የሚያገናኝ
26.	496932	1161896	2165 m	ቆርኬ መገንጠያ	አባ ጋስጫ ጊዮርጊስ ገዳም መገንጠያ/32 ኪ.ሜ
27.	479565	1157161	1863 m	አባ ጋስጫ ጊዮርጊሰ ገዳም ከስር	ቀበሌ 020 ጥራንጥር/42 ኪ.ሜ
28.	479336	1157110	1926 m	አባ ጋስጫ ጊዮርጊሰ ገዳም ከላይ	ቀበሌ 020 ጥራንጥር
29.	500388	1170253	2524 m	ከላላ ከተማ	የወረዳ ከተማ
30.	498396	1153961	1918 m	ደገር	የቀበሌ 014 ማዕከል/26 ኪ.ሜ
31.	511356	1152814	1544 m	ከላላ ጃማ መስመር ድልድዩ	በቶ ወንዝ ቀበሌ 012 ኮባ

ተቁ	X-Coordinate	Y-Coordinate	Altitude	ልዩ መጠሪያ	ማብራሪያ
				ዝቅ ብሎ	ሸለቆ
32.	506094	1147142	1478 m	ጃማና ሰ/ሸዋ ድንበር	ጠቀስ ወንዝ የድንበር ምልክት
33.	499660	1143505	1419 m	ቀይ ገደል መጀመሪያ አካባቢ	ቀበሌ 013/አናራት
34.	494795	1143737	1391 m	ዳራ የመስኖ እርሻ ቡርቃ አካባቢ	ቀበሌ 013/አናራት
35.	493364	1144181	1370 m	አጤሳ ወንዝ	የቀበሌ 013 እና 014 ድንበር
36.	492928	1144199	1367 m	ከላላ ሪማ ኦሮሞ መንገድ መሻገሪያ በቶ ወንዝ	ቀበሌ014/ደገር
37.	492196	1145023	1429 m	ኩበት መጠያ አካባቢ	ቀበሌ 014 ካሁን በፊት የታረሰና እያጋገመ ያለ ደን
38.	491846	1146493	1416 m	ለቡ/መረቆ/ፍልፈል/ አካባቢ	የቀበሌ 014 እና 017 ደንበር
39.	490328	1146501	1508 m	የቱሉ ጅሌ ደን	መመልከቻ ቦታ/ቀበሌ 017
40.	488865	1147034	1396 m	የአገዩና ሚራቱ ደን መጀመሪያ ጠቆኖ/ጀጀባና ሊጮ ወንዝ	የቀበሌ 017 እና 019 ድንበር
41.	484037	1148516	1593 m	ወደ ሚራቱ መንደር ጎፎ ወንዝ ጠጋ ብሎ	የቀበሌ 019 እና 020 ድንበር
42.	485941	1151897	1890 m	የቀበሌ 019፣ 017 እና 018 መገናኛ	
43.	488112	1157366	2075 m	አቤቱ ውሃ የገጠር ከተማ	የቀበሌ 018 ማዕከል
44.	515739	1190243	2719 m	ጭጭፍቱ ወደ ከላላ መገንጠያ	